# የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 896/2014

Cooperative Organizations Directive No. 896/2014

ECC

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን

Ethiopian Cooperative Commission

መጋቢት 1፥ 2014

# የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 896/2014 ዓ.ም

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት የማይተካ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በአገራችን በርካታ የተለያዩ ዓይነትና ደረጃ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው ይገኛሉ፡፡ በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖረው ሕዝብ ያለው ኢኮኖሚ አቅም አነስተኛ ነው፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የህብረተሰቡን ችግር በማቃለል የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ኅብረት ሥራን በተመለከተ የኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጥና የሚመዘግብ በፌዴራልና በክልል መንግስታት የተቋቋሙትን አካላት ማጠናከር በማስፈለጉ፡፡

አሁን ያሉትንም ሆነ ወደፊት የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶችና የአደረጃጀት ደረጃዎች፣ ስለ አዋጭነት ጥናት፣ ስለ ንግድ ሥራ ዕቅድ እና ስለ መተዳደሪያ ደንብ በግልፅ ለማሳየትና ወደ ተግበር ለመተርጎም እንዲያስችል፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ወጥ የሆነ አደረጃጀት፣ የምዝገባ እና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ማዘመን በማስፈለጉ፣ አባላት እና አስፈፃሚ አካላት እንዲውቁትና የሥራ መመሪያ ሆኖ እንዲያገለግል በማድረግ ስለ አባላት፣ አመራር አካላት፣ የቅጠር ሰራተኞች ተግባርና ሃላፊነትን ማሻሻል በማስፈለጉ፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት ስለ የካፒታል አመሰራረትና አማራጭ ፋይናንስ ምንጮች እና ስለትርፍ ክፍፍል እና የብድር አስተዳደር፣ ስለሚዋሃዱበት፣ ስለሚከፈሉበትና ስለሚፈርሱበት እና ስለ ልዩ መብቶች አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት፣ አግባብ ያለው ባለስልጣን ጋር፣ ከባለድርሻ አካላት፣ ከአቅም ገንቢዎች፣ እርስ በርሳቸው  ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ስለሚኖራቸው የግንኙነት አግባብ ግልፅ አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፣

"የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 76(3) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

*ይህ መመሪያ "የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 896 / 2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡"*

## 2. ትርጓሜዎች

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ውስጥ፡

1) **በአዋጅ ቁጥር 985/2009** ትርጓሜዎች በዚህ አንቀጽ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
2) **አዋጅ፡-** ማለት የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ነው፡፡
3) **አነስተኛ የመድን ዋስትና፡-** ማለት የኅብረት ስራ ማህበራት አባላት ሊያጋጥማቸው ከሚችል ስጋት ወይም ጉዳት ለኪሳራው ተመጣጣኝ የሆነ የመድን መግቢያ ዋጋ (አረቦን) በማስከፈል ከሚያጋጥም ኪሳራ ለመከላከል ወይም ለመታደግ የሚያስችል አሰራር ነው ፡፡
4) **ማበረታቻ ፡- ማለት** ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓላማ ስኬትማነት የላቀ አስተዋፅኦ ለአበረከቱ አባላት፣ አመራር አካላትና ቅጥር ሰራተኞች የስራ ተነሳሽነታቸውን ለማሳደግ እና ሞራላቸውን ለመገንባት በገንዘብ ወይም በአይነት ወይም እውቅና በመስጠት ወይም በምስጋና የሚሰጥ የማነቃቂያ አይነት ሆኖ የቅጥር ሠራተኛው ላስገኘው ተጨማሪ ውጤት የኅብረት ስራ ማህበሩን ዓላማና ዕቅድ መሠረት አድርጎ የሚሰጥ የገንዘብ ወይም ዓይነት ክፍያ ወይም የሚሰጥ የደረጃ እድገት ያጠቃልላል፡፡
5) **የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት ትስስር፡-** ማለት ኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት ጋር በምርት ወይም በአገልግሎት ወይም በምርት እና በአገልግሎት አቅርቦት የሚገናኙበት እንዲሁም የአባላትን ምርት ወይም አገልግሎት ለሸማቹ ወይም ለተገልጋዩ አገልግሎት የሚሸጡበት የግብይት ሥርዓት ሲሆን የፋይናንስ ግብይቱንም ይጨምራል፡፡
6) **የፋይናንስ ግብይት ትስስር፡-** ማለት የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥም ወይም ስራ ላይ ያልዋለ ተቀማጭ ገንዘብ ሲኖር ወይም የአባላትን የብድር ፍላጎት ለማሟላት እንዲቻልየፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የማበደር ፍላጎትና አቅም ካላቸው ባንኮች፣ የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት፣ የሊዝ ፋይናንስ ተቋማት፣ ከመሰል የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት፣ የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ካልሆኑ እና ከሌሎች አቅም ገንቢ ተቋማት ጋር የጋራ ጥቅም በሚያስገኝ መልኩ ውጤታማና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ የሚደረግ የፋይናንስ ግብይት ትስስር ነው፡፡
7) **የአነስተኛ መድን ዋስትና ውክልና፡-** ማለት ዋስትና መግባት ከሚፈልጉ የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በውሉ መሰረት የመድን መግቢያ ዋጋ (አርቦን) ተቀብሎ በውሉ ላይ የተመለከተው አደጋ በደረሰ ጊዜ ዋስትና ለገባው አባል የተወሰነውን ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት የውክልና ውል ነው፡፡
8) **"የኅብረት ሥራ ማህበራት የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ፡-** ማለት በኅብረት ሥራ ማህበር ደረጃ ተመስርቶ በሚያከናውኑት ዓላማ እና ተግባር ላይ የቴክኒክ ምክር አገልግሎት የሚሰጥ የባለሙያዎች እና የበጎ ፍቃደኞች ኮሚቴ ነው፡፡
9) **ቋሚ ንብረት፡-** ማለት የረዥም ጊዜ የሚጨበጥ ጠቀሜታ ያለው የተናጥል ዋጋው በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚወሰን ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ ጠቃሚ ህይወት የሚኖረውና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ እንደ ተክል፣ እቃዎች እና ንብረት ያለውን የሚያጠቃልል ሲሆን በሒሳብ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ያለ ንብረትን የሚያካቲት ነው፡፡
10) **በመጣራት ላይ ያለ ሂሳብ፡-** ማለት የሂሳብ አጣሪዎች የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሀብትና ንብረት በማሰባሰብ ወደ ጥሬ ገንዘብ በመለወጥ የሚያጠራቅሙበት እና ወጪ ያደረጉ ክፍያዎችን የሚፈፅሙበት የባንክ ሂሳብ ማለት ነው፡፡

11) **ኅብረት ሥራ ማኅበራት ማዋሀድ፡-** ማለት በንብረት ባለቤትነት፣ በአስተዳደር፣ በሥራ አካባቢ፣ በስያሜ፣ በተግባር ከአንድ በላይ የህጋዊ ሰውነት የነበራቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራኅብረት ሥራ ማኅበራት ት ጠንካራ ኅብረት ሥራ ማህበር ለመፍጠር እና አላስፈላጊ እርስ በእርስ ውድድርን ለማስቀረት ሲሉ አንድ ሆነው ለመስራት የሚያደርጉት መቀላቀል ነው፡፡

12) **የኅብረት ሥራ ማህበራት መከፈል፡-** ማለት በንብረት ባለቤትነት፣ በአስተዳደር፣ በሥራ አካባቢ፣ በስያሜ፣ በተግባር አንድ የህጋዊ ሰውነት የነበረውን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወደ ሆኑ ወደ ተመሳሳይ ወይም ወደ ተለያያ ዓይነት ኅብረት ሥራ ማህበራት በመከፈል የአባላትን ፍላጎት እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና ተደራሽ ለማድረግ የሚሰራ ነው፡፡

13) **ሂሳብ ማጣራት፡-** ማለት የመፍረስ ወይም የማዋሃድ ውሳኔ የተሰጠበትን የኅብረት ሥራ ማህበር ንበረት ማሰባሰብ፣ ንበረት ወደ ጥሬ ገንዘብ መቀየር፣ ያለበትን ዕዳ የመለየትና መክፈል፣ የማህበሩን ጠቅላላ እንቅስቃሴ መዝጋት እና የሂሳብ አቋም ማሳወቅ ማለት ነው፡፡

14) **የሂሳብ አጣሪዎች ፡-** ማለት አግባብ ባለው ባለስልጣን የኅብረት ሥራ ማህበራትን ሂሳብ የማጣራት ሥራ እንዲያከናውኑ የሚመደቡ ባለሙያዎች ማለት ነው፡፡

15) **የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን አገልግሎት፡-** ማለት የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሚያመርቱት ምርት ወይም አገልግሎት ገበያው የሚፈልገውን መጠንና የጥራት ደረጃ ያሟላ እንዲሆን ሙያዊ ምክር መስጠት እና ስለ ኅብረት ሥራ ጽንሰ ሐሳብ እና ፍልስፍና ግንዛቤ፣ ትምህርት እና መረጃ መስጠት ነው፡፡

16) **የመስራች ኮሚቴ፡-** ማለት ለመደራጀት ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች በመለየት፣ ያለውን የአከባቢውን ሀብት በመለየት፣ የአዋጭነት ጥናት በማጥናት፣ የንግድ ሥራ እቅድ በማዘጋጀት እና የመተዳሪያ ደንብ በማዘጋጀት የኅብረት ሥራ ማህበሩን የመመስረት ስራ የሚሰሩ ለመደራጀት ፍላጎት ካላቸው አካለት፣ ከአግባብ ያለው ባለስልጣን እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካለት የተውጣጡ የሰዎች ስብስብ ነው፡፡

17) **ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማህበር፡-** ማለት በአባላት ፍላጎት እና ዓላማ ላይ የተመሰረተ ለአባለት አስፈላጊ የሆኑ በማምረትና አገልግሎት መስጠት ተግባር ላይ የሚደራጁ ማለትም የብድር አቅርቦት፣ የተሻሻሉ ምርጥ ዘር አቅርቦት፣ የግብርና መሣሪያዎችን፣ የአፈር ማዳበሪያዎች እና ኬምካሎች፣ የአካባቢ ጽዳትና ንፅህና፣ ጤናን አገልግሎት እና የመሳሰሉትን የተለያዩ ግቦችን ለማሳካት የተቋቋመ ሁለገብ ዓላማ ያለው የኅብረት ሥራ ማህበር ይባላል፡፡

18) **ተወካይ፡-** ማለት አወካከሉ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ሆኖ በመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በግለሰብ አባላት ተወክሎ በጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ የሚሰጥ ወይም በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ወይም በኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን በጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ተክቶ በማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ በመገኘት ድምፅ የሚሰጥ ግለሰብ ነው፤

19) **ኅብረት ሥራ ማህበር የስራ ክልል፡-** ማለት በማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደርያ ደንብ የተወሰነና አግባብ ባለው ባለስልጣን የተመዘገበ የስራ ክልል ነው፡፡

20) **አቅም ገንቢ አካላት ፡-** ማለት ለኅብረት ሥራ ማህበራት እድገትና መሻሻልና መዘመን የሚያግዙ የእውቀት፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂ እና የአሰራር ክፍተቶችን በመሙላት የአቅም ግንባታ ድጋፍ የሚደርጉትን የሚገነቡ መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን ወይም ድርጅትቶችን ማለት ነው፡፡

21) በዚህ ደንብ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ያካትታል፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በመላው ሀገሪቱ በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 መሰረት በተለያየ ዓይነት እና ደረጃ በተደራጁ እና በሚደራጁ ኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የኅብረት ሥራ ማህበራት መርሆዎች

በዚህ የአደረጃጀት መመሪያ መሰረት የሚደራጅ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የኅብረት ሥራ ማህበራት መርሆዎች መሰረት መደራጀት እና ሥራውን መምራት ይኖርበታል፡፡

1) **አባልነት ለሁሉም ክፍት እና በፈቃደኝነት፡-** የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባልነት በማኅበራቱ አገልግሎት ለመጠቀም ለሚፈልጉና የአባልነት ግዴታዎችን ለመቀበል ፈቃደኛ ለሆኑ ሰዎች ሁሉ በጾታ፣ በማኅበራዊ አቋም፣ በዘር፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳተኝነት ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ ለሁሉም ክፍት ይሆናል፡፡
2) **በአባላት ቁጥጥር የሚደረግባቸው ዲሞክራሲ ተቋም፡-** የኅብረት ሥራ ማኅበራት ፖሊሲ በማውጣትና ውሳኔዎችን በማስተላለፍ የነቃ ተሳትፎ በሚያደርጉ አባላት የሚመሩ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች፣ እያንዳንዱ አባል እኩል ድምጽ ያለው እንዲሁም አንድ አባል አንድ ድምጽ ብቻ ያለው ይሆናል፡፡
3) **የአባላት ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት፡-** ከትርፍ ላይ ለመጠባበቂያ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ተቀንሶ ከተቀመጠ በኋላ አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ በገዙት ዕጣ መጠን እና ባደረጉት ተሣትፎ መሠረት ቀሪው ትርፍ ይከፋፈላል፡፡
4) **ነፃና የራስ በራስ አስተዳደር፡-** ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከሌሎች አካላት ጋር መንግሥትንም ጨምሮ ስምምነት የሚያደርጉት ወይም ከኅብረት ሥራ ማኅበራቸው ውጭ ከሚገኝ ምንጭ ገንዘብ በመበደር ካፒታላቸውን ማሳደግ የሚችሉት የአባላት ዲሞክራሲያዊ ቁጥጥርን በሚያረጋግጥ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራቸውን የራስ በራስ ማስተዳዳር መብት በሚጠብቅ እንዲሁም የራስ አገዝ ባህሪውን በማይነካ ሁኔታ መሆን ይኖርበታል፡፡
5) **ተከታታይ ትምህርት፣ ስልጠናና መረጃ መስጠ**ት፡- የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት፣ ተመራጮች፣ ሥራ አስኪያጅ እና ሠራተኞች ለኅብረት ሥራ ማኅበራቸው ዕድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋሉ፤ ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ምንነትና ጥቅም ለሕዝቡ በተለይም ለወጣቱ ያስተዋውቃሉ፡፡
6) **ከሌሎች አቻ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ጋር ኅብረት መፍጠር፡-** በአካባቢ፣ በሀገር አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት መዋቅሮች ጋር በመተባበር የኅብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴን በማጠናከር አባሎቻቸውን በሚገባ ያገለግላሉ፡፡
7) **ለአካባቢ ዘላቂ ልማት ጥረት ማድረግ፡-** የኅብረት ሥራ ማኅበር አባሎቻቸው ባፀደቋቸው ፖሊሲዎች አማካኝነት በአካባቢያቸው ላለው ኅብረተሰብ ዘላቂ ልማት ለማምጣት የሚያስችል ተግባር ያከናውናሉ፡፡

## 5. የኅብረት ሥራ ማህበራት እሴቶች እና የአባላት የሥነ ምግባር እሴቶች

1) በዚህ የአደረጃጀት መመሪያ መሠረት የሚደራጅ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሚከተሉትን እሴቶች ይኖሯቸዋል፡፡

   ሀ) ራስን በራስ መርዳት፣

   ለ) የግል ሃላፊነትን መወጣት፣

   ሐ) ዴሞክራሲን ማስፋፋት፣

   መ) እኩልነት፣

   ሠ) ፍትሃዊነት፣

   ረ) ወንድማማችነት፣

2) በዚህ አንቀጽመሠረት በተደረጃ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ውስጥ አባል የሚሆኑ ግለሰቦች የሚከተሉትን የአባላት የሥነ-ምግባር እሴቶች ይኖሯቸዋል፣

ሀ) ታማኝነት፣

ለ) ግልፀኝነት፣

ሐ)ተጠያቂነት፣

መ)አሳታፊነት፣

ሠ) ማህበራዊ ኃላፊነት፣

ረ) ለሌሎች ማሰብ፣

## 6. የኅብረት ሥራ ማህበር ዓላማዎች

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት የሚቋቋሙ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደተቋቋሙለት ዓላማ እና ባህሪ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖራቸዋል፤

ሀ) አባላት በተናጠል በመሥራት ሊወጧቸው የማይችሏቸውን የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ችግሮችን በተባበረ ጥረት መወጣት፣ መቋቋም እና መፍታት፤

ለ) አባላት ያላቸውን ዕውቀት፣ ሀብትና ጉልበት በማቀናጀት፣ ተወዳዳሪ፣ ዘመናዊና ውጤታማነትን ማስፈን፤

ሐ) በአባላት ዘንድ በራስ መተማመንን ማጎልበት፤

መ) ለማምረት የሚያስፈልገውን ወጪና የአገልግሎት ዋጋን በመቀነስ አባላት የሚፈልጉትን ግብአት ወይም አገልግሎት በአነስተኛ ዋጋ እንዲያገኙ ማድረግ እና ምርታቸው ወይም አገልግሎታቸው የተሻለ የገበያ ዋጋ እንዲያገኝ ማስቻል፤

ሠ) የቴክኒክ ዕውቀትን እና የሥራ ፈጠራን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች እንዲስፋፉ ማድረግ፤

ረ) በአባላት መካከል የቁጠባ ባህል እንዲዳብር እና እንዲስፋፋ ማድረግ፤

ሰ) ለአባላት የብድር አገልግሎትን በመስጠት ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፤

ሸ) ለአባላት የብድር የሕይወት መድን ዋስትና መስጠት፤

ቀ) አባላቱ በግላቸው ቢሰሩ ኖሮ ሊደርስባቸው የሚችለውን ጉዳትና ኪሣራ በጋራ በማካፈል የእያንዳንዱ ሰው ጉዳትና ኪሣራ መቀነስ፤

በ) አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አቅማቸውንና ባህላቸውን ማጎልበት፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኅብረት ሥራ ማህበራትን ስለማደራጀት እና የመደራጀት ጥያቄ አቀራረብ

## 7. የኅብረት ሥራ ማህበራትን ስለማደራጀት

በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 7፣ 14 እና 15 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኅብረት ሥራ ማህበር ለመደራጀት ሲወሰን አግባብ ላለው ባለስልጣን በሚከተሉት የማደራጀት ቅድመ-ሁኔታዎች ተግባራዊ ያደርጋል፤

1) ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች የመደራጀት ጥያቄያቸውን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2) በሚቀርበው የመደራጀት ጥያቄ ላይ የአመልካቾቹ ስም፣ አድራሻ፣ እድሜ፣ ስራ እና ፊሪማ አብሮ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

3) ጥያቄ አቅራቢዎችን በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ በመጥራት በጥያቄያቸው መሰረት በፍላጎታቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣

4) የመደራጀት ፍላጎቱን በማረጋገጥ የመስራች ኮሚቴ ያቋቁማሉ፣
5) ለሚቋቋመው የመስራች ኮሚቴ አባላት ተግባርና ኃላፊነት መስጠትና ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይደረጋል፣
6) የሚቋቋመው የመስራች ኮሚቴ አስፈላጊ የሆኑ የአዋጭነት ጥናት በማካሄድ፣ የንግድ ሥራ ዕቅድ እና መተዳደሪያ ደንቦችን ያዘጋጃል፣
7) ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠነዶችን እና ማህተሞችን ያሳትማል፣ የባንክ ሂሳብ ቁጥር (አካውንት) የመክፈት ተግባራትን ማከናወን አለበት፡፡
8) የመስራች ኮሚቴው አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ የመስራቾች የምስረታ ጉባኤ በማካሄድ የተዘጋጁ ሠነዶችን ያፀድቃል፡፡
9) በምስረታ ጉባኤው ላይ በእለቱ በሚመረጡት አስመራጭ ኮሚቴዎች አማካኝነት ቀደም ሲል በተዘጋጀው የኮሚቴዎች መሰምረጫ መስፈርት ተከትለው የሥራ አመራር፣ የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት እና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴ አባላትም እንዲመረጡ ይደረጋል፡፡
10) የመስራች ኮሚቴው ሲሰራባቸው የነበሩትን ማንኛውንም ሠነድና ንብረት አዲስ ለተመረጠው የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ያስረክባል፡፡ በሪክክቡም ላይ በመገኘት ድጋፍ ያደርጋል፡፡
11) ለመደራጀት ጥያቄ ያቀረቡ አካላት የሚጠበቅባቸውን አሟልተው ሲገኙ አዲስ በተመረጡት የኅብረት ሥራ ማህበሩ አመራር አካላት አማካኝነት ለምዝገባ አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶችን በማሟላት ለምዝገባ ጥያቄ በማቅረብ የማደራጀት ተግባር የሚከናወን ይሆናል፡፡
12) በማህበረሰብ ተፋሰስ ላይ የሚደራጁት የመሬት ተፋሰስን መሰረት አድረጎ የአስተዳር ወሰን ተከትለው በመሆኑ የሚጠናው አዋጭነት ጥናት ትኩረት የሚያደረገው ተፋሰሱን ተከትሎ በሚወሰነው መሰረት ይሆናል፡፡
13) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የምዝገባ ሠርተፊኬቱን ባገኘ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ መደበኛ ስራውን መጀመር ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ያለምንም አሳማኝ ምክንያት መደበኛ ስራውን ያልጀመረ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በአዋጅ 985/2009 አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት እርምጃ ይወሰዳል፡፡

## 8. <u>በኅብረት ሥራ ማህበር የመደራጀት ጥያቄ አቀራረብ</u>

1) በመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ለመደራጀት የግለሰብ አባላት የሚያቀርቡት የእንደራጅ ጥያቄ አቀራረብ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ) በመኖሪያ አካባቢ፣ በስራ ቦታ፣ ተመሳሳይ የሙያ ችሎታ መደራጀት የሚፈልጉ ግለሰቦች በአካባቢያቸው ወደሚገኘው የሚመለከተው አግባብ ያለው ባለስልጣን በመሄድ በአካል ወይም በተወካዮቻቸው አማካኝነት ጥያቄያቸውን ያቀርባሉ፡፡

ለ) ቁጥራቸው ከ50 በላይ የሆኑ ተመሳሳይ ፍላጎት እና የጋራ ችግር ያላቸው ግለሰቦች፣

ሐ) አግባብ ባለው ባለስልጣን በሚያዘጋጀው ቅፅ መሠረት የሁሉንም የሚደራጁ ግለሰቦች መታወቂያ ፎቶ ኮፒ፣ ስም ዝርዝራቸውን እና ፊርማቸውን አስፈርመው መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

መ) በሙያ የሚደራጁ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር እያንዳንዱ አባል ስለሙያዊ ብቃቱ ጉዳዩ ከሚመለከተው የሥራ ዘርፍ የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

ሠ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 (መ) ላይ የተጠቀሰው የሙያ ብቃት የሚቀርብባቸው በህግ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲያወጡ በሚያስገድዱ የስራ መስኮች ብቻ ላይ ይሆናል፡፡

ረ) በልዩ የሙያ መስክ የተደራጁ ኅብረት ሥራ ማህበራት እሴት ጨምረው ለሚያመርቱት ምርት ወይም ለሚሰጡት አገልግሎት የጥራት ማረጋገጫ ጉዳዩ ከሚመለከተው ዘርፍ ምስክር ወረቀት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ሰ) አግባብ ያለው ባለስልጣን የግለሰቦችን የአጭርና የረጅም ጊዜ ግብ ለመረዳት የሚያስችል የጋራ ውይይት ያደርጋል፣

ሸ) በመደራጀት ጥያቄ ላይ የጋራ መግባባት ሲደረስ የመስራች ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

ቀ) ግዴታቸውን ለመወጣት ፈቃደኛ የሆኑ ግለሰብ ጠያቂዎች አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚያዘጋጀው የአባልነት ማመልከቻ ቅፅ መሠረት ጥያቄያቸውን እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡

2) የግለሰብ የአባልነት መጠየቂያ ማመልከቻ ቅፅ የሚከተሉት ይዘቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የአባሉን ሙሉ ስም፣ ፆታ፣ ዕድሜ

ለ) የትምህርት ደረጃ፣

ሐ) አድራሻ፣

መ) የስራ ዓይነት፣

ሠ) የሚደራጅበት ዓላማ፣

ረ) ማመልከቻው የቀረበበት ቀንና ፊርማ፣

3) ቀድሞ በተደራጀ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ውስጥ የአባልነት ጥያቄ የሚቀርብ ከሆነ የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ባዘጋጀው የአባልነት ማመልከቻ ቅፅ መሠረት ይሆናል፡፡

4) በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ለመደራጀት ጥያቄ የሚያቀርቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጥያቄ አቀራረብ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ) በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ የፀደቀ በማህተም የተረጋጋጠ ቃለ-ጉባኤ ኮፒ፣

ለ) አመልካች ኅብረት ሥራ ማህበራት በተመዘገቡበት አግባብ ያለው ባለስልጣን በመቅረብ የሊቀ-መንበር ወይም የተወካይ ስም እና ፊርማ ያረፈበት የጥያቄ ማቅረቢያ ቅፅ የተሞላ፣

ሐ) ከማመልከቻው ጋር የዘመኑን የኦዲት ሪፖርት የትርፍና ኪሳራ መግለጫ አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

መ) የመደራጀት ጥያቄ በፅሁፍ እንደደረሰው አግባብ ያለው ባለስልጣን ማመልከቻውን በአግባቡ በማየት ጥያቄው ተገቢነት እንዳለው በማረጋገጥ የምስረታ ሂደቱን መጀመር ይኖርበታል፡፡

ሠ) አግባብ ያለው ባለስልጣን የቀረበለትን ማማልከቻ ከገመገመ በኃላ ጥያቄው በጠቅላላ የጉበኤው ልዩ ውሳኔ መሰረት ፀድቆ መምጣቱን ያረጋግጣል፣

ረ) አግባብ ያለው ባለስልጣን የመደራጀት ጥያቄውን የማይቀበል ከሆነ በአምስት ቀናት ውስጥ ምላሹን ጥያቄውን ላቀረበው አካል በቃል ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በፅሁፍ መስጠት ይኖርበታል፡፡

ሰ) ለመደራጀት ጥያቄ የሚያቀርብ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ከተመሠረተበት ሦስት ዓመት የሞላው መሆን አለበት፡፡

ሸ) ከምስረታ በኋላ ሌሎች ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸው እና የመተዳደሪያ ደንብ ግዴታዎችን ተቀብሎ ለመፈፀም ፈቃደኛ የሆኑ መሰረታዊ ወይም ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች በአባልነት ሊታቀፉ ይችላሉ፡፡

ቀ) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ ከ1 እስከ 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና ፌዴሬሽኖች ሲመሰረት የአባልነት ግዴታቸውን መወጣት የሚችሉ ሌሎች መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች አባል መሆን ይችላሉ፡፡

## 9. <u>የማህበረሰብ የተፋሰስ ልማትን መሰረት የደረገ አደረጃጀት</u>

1) የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበር አባል የሚሆኑት በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ውስጥ የተደነገገው መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ የማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1223/2012 አንቀጽ 11 ን/አንቀጽ 1-5 ውስጥ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ የሚደራጁና ሠርተፊኬት የሚያገኙ ይሆናል፡፡

2) በማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1223/2012 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ተገቢውን መስፈርት አሟልተው የተገኙ በተፋሰሱ ውስጥ የሚኖሩ ልዩ ትኩረት የሚያሻቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

3) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በከኅብረት ሥራ ማህበሩ መርህና እሴት በመነሳት ተፋሰሱ ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋዊን የተለየ ትኩረት በመስጠት ሊደግፋቸው ይችላል፡፡

4) በተፋሰስ ልማቱ ውስጥ ለሚኖሩ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋዊን ስለሚደረግላቸው ልዩ ትኩረት፣ ስለሚያገኙት ጥቅም እና ክብር እንዲሁም በዘላቂነት ኑሮዋቸው የሚሻሻልበት በተመለከተ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በሚወስኑት መሰረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

## 10. <u>በሞግዚት አማካኝነት ሲለሚደረግ አባልነት</u>

1. ማንኛውም ዜጋ እድሜው ከ18 አመት በላይ የሆነ በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 በተደነገገው መሰረት መደራጀት ይችላል፡፡ ሆኖም የማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1223/2012 አንቀጽ 11 ን/አንቀጽ 4

መሰረት እድሜቸው ከ18 አመት በታች የሆኑት ወጣቶች በሞግዚቶቻቸው አማካኝነት በማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች በኅብረት ሥራ ማህበር መደራጀት ይችላሉ፡፡

2.እድሜያቸው ለአባልነት እስኪደርስ ድረስ ማንኛውም ቁጠባ የማሰባሰብም ሆነ ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች በሞግዚቶች አማካኝነት የሚከናወን ይሆናል፡፡

3.በሞግዚት አማካኝነት አባል በሚሆንባቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ አባልነቱ የተለየ ጥቅም አያስገኝም፡፡

4. በኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ በአባልነት የሚመዘገበው የሞግዚቱ ስም ሳይሆን አካለ መጠን ያልደረሰ ወጣት ስም ይሆናል፡፡

5.በአባሉ ስም የሚደረጉት ማናቸውም ውሎችም ሆነ ተግባራት በተመለከተ በአገሪቱ ስለ ሞግዚት አስተዳደር በተቀመጠው ሕግና አሰራር መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

6.እድሜያቸው ከ18 አመት በታች የሆነ እና በሞግዚቱ አማካኝነት የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል የሆነ ማንኛውም ወጣት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሕግና አሰራር በሚፈቅደው መሰረት ሙሉ አባልነቱን ከሞግዚታቸው ላይ በመረከብ በፈቃደኝነታቸው ላይ በመመስረት የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ሆነው ሊቀጥሉ ይችላሉ፡፡

7.ስለ ሞግዚት አባልነት ጉዳይ በጠቅላላ ጉባኤ በፀደቀ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪ ደንቡ ውስጥ መካተት ይኖርበታል፡፡

## 11. <u>በኅብረት ሥራ ማህበር የክብር አባልነት</u>

1) በማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1223/2012 አንቀጽ 12 እና 13 መሰረት በማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማጠናከርና ለመደገፍ ሲባል መንግስትም ሆነ ሌሎች አካላት ያለምንም ድምፅ ሙያዊ የቴክኒክ የምክር አገልግሎት ለመስጠት፣ በፋይናንስ እና በሌሎች ጉዳዮች የኅብረት ሥራ ማህበሩን ለመደገፍ እንዲቻል የክብር አባል በመሆን ሊደራጁ ይችላሉ፡፡
2) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክብር አባልነት የሚያስገኝላቸው የትርፍ ወይም የወለድ ጥቅም አይኖርም፡፡ ሆኖም የክብር አባል ሆነው በማገዛቸው ምክንያት የኅብረት ሥራ ማህበሩ እውቅና ሊሰጣቸው ይችላል፡፡
3) የክብር አባል የነበሩት አባላት ከአባልነታቸው ሲለቁ ለአባልነት የከፈሉትን የእጣ መጠን ሙሉውን ወይም ከፊሉን ለኅብረት ሥራ ማህበሩ መተው ይችላሉ፡፡ በዚህ መሰረት የሚቀርብ ማንኛውም ገንዘብ በማይከፋፈል የጋራ ንበረት ውስጥ በስጦታ አርዕስት የሚመዘገብ ይሆናል፡፡
4) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ተባባሪ አባልነታቸውን ሲያቋርጡ የከፈሉትን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል መውሰድ ይችላሉ፡፡
5) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚያቋርጥ ማንኛውም ተባባሪ አባል ገንዘቡን መውሰድ የሚችለው ከኅብረት ሥራ ማህበሩን አደጋ ላይ በማይጥል ሆኖ በሚያደርጉት ስምምነት መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡
6) ስለ ክብር አባልነት በተመለከተ በመተዳሪያ ደንባቸው ውስጥ ማከካተት ይኖርበታል፡፡

## 12. <u>ኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ የመደራጀት ጥያቄ አቀራረብ</u>

1) በኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉንም የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚወክል ሊግ በአገር አቀፍ ደረጃ ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡
2) በኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ ለመደራጀት አግባብ ላለው ባለሥልጣን ጥያቄ የሚያቀርቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጥያቄ አቀራረብ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ) በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ የፀደቀና በማህተም የተረጋገጠ የእንደራጅ ውሳኔ ቃለ-ጉባኤ፣

ለ) የመደራጀት ጥያቄ ማመልከቻ፣

ለ) አመልካች ኅብረት ሥራ ማህበራት በተወካያቸው አማካኝነት ጥያቄ ያቀርባሉ፣

ሐ) የቀረበውን በሊግ የመደራጀት ጥያቄ በማመልከቻው መሠረት አግባብ ያለው ባለስልጣን የሚያስተናግድ ይሆናል፡፡

መ) በሂደት ከምስረታው በኋላ የሚደራጁ ሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት በሊጉ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ግዴታቸውን በመወጣት በአባልነት ሊታቀፉ ይችላሉ፡፡

## 13. መስራች ኮሚቴ ስለማቋቋም

1) የምስረታ ሥራውን ለማቀላጠፍ ሲባል ከ5-7 አባላት ያሉት የመስራች ኮሚቴ ይቋቋማል፣
2) ከ3-5 የሚሆኑ የመስራች ኮሚቴ አባላት ከመስራች አባለት መካከል በቀጥታ የሚመረጡ ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ከሚመረጡት የመሥራች ኮሚቴ አባላት ውስጥ ከ2-3 የሚሆኑ ሴቶች እና ወጣቶችን በመሥራች ኮሚቴ አባልነት የሚያካትት ይሆናል፡፡
3) ቀሪዎቹ 2 የመስራች ኮሚቴ አባላት ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካል እና አግባብ ካላው ባለስልጣን የሚወከሉ ይሆናል፡፡
4) የሚመረጠው የመስራች ኮሚቴ አባላት ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ ፀሓፊ እና ሌሎች አባላት ይኖሩታል፡፡
5) የመስራች ኮሚቴ አባላትም በኅብረት ሥራ ማህበር መቋቋም ላይ ተነሳሽነት ያላቸው፣ ውሳኔ የመሠጠት ብቃት ያላቸው እና በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሆኖ የኮሚቴው ሰብሳቢ በተቋቋመው የመሥራች ኮሚቴ አባላት መካካል የሚመረጥ ወይም የሚወከል ይሆናል፡፡
6) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የሚቋቋመው የመስራች ኮሚቴ ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በላይ ላሉ አደረጃጀቶች በተመሳሳይ መልኩ የሚቋቋም መስራች ኮሚቴ አባላት ይኖሩታል፡፡
7) ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በላይ ላሉ አደረጃጀቶች የሁሉም መስራች ኅብረት ሥራ ማህበራት የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት ወይም ተወካዮች ያሉበት መስራች ኮሚቴ አባላት ይኖሩታል፡፡
8) መስራች ኮሚቴው ለሚያከናውነው ወጪ የመሥራች አባላት በሚያዋጡት ገንዘብ የሚሸፈን ሆኖ ከምስረታ በኋላ ለህብረት ሥራ ማህበሩ በሚቀርብ መረጃና ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ይተካላቸዋል፡፡
9) ለመስራች ኮሚቴዎች ተግባራት ማከናወኛ በአካባቢው ከተለያዩ አካላት ጋር በመሆን ጊዜያዊ የመሥሪያ ቦታ ሊያመቻቹ ይችላል፡፡

## 14. የመስራች ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ኅብረት ሥራ ማህበራትን ለመመስረት የተቋቋመው መስራች ኮሚቴ የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

1) የአባላት አባልነት ጥያቄያቸው መሠረት አባላትና የአባላትን መረጃ ያረጋግጣል፣
2) አባል ለመሆን ጥያቄ ላቀረቡ እና ለሌሎች ግለሰቦች ወይም ኅብረት ሥራ ማህበራት መረጃ ይሰጣል፣ ግንዛቤ ይፈጥራል፣
3) አባል ለመሆን ፍላጎት ያላቸውንና ፈቃደኛ የሆኑትን ግለሰቦች ወይም ኅብረት ሥራ ማህበራት ይመዘግባል፣
4) የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ጥናት ያካሂዳል፣
5) ከ3-5 ዓመት ኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚመራበት የንግድ ሥራ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፣
6) አግባብ ያለው ባለስልጣን ባዘጋጀው ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፣

7) አባል ለመሆን የተመዘገቡ ግለሰቦችን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት የስራ አመራር ኮሚቴ ወይም ተወካዮችን ለምስረታ ጉባኤ ስብሰባ ይጠራል፤

8) በምስረታ ጉባኤው ላይ ከተገኙት መካከል የስራ አመራር ኮሚቴ፣ የቁጥጥር ኮሚቴ እና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎችን ለመምረጥ ሶስት አባላትን የያዘ አስመራጭ ኮሚቴ ያስመርጣል፤

9) የአዋጭነት ጥናት መነሻ በማድረግ የመመዝገቢያ እና የዕጣ መጠንና ዋጋ በጉባኤ ያፀድቃል፣

10) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ስምና አድራሻ መነሻ በማቅረብ በጉባኤው እንዲሰየም በማድረግ ያፀድቃል፣

11) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ገንዘብ የሚቀመጥበት የሂሳብ አካውንት የሚከፈትበትን ባንክ ያስወስናል፣

12) በእጁ የሚገኙትን የአዋጭነት ጥናት፣ የንግድ ሥራ ዕቅድ፣ በጠቅላላ ጉባዔ የፀደቀ መተዳዳሪያ ደንብ፣ ቃለ-ጉባዔ እና ሌሎች ሰነዶች ለተመረጡ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የስራ አመራር ኮሚቴ/ቦርድ ያስረክባል፣

13) ለምስረታው የሚውል ፈንድ የማፈላለግ ሥራ ያከናውናል፣

14) የኅብረት ሥራ ሊግ አገራዊ ጉባዔ ለማካሄድ ቅደመ ዝግጅት ያደርጋሉ፣

15) በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚደራጀው የኅብረት ሥራ ሊግ በአገሪቱ ለሚገኙ ሁሉም ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባልነት ጥሪ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን እንዲደርሳቸው ያደርጋል፣

## 15. የምስረታ ጉባኤ ማካሄድ አባላትን ስለመጥራት

1) አግባብ ያለው ባለስልጣን በዚህ አንቀጽአንቀፅ 13 እና 14 በተደነገገው መሠረት መስራች ኮሚቴ የቅድመ ዝግጅት ስራውን እንዳጠናቀቀ በአምስት የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ በአባልነት የተመዘገቡት ግለሰቦች ወይም ተወካዮች በተገኙበት የምስረታ ጉባኤ ስብሰባ መጥራት አለበት፡፡

2) በመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የመደራጀት ጥያቄ ያቀረቡ ግለሰቦች ቢያንስ 2/3ኛ የሚሆኑት በሚካሄደው የመስራች አባላት ስብሰባ ላይ መገኘት አለባቸው፡፡

3) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ለመመስረት ለአባልነት ጥያቄ ያቀረቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተወካዮች ቢያንስ 2/3ኛው በሚካሄደው የመስራች አባላት ስብሰባ ላይ መገኘት አለባቸው፡፡

4) በመሥራች ስብሰባው ላይ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በቃለ-ጉባዔ በአግባቡ መያዝ አለበት፡፡

5) በመስራች ሰብሰባው ላይ አግባብ ያለው ባለስልጣን ተወካይ ሊገኝ ይገባል፡፡

## 16. በመስራች ጉባኤ ላይ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች

1) በምሥረታ ጉባዔ ላይ ቀርበው የሚወሰኑና የሚጸድቁ ጉዳዮች የሚከተሉትን ያካትታል፤

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓይነት

ለ) አዋጭነት ጥናት፣

ሐ) የንግድ ሥራ ዕቅድ፣

መ) የመተዳደሪያ ደንብ፣

ሠ) ስራውን የሚያከናውንበት ክልል ወይም ቦታ ወሰንና መግለጫ፣

ረ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ስም ስያሜ እና አርማ፣

ሰ) የስራ አመራር ኮሚቴ፣ የቁጥጥር ኮሚቴ እና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎችን ምርጫ፣

ሸ) መመዝገቢያ የገንዘብ መጠን ማስወሰን፣

ቀ) የዕጣ ካፒታል ለሽያጭ የተወሰነ የዕጣ ብዛት፣ የአንድ ዕጣ ዋጋ፣ የተሸጠ ዕጣ መጠን፣ ቃል የተገባ ዕጣ ብዛት እና ዕጣው ተሸጦ የሚያልቅበት ጊዜ ማስወሰን፣

በ) ከሌላ ምንጭ የተገኘ የካፒታል መጠን፣

2) የምስረታ ጉባኤ ጥሪ ለሁሉም ሊደርስ በሚያስችል የማስታወቂያ መንገዶችን በመጠቀም እንዲተላለፍ መደረግ አለበት፡፡

3) በጉባኤው ላይ የሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት እንዲገኙ ሊደረግ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን በሚተላለፈው ውሳኔ ላይ ድምፅ መስጠት አይችሉም፡፡

4) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ (3) በተጠቀሰው መሰረት በጉባኤው ላይ የሚተላለፉ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሚመለከቱ ውሳኔዎችን በቅደም ተከተላቸው በቃለ-ጉባዔ በአግባቡ መያዝ አለበት፡፡

5) በመስራች ጉባዔ ላይ አግባብ ያለው ባለስልጣን በአካል በጉባዔው ላይ ተገኝቶ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## 17. የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር አደረጃጀት

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በኅብረት ሥራ ማህበር መደራጀት ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 17 ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ዜግነታቸው ከኢትዮጵያ ውጭ የሆኑ ሰዎች በውክልና ሊደራጁ አይችልም፡፡

3) የመስራች አባላት ያቀረቡትን ማመልከቻ የተቀበለው ባለስልጣን በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ የመስራች አባላት ስበሰባ ይጠራል፡፡

4) የመስራች ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት በተመለከተ በዚህ አንቀጽአንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (1-15) መሰረት ይሆናል፡፡

5) የመስራች ኮሚቴ አባላት የተሰጣቸውን ተግባርና ሃላፊነት ካከናወኑ በኋላ በኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዲመዘገብላቸው ጥያቄውን በጽሁፍ አግባብ ላለው ባለስልጣን ማቅረብ ኖርባቸዋል፣

6) የኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዲመዘገብ ማመልከቻውን የተቀበለው አግባብ ለው ባለስልጣንም ጥያቄቸውን በ5 ቀን ውስጥ መርምሮ መመዝገብ ይኖርበታል፣

7) አግባብ ያለው ባለስልጣን በ5 ቀን ውስጥ መርምሮ ያልተመዘገቡበትን ምክንያት ዘርዝሮ ጥያቄ ላቀረቡት መልስ መስጠት አለበት፣

8) በ5 ቀናት ጊዜ ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበር ሆኖ ያልተመዘገበ መሆኑ በጽሁፍ ካልተገለፀ የኅብረት ሥራ ማህበሩ እንደተመዘገበ ተቆጥሮ መተዳደሪያ ደንቡ እና የሥራ እቅዱ ላይ ያስፈራቸውን ስራዎች መስራት ይችላል፡፡

9) አግባብ ያለው ባለስልጣን የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጥያቄ በጽሑፍ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚመዘገብበት ጊዜ ድረስ ተገቢውን የሙያ ድጋፍ መስጠት አለበት፣

10) ተመሳሳይ ተግባራትን የሚያከናውኑ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በአንድ የሥራ ክልል መቋቋም አይችሉም፡፡ ሆነውም ከተገኙ በጥናት ላይ በመመስረት ማዋኸድ ይኖርበታል፡፡

11) በመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ ሙሉ የስራ ሰዓት የሚሰራ ማንኛውም ሰራተኛ ምርት በማምረት አባላት በቀጥታ በሚሳተፉባቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ መደራጀት አይችልም፡፡

12) የኅብረት ሥራ ማህበር አባላት በጋራ ሆነው ምርት በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት በቀጥታ በሚሳተፉባቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ የተደራጀ ማንኛውም አባል በምትኩ ሌላ ሰው ቀጥሮ ማሰራት አይችልም፡፡

13) በአንድ የቤተሰብ አባላትን ብቻ በአባልነት በመያዝ የኅብረት ሥራ ማህበር መደራጀት አይቻልም፡፡

14) ሴቶች ወይም ወጣቶች ወይም አካል ጉዳተኞች ከሚሰሩት ልዩ የሥራ ባህሪ በመነሳት ችግሮቻቸውን ለመፍታት በማህበራዊና የኢኮኖሚ አዋጭነት ጥናት መሠረት በማድረግ በተለያዩ የስራ ዘርፎች በፍላጎታቸው ለብቻቸው ሊደራጁ ይችላል፡፡

15) የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የቅጥር ሠራተኛ የሆነ ማንኛውም ሰው የሚጠበቅበትን የአባልነት ግዴታ በመወጣት በተቀጠረበት የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ውስጥ አባል መሆን ይችላል፡፡ ሆኖም በማንኛውም የኮሚቴ አባልነት መመረጥ አይችልም፤ በኮሚቴ አባልነት ከተመረጠ ሠራተኛነቱን ይለቃል፡፡

16) ማንኛውም የቅጥር ሠራተኛ በአካል ሊሳተፍ በማይችልባቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ አባል መሆን አይችልም፡፡

## 18. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አደረጃጀት፣</u>

1) በኅብረት ሥራ ማህበራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 14 የተደነገገው እንተጠበቀ ሆኖ ተመሳሳይ ተግባርና ዓላማ ያላቸው ከሁለት በላይ የሆኑ የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱን በማረጋገጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ማደራጀት ይችላሉ፡፡

2) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ለማደራጀት የሚከተሉት ማሟላት አለባቸው፤

ሀ) በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ የፀደቀ የመደራጀት የፍላጎት ጥያቄ መቅረብ አለበት፣

ለ) ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁ መሆን ይገባቸዋል፣

ሐ) ቢዝነሳቸውን ለማላቅ ወይም ከፍተኛ ካፒታል የሚጠይቁ ዘመናዊ ኢንቨስትመንት ዓላማ ለማሳካት ስለመቻላቸው በአዋጭነት ጥናት ማረጋገጥ አለበት፣

መ) በጥናት የተለዩ ከመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት አቅም በላይ የሆኑ ችግሮች መኖራቸውን መረጋገጥ አለበት፣

መ) መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት እያንዳንዳቸው ከጠቅላላ ካፒታላቸው 25 በመቶ ያህል ዕጣ ለመግዛት ፈቃደኛ መሆን አለባቸው፡፡

ሠ) ተመሣሣይ ዓላማና ተግባር ያላቸው መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት መሆን አለባቸው፣

ረ) በኅብረት ሥራ አዋጅ የተደራጁ እና አግባብ ባለው ባለሥልጣን ተመዘገበው ሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኙ መሆን አለባቸው፣

ሰ) በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን አባል የሚሆን ኅብረት ሥራ ማህበር ከተመሠረተ ሦስት ዓመት የሞላው መሆን አለበት፡፡

ሸ) የኅብረት ሥራ አዋጅ፣ ደንብና በዚህ አንቀጽአባልነትን አስመልክቶ የወጣውን ድንጋጌ የሚያሟላ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ከሆነ በአባልነት ሊታቀፍ ይችላሉ፡፡

3) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 16 በንዑስ አንቀፅ 2 (ከሀ-ሸ) በተደነገገው መሠረት በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ለመደራጀት የፍላጎት ጥያቄ ሲቀርብለት አግባብ ያለው ባለስልጣን ከምስረታው አስቀድሞ የአዋጪነት ጥናት በማካሄድ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

4) ተመሳሳይ ዓላማና ተግባር የሚያከናውኑ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን መደራጀት ይችላሉ፡፡

5) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ለመመስረት ፈቃደኛ የሆኑ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ መፅደቅ አለበት፡፡ የጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔም በቃለ-ጉበኤ ዩኒዬኑ ለምዝገባ በሚቀርብበት ወቅት አግባብ ላለው ባለስልጣን መቅረብ አለበት፣

6) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ፈቃደኛ የሆኑ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት የጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ካሳለፉ በኃላ በጋራ አግባብ ላለው ባለስልጣን የመደራጀት ጥያቄያቸውን በጽሑፍ ያቀርባሉ፣

7) የመደራጀት ጥያቄው በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ አግባብ ያለው ባለስልጣን የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላትን በመጥራት ስለሚመሰረተው ዩኒዬን ቅድመ ዝግጂት የሚያደርጉ ከ3-7 አባላትን የያዘ መስራች ኮሚቴ ያስመርጣል፡፡ የኮሚቴ አባላት አመራረጥ በዚህ አንቀጽአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 መሰረት ይሆናል፡፡

8) የተመረጠው መስራች ኮሚቴም አግባብ ካለው ባለስልጣን ጋር በመሆን የዩኒዬኑን ቅድመ ምስረታ ተግባራትን ካጠናቀቀ በኃላ የዩኒዬኑን መስራች ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራል፣

9) በመስራች ጉባኤውም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አመራር ቦርድና ሌሎች የኮሚቴ አባላት ይመረጣሉ፤ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኑ እቅድ፣ መተዳደሪያ ደንብ ፀድቆ የማህበሩ ምስረታ እውን ይሆናል፡፡

10) በተመሰረተው ዩኒዬን የሥራ አመራር ቦርድ አማካኝነት የምዝገባ ጥያቄ አግባብ ላለው ባለስልጣን ይቀርባል፡፡

11) ዩኒዬኑ ከተመሰረተ በኃላ ከዩኒዬኑ ጋር ተመሳሳይ ፍላጎት ያለውና የዩኒዬኑን ዓላማ የተቀበለ ሌላ ኅብረት ሥራ ማህበር አባል መሆን ይችላል፣

12) በአንድ የሥራ ክልል ተመሳሳይ አላማና ተግባር ላይ የተሰማሩ ከአንድ በላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ማቋቋም አይቻልም፡፡

## 19. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን አደረጃጀት</u>

1) በኅብረት ሥራ ማህበራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 15 የተደነገገው እንተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ተመሳሳይ ተግባርና ዓላማ ባላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች ይደራጃል፡፡

2) የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ለማደራጀት ፍላጎት ያላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፤

ሀ) በጠቅላላ ጉባኤዎቻቸው ልዩ ውሳኔ የፀደቀ የመደራጀት የፍላጎት ማመልከቻ ጥያቄ፣

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች እያንዳንዳቸው ከጠቅላላ ካፒታላቸው 30 በመቶ ያህል ዕጣ ለመግዛት ፈቃደኛ መሆናቸውን የሚገልፅ ደብዳቤ፣

ሐ) ተመሣሣይ ዓላማና ተግባር ላይ የተሰመሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች ስለመሆናቸው የሚገልፅ ከመዘገባቸው አካል የድጋፍ ደብዳቤ፣

መ) በኅብረት ሥራ አዋጅ የተደራጁ እና አግባብ ባለው ባለሥልጣን ተመዘገበው ሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኙ፣

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከተመሠረተ ሦስት ዓመት የሞላው፣

ረ) በብቃት ደረጃ ማረጋገጫ እና ዕውቅና አሰጣጥ መመዘኛ መስፈርት ተመዝኖ መካከለኛ እና ከዚያ በላይ ደረጃ ያገኙ፣

ሰ) የኀብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ፣ ደንብና በዚህ አንቀጽአባልነትን አስመልክቶ የወጣውን ድንጋጌ የሚያሟላ ከሆነ፣

ሰ) የፌዴሬሽኑ አባል በሆነ ዩኒዬን አባል ያልሆነ ተመሳሳይ ዓላማና ተግባር ላይ የተሰማሩ መሰረታዊ ኀብረት ሥራ ማህበር፣

3) የኀብረት ሥራ ፌዴሬሽን ለመመስረት ፈቃደኛ የሆኑ ዩኒዬኖችና መሰረታዊ ኀብረት ሥራ ማህበራት ፈቃደኝነታቸው በቅድሚያ በጠቅላላ ጉባኤዎቻቸው ልዩ ውሳኔ የፀደቀ የመደራጀት የፍላጎት ጥያቄ አግባብ ላለው ባለስልጣን መቅረብ አለበት፣

4) የኀብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ለማደራጀት የፍላጎት ጥያቄ ሲቀርብለት አግባብ ላለው ባለስልጣን ከምስረታው አስቀድሞ ከኀብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አቅም በላይ የሆኑ ችግሮች መኖራቸውን እና አዋጭነቱን ጥናት መረጋገጥ አለበት፣

5) አግባብ ያለው ባለስልጣን የመደራጀት ጥያቄ በደረሰው በ5 ቀናት ጊዜ ውስጥ የመስራች ኀብረት ሥራ ማህበራትን የሥራ አመራር ቦርድ በመጥረት ስለሚመሰረተው ፌዴሬሽን ቅድመ ዝግጁት የሚያደርጉ ከ3-7 የሚደርሱ አባላትን የያዘ የመስራች ኮሚቴ ያስመርጣል፡፡

6) ከኀብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች አቅም በላይ የሆኑ ተግባራት መኖራቸውን በጥናት ሲያረጋግጥ አግባብ ላለው ባለስልጣን በፍላጎት ላይ ተመስርቶ የኀብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን እንዲደራጅ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የአደረጃጀት ሂደትም በኀብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አመሰራረት አንቀጽ 18 መሰረት ይሆናል፣

7) አግባብ ያለው ባለስልጣን የማህበራዊ እና የኢኮኖሚ አዋጭነታቸውን መሰረት በማድረግ በክልልም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ ሊያደራጃቸው ይችላል፡፡ ሆኖም በክልል ደረጃም ሆነ በፌዴራል ደረጃ የሚደራጁት የኀብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖች ከየኀብረት ሥራ ማህበሩ አይነት ከአንድ በላይ ማደራጀት አይቻልም፡፡

8) ተመሳሳይ ተግባራ ላይ የተሰማሩ ከአንድ በላይ ፌዴሬሽን በክልል ወይም በፌዴራል ደረጃ ሊደራጁ አይችሉም፡፡ ሆኖም የሚደራጁት የኀብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖች እንደየኀብረት ሥራ ማህበሩ ዓይነት አንድ ብቻ ይሆናል፡፡

9) በአካባቢያቸው ባለው ሀብት፣ በተሰማሩበት የስራ መስክና ዓላማ አንፃር ባላቸው ልዩ ባህሪ ምክንያት በክልል ደረጃ የተደራጁ ወይም በኀብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አባል መሆን ያልቻሉ መሠረታዊ ኀብረት ሥራ ማህበራት በፌዴራል አልያም በክልል ደረጃ በተቋቋመው የኀብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን የአባልነት ግዴታዎችን በማሟላት አባል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 20. የኀብረት ሥራ ማህበራት ተግባርና ሃላፊነት

1) ማንኛውም የኀብረት ሥራ ማህበር በየሦስት ወሩና በአመት አጠቃላይ የሥራ ሪፖርት አግባብ ላለው ባለስልጣን ያቀርባል፡፡ የሪፖርቱ ይዘትና ቅፅ አግባብ ባለው ባለስልጣን በሚዘጋጀው መሠረት ይሆናል፡፡

2) ማንኛውም የኀብረት ሥራ ማህበር ዓማታዊ የሥራ ዕቅዱን በጠቅላላ ጉባኤ ካፀደቀ በኃላ አግባብ ላለው ባለስልጣን መላክ አለበት፣

3) ማንኛውም የኀብረት ሥራ ማህበር አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ ከማድረጉ ከ15 ቀናት በፊት በጽሁፍ አግባብ ላለው ባለስልጣን ማሳወቅ አለበት፡፡

4) ማንኛውም የኀብረት ሥራ ማህበር በሰልጣን ላይ ያሉ የሥራ አመራር ኮሚቴ (ቦርድ) አባላት በተለያዩ ምክንያቶች ከሥራ ቢወገዱ ወይም ቢያቋርጡ ከተወገዱበት ቀን አንስቶ በ5 ቀናት ውስጥ ለመዝጋቢው አካል በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

5) ማንኛውም የኀብረት ሥራ ማህበር አዲስ የሥራ አመራር ኮሚቴ (ቦርድ) በተመረጠ በ3 ቀናት ጊዜ ውስጥ አግባብ ላለው ባለስልጣን መመረጣቸውን ማሳወቅ አለበት፡፡

6) ሕጋዊ ሰውነት ያገኛ ማንኛውም የኀብረት ሥራ ማህበር የራሱ የሆነ አድራሻና የሥራ ክልል ይኖረዋል፡፡

7) የኀብረት ሥራ ማህበሩ ቋሚ አድራሻውን ሲለውጥ ከ30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አግባብ ላለው ባለስልጣን ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ሌሎችም እንዲያውቁት በሚዲያ ማሳወቅ አለበት፡፤

8) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ሂሳቡን በውጪ ኦዲተር ለማስመርመር ሲፈልግ አስቀድሞ አግባብ ያለውን ባለስልጣን ማስፈቀድ አለበት፣

9) የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ምርት በማሰባሰብ የተሻለ ገበያና ዋጋ እንዲያገኝ ማድረግ ይኖርበታል፣

10) የአባላትን ምርት በማሰባሰብ ወደተለያዩ ምርቶች በመለወጥ (እሴት በመጨመር) ደረጃቸውን ጠብቀውና ታሽገው በገበያ በማቅረብ ተጨማሪ ዋጋ እንዲያገኙ ማድረግ፣

11) የአባላት ምርት በጥሬ እቃነት የሚጠቀሙ የተለያዩ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም ለምርታቸው ተጨማሪ የገበያ ሁኔታ መፍጠር፣

12) የተለያዩ ዘመናዊ ግብዓቶችን በተገቢው ጊዜ፣ መጠን እንዲሁም ቦታ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ በአባላት ላይ የሚደርሰውን ተጨማሪ ወጪ ማስቀረት፣

13) የአባላትን ምርትና ምርታማነት የሚያሳድጉ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ከተለያዩ ተቋማት በማፈላለግ አባላት እንዲጠቀሙባቸው ማስተዋወቅና ማቅረብ፣

14) ለሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪና የውጪ ገበያ የሚሆን ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ ምርት እንዲያመርቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣

15) አባላት ለማምረት የሚፈልጉትን የተለያዩ ግብዓቶች ገዝተው መጠቀም እንዲችሉ ከተለያዩ የገንዘብ ተቋማት ጋር በመደራደርና ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ካፒታል ብድር መስጠት፣

16) አባላት ከምርታቸው ከማያገኙት ገቢ በአግባቡ ሊጠቀሙ የማያስችላቸውን የቁጠባ ባህል ማሳደግና የቁጠባ አገልግሎት መስጠት፣

17) ለአባላት ምርትና ምርታማት ማደግ ወሳኝ የሆኑ ርዕሶች ላይ ጥናትና ምርምር ማድረግና ስልጠና መስጠት፣

18) የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የኤክስቴሽን አገልግሎት በቀጣይነት ተደራሽ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግና ብክነትን በመቀነስ ውጤታማ እንዲሆኑ መማድረግ፣

19) ኅብረት ሥራ ማህበራት በአከባቢ የተ ፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እና እንክብካቤ ላይ የመሳተፍ፣

20) የኅብረት ሥራ ማህበራት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረት አወጋገድ ጉዳይ ትኩረት ሊያገኝ ይገባል

21) ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎች የኅብረት ሥራ ማህበራትን ገንዘብ ስለሚይዝ፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ስላለው እና ምቹ የስራ ቦታን ለመፍጠር እንዲቻል አገልግሎት የማይሰጡ ንብረት አወጋገድ ጉዳይ በትኩረት ይሰራሉ፣

22) ኅብረት ሥራ ማህበራት እንደየ ሀብት መጠናቸው እና የስራ ባህርያቸው መሰረት መክፈል ያለባቸውን ግብር ወቅቱን ጠብቆ መክፈል አለባቸው፣

23) ሌሎች ተግባራት በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪ ደንብ ላይ በሚደነገገው መሰረት ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች፣ አዋጭነት ጥናት፣ የንግድ ሥራ ዕቅድ እና የመተዳደሪያ ደንብ፤

### 21. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች፤

1) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የምርት ወይም የአገልግሎት መስጠት ወይም የምርትና የአገልግሎት መስጠት ተግባራትን አጣምሮ የሚያከናውን ሆኖ ሊደራጅ ይችላል፡፡

2) በግብርና ነክ በማምረት ተግባራት ላይ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች የእንሰሳትና የእንሰሳት ተዋፅኦ፣ የሰብል እና የደን ውጤቶች የሚያካትት ይሆናል፤

3) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ የእንሰሳትና የእንሰሳት ተዋፅኦ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ) የእንሰሳት እርባታ ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ለ) የእንሰሳት ማደለብ ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሐ) የወተት እና የወተት ተዋጽኦ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

መ) የአሣ አስጋሪዎች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሠ) የንብ አናቢዎች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ረ) የዶሮ እርባታ ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሰ) የእንሰሳት መኖ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሸ) የዝባድ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

4) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሰብል እና የደን ውጤቶች ኅብረት ሥራ ማህበር ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ) የሰብል አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ለ) የዘር ብዜት አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሐ) የቡና አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

መ)የሸንኮራ አገዳ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሠ) የአትክልት እና ፍራፍሬ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ረ) የቅመማ ቅመም አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሰ) የዕጣን እና የዱር ሙጫ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሸ) የደን እና የደን ውጤቶች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ቀ) የመስኖ ልማት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

5) በአነስተኛና በመካከለኛ ደረጃ በሚደራጁ የግንባታ እና ኮንስትራክሽን ጥሬ ዕቃዎች እና ውጤቶች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ) የባህላዊ ማዕድን አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ለ) የግንባታና ኮንስትራክሽን ዕቃዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

6) በአነስተኛና በመካከለኛ ደረጃ የሚደራጁ የኢንዱስትሪ እና የዕደ ጥበብ ውጤቶች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ) የሸመና ውጤቶች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ለ) የቤት እና የቢሮ ዕቃዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሐ) የሸክላና የሸክላ ውጤቶች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

መ) ሣሙናና የፅዳት ዕቃዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሠ) የጌጣጌጥ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማህበር፣

7) በአገልግሎት መስጠት ተግባር ላይ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች የሸማቾች፣ የገንዘብ ቁጠባና ብድር፣ የመኖሪያ ቤቶች፣ የጽዳትና ውበት፣ የባልትና ባልትና ውጤቶች፣ የምግብ ዝግጅት፣ የገጠር ኤሌክትሪክ፣ የትራንስፖርት እና የልዩ ሙያ አገልግሎት ዓይነቶችን የሚያካትት ይሆናል፤

8) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 7 እንደተጠበቀ ሆኖ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ) ተቋሚን መሰረት አድርገው የሚደራጁ የሸማቾች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ለ) አከባቢን መሰራት አድርገው የሚደራጁ የሸማቾች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

9) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 7 እንደተጠበቀ ሆኖ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ) ተቋሚን መሰረት አድርገው የሚደራጁ የገንዘብ ቁጠባና ብድር አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ለ) አከባቢን መሰራት አድርገው የሚደራጁ የገንዘብ ቁጠባና ብድር አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

10) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 7 እንደተጠበቀ ሆኖ የመኖሪያ ቤቶች ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ) የሠራተኞች የመኖሪያ ቤቶች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ለ) የከተማ ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤቶች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሐ) የገጠር ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤቶች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

11) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 7 እንደተጠበቀ ሆኖ የጽዳትና ውበት ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ) የቆሻሻ ማንሳት አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ለ) የመኪና ዕጥበት አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሐ) የአልባሳት ዕጥበት አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

መ) የቤቶችና ግቢ ጽዳት አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሠ) የውበት ሣሎን አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

12) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊደራጅ ይችላል፡-

ሀ) የግብርናና የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃን የሚያቀናብር የባልትና እና የባልትና ውጤቶች አግልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ለ) የምግብ ዝግጅት አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሐ) የገጠር ኤሌክትሪክ አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

መ) የትራንስፖርት አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

13) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የልዩ ሙያ አገልግሎት ሰጪ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ) የጤና ሙያ አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ለ) የሂሳብ አዋቂዎች አገልግሎት ኅብረት ስራ ማህበር፣

ሐ) የትምህርትና ሥልጠና ባለሙያዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

መ) የኤሌክትሪክ ጥገና ባለሙያዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሠ) የውሃ ቧንቧ ሥራ ባለሙያዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ረ) የማማከር አገልግሎት የኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሰ) የምህንድስና ሙያ አገልግሎት የኅብረት ስራ ማህበር፣

ሸ) የግንበኞች እና አናጺዎች አገልግሎት ኅብረት ስራ ማህበር፣

ቀ)የህግ ሙያ አገልግሎት የኅብረት ስራ ማህበር፣

14) በማምረትና አገልግሎት መስጠት ተግባር ላይ የሚደራጁ ሁለገብ የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚያካትት ይሆናል፡፡

15) ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚያካናውኗቸው በርካታ ተግባራት መካከል የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት ይጠቀሳሉ፡-

ሀ) የግብርና ተግባራትን፣ የቢዝነስ ተግባራትን እና ሌሎች ሥራቸውን እንዲያሳድጉ ለመደገፍ ለአባላቱ ብድር አገልግሎት እንዲያገኙ በማፈላለግ ማቅረብ፣

ለ) የተሻሻለውን የግብርና ቴክኒክ ወይም ዘዴ በማበረታታት አባለት የላቀ የግብርና ምርት እንዲያገኙ የግብርና ግብዓቶችን እና የእርሻ መሳሪዎችን ማቅርብ፣

ሐ) በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካይነት በአባላቱ በሚያመረቱት የግብርና ምርትና ሌሎች ሸቀጦች ላይ እሴት በመጨመር ግብይት ማካሄድ፣

መ) የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ከእርሻቸው ወይም ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎች፣ ተጨማሪ ንግድና አነስተኛና መካከለኛ ደረጃ ያላቸው ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም የአባላትን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በማሻሻል የኑሮ ዘይቤዎቻቸውን ማጎልበት፣

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት የቁጠባ ባህል በማሳደግ፣ ለአባላት ጤናማነት፣ ትምህርት እና መዝናናት የሚሆኑ የብድር አገልግሎት ተደራሽ በማድረግ ችግራቸውን መፍታት ይችላሉ፣

ረ) ለአባሎቻቸው የተለያዩ እቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ገዝተው ያቅርቧቸዋል፣

ሰ) በአባላት መካከል የተፈጠሩ አለመግባባቶችን በግልግል ዳኝነት እና ዳኝነት ለመፍታት ይሞክሩ፣

16) ማንኛውም በማምረት ሥራ ላይ የተሰማራ ኅብረት ሥራ ማህበር የሚያከናውናቸው ተግባራት ሁሉም አባላት በቀጥታ በጋራ ሆነው የማምረት ተግባራትን በአንድነት የሚፈፅሙ ሊሆን ይገባል፡፡

17) የኅብረት ሥራ ማህበራትን ዓይነቶችን በተመለከተ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 16 የተደነገገው እንደጠጠበቀ ሆኖ የተለየ ባህሪ ኖራቸው የሚቀርቡ የእንደራጅ ጥያቄዎችን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አስፈላጊነታቸውን በጥናት በማረጋገጥ አግባብ ያለው ባለስልጣን በልዩ ሁኔታ በሌሎች ዘርፎች የኅብረት ሥራ ሊያደራጅ ይችላል፡፡

## 22. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት የአዋጭነት ጥናት ማካሄድ</u>

1) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር አዋጭነቱ በጥናት ሳይረጋገጥ ማደራጀት አይቻልም፡፡

2) የአዋጭነት ጥናት አግባብ ባለው ባለስልጣን በሚቋቋመው የመስራች ኮሚቴ አባላት የሚጠና ይሆናል፡፡

3) በአካባቢው ኅብረት ሥራ ማህበራትን በማደራጀት ሊያስገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም፣ የህብረተሰቡን አኗኗር እና ምቹ ሁኔታዎች የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡

4) ሊደራጅ የታሰበው ኅብረት ሥራ ማህበር አዋጭነቱ በጥናት በማረጋገጥ ኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዲደራጅ ወይም እንዳይደራጅ መወሰን ይኖርበታል፡፡

5) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የሚካሄደው የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለማደራጀት የሚደረግ የአዋጭነት ጥናት የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታል፤

ሀ) የአባላትን ሁኔታ

ለ) ወደፊት አባል ስለሚሆኑ ግለሰቦች

ሐ) የአካባቢውን ሀብት

መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት

ሠ) የኢኮኖሚ አዋጭነት ሁኔታ

ረ) የአካባቢው የምርት እና የአገልግሎት ሁኔታ

ሰ) የአባላትን ምርትና አገልግሎት ሁኔታ

ሸ) የፍላጎት እና አቅርቦት ሁኔታ

ቀ) የቴክኒክ አዋጭነት

በ) የፋይናንስ አዋጭነት ትንበያ

ተ) የገበያ ሁኔታ ትንተና

6) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 2 የሚካሄደው የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየንና ፌዴሬሽን ለማደራጀት የሚደረግ የአዋጭነት ጥናት የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታል፤

ሀ) የአባላትን ሁኔታ

ለ) ወደፊት አባል ስለሚሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት

ሐ) የአካባቢውን ሀብት

መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሀብት

ሠ) ተንቀሳቃሽ፣ ቋሚ ንብረት፣ ዕዳና ካፒታል

ረ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት

ሰ) የኢኮኖሚ አዋጭነት (የገበያ ሁኔታ)

ሸ) የአካባቢው የምርት እና የአገልግሎት ሁኔታ

ቀ) የአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ምርትና አገልግሎት ሁኔታ

በ) የፍላጎት እና አቅርቦት ሁኔታ

ተ) የቴክኒክ አዋጭነት

ቸ) የፋይናንስ አዋጭነት ትንበያ

ነ) የማህበራዊ ተጽኢኖ

## 23. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት የንግድ ሥራ ዕቅድ ስለማዘጋጀት</u>

1) የኅብረት ሥራ ማህበራ የንግድ ሥራ ዕቅድ በመስራች ኮሚቴ ይዘጋጃል፡፡ ሆኖም የንግድ ሥራ ዕቅድ ሳያዘጋጅ መደራጀት አይቻልም፡፡

2) የንግድ ሥራ ዕቅድ ኅብረት ሥራ ማህበር በቀጣይ ለሚያደርገው የስራ እንቅስቃሴ እንደ ፍኖተ ካርታ ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 23 ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት የተዘጋጀው የሥራ ዕቅድ የሚከተሉትን ይዘቶች ይኖሩታል፤

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ራዕይ እና ተልዕኮ

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓላማ እና ተግባር

ሐ) የሁኔታዎች ትንተና

መ) የምርት ወይም የአገልግሎት ዕቅድ

ሠ) የገበያ ትንተና

ረ) የገበያ (የግዥ እና ሽያጭ) ዕቅድ

ሰ) የሰው ሀይል ዕቅድ

ሸ) የፋይናንስ ዕቅድ፡፡

## 24. <u>የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ</u>

1) የመስራች ኮሚቴ አግባብ ካለው ባለስልጣን በሚሰጠው መነሻ ረቂቅ ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ለሚደራጀው ኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

2) የመሥራች ኮሚቴው መተዳዳሪያ ደንብ ሲያዘጋጅ የአዋጭነት ጥናትን እንደ ግብዓት ሊጠቀም ይችላል፡፡

3) በመስራች ኮሚቴው የተዘጋጀውን ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብ ለመስራቾች ጉባዔ በማፀደቅ አዲስ ለሚመረጠው የሥራ አመራር ኮሚቴ የሚያስተላልፍ ይሆናል፡፡

4) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት የፀደቀ የመተዳደሪያ ደንብ በአባላት ላይ አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

5) የመተዳዳሪያ ደንብ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የበላይ ህግ በመሆን የተለያዩ የሥራ መመሪያዎች፣ አሰራሮች፣ አደረጃጀቶች፣ ውሰጠ ደንቦች እና አፈፃፀሞች መነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

6) የኅብረት ሥራ ማህበራት የመተዳደሪያ ደንብ የሚከተሉትን መርሆዎች ይኖሩታል፣

ሀ) ግልፅነት፣

ለ) ወጥነት፣

ሐ) ቀጣይነት/ተከታታይነት፣

መ) አካታችነት፣

ሠ) ሊተገበር የሚችል ሊሆን ይገባል፡፡

7) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጁ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 (ከሀ-ኀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ በተጨማሪነት የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ ክልል እና የቦታ መግለጫ

ለ) የአባላት መዝገብ ስለማደራጀት፣

ሐ) አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ስለሚቀበልበት፣ ስለሚመዘግብበት እና ስለየሚታገድበት ሁኔታ፣

መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ድርጅታዊ መዋቅር፣

ሠ) የጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ፣ አስቸኳይ እና ልዩ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች፣

ረ) ስለመመዝገቢያና የዕጣና የዕጣ ሰርተፍኬት አሰጣጥ

ሰ) ስለኅብረት ሥራ ማህበሩ ካፒታል ማፍራት

ሸ) የሂሳብ አያያዝና ገንዘብ አጠቃቀም፣

ቀ) የብድር እና ብድር አስተዳደር፣

በ) የክፍያና የማበረታቻ ሥርዓት፣

ተ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከሌሎች አካላት ጋር ስለሚያደርገው የቀጥታ እና የጎንዮሽ ግንኙነት፣

ቸ) የኅብረት ሥራ ማህበር የበጀት ዓመት

ነ) ኢንስፔክሽንና የብቃት ደረጃ ዕውቅና

ኘ) ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚከፈልበት ወይም የሚዋሃድበት ወይም የሚፈርስበት ሁኔታ፣

አ) በኅብረት ሥራ ማህበራት ስለሚፈጠሩ ያለመግባባቶች አፈታት፣

ወ) ስለኅብረት ሥራ ማህበራት ፈንድ መቋቋምና አስተዳደር

ዘ) ስለኅብረት ሥራ ማህበራት አማካሪ ምክር ቤት አመሰራረት፣ ተግባርና ኃላፊነት፣

ጠ) ለአባላት፣ አመራር አካላት እና ቅጥር ሠራተኞች ትምህርትና ስልጣና ስለመስጠት፣

ጨ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጠ ደንብ ይዘቶች፣

ቀ) መተዳደርያ ደንብ የጸናበት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት፣ መያዝ አለበት፡፡

8) አግባብ ባለው ባለስልጣን የተመዘገበው የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ ቅጂ ወደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ መመለስ አለበት፣

## 25. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራትን መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል</u>

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 እና በዚህ አንቀጽመሰረት የተመዘገበ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የስም ለውጥ ሲያደርግ መተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻል ይኖርበታል።

2) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉበኤ የፀደቀና ለመዝጋቢው አካል ቀርቦ እስከሚመዘገብ ድረስ ዋጋ የለውም

3) የመተዳደሪያ ደንቦቹ ማናቸውም ማሻሻያዎች ከኅብረት ሥራ ማህበራት አወጅ 985/2009 ወይም ከዚህ መመሪያ ጋር የሚስማማ ሆኖ ከተገኘ ማሻሻያውን እንዲመዘግብ የሚከለክል አለመሆኑን የመዝጋቢው ሲያረጋግጥ ሊመዘግብ ይችላል፡፡

4) መዝገቢው ባለሥልጣን ማንኛውንም የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ የማይመዘግብ ከሆነ አለመመዝገቡን በወቅቱ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሰረት ቅሬታ ያለው ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ቅሬታውን በየደረጃው ለሚገኘው ይግባኝ ሰሚ ችሎት በ 30 ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

5) በየደረጃው ያለው አግባብ ያለው ባለስልታን የኅብረት ሥራ ማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ በሚመዘግብበት ጊዜ የተረጋገጠውን ማሻሻያ ቅጅ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ መስጠት አለበት፡፡ ይህም ማሻሻያው በትክክል መመዝገቡን የሚያረጋግጥ ተጨባጭ ማስረጃ ይሆናል፡፡

6) በዚህ አንቀጽዓላማ መሰረት “ማሻሻያ” የሚለው አገላለጽ አዲስ መተዳደሪያ ደንብ ማውጣት እና መተዳደሪያ ደንቡን መተካት ወይም መሻርን ያጠቃልላል ፡፡

7) የትኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ስም፡

ሀ) ከሌላ ኅብረት ሥራ ማህበር ስም ጋር ተመሳሳይ ስም ሊኖረው አይችልም፣

ለ) መጠቀሙ በመዝጋቢው አስተያየት ግራ ሊያጋባ ወይም ሊያሳስት አይገባም፣

ሐ) በዚህ ሕግ ከተመዘገበው ሌላ የኅብረት ሥራ ማህበር ስም ጋር ተመሳሳይ መሆን ዬለበትም፣

(መ) በሕግ የተከለከለ መሆን የለበትም

ሠ) ከፖለቲካ ፓርቲ ወይም ከፖለቲካ ፓርቲ መሪ ጋር ግንኙነት መኖሩን የሚጠቁም ወይም የሚያመለክት መሆን የለበትም፣

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የኅብረት ሥራ ማህበር ስም ስያሜ እና አርማ ትርጉም፣ የሥራ ክልልና የመስሪያ ቦታ መግለጫ እና የሂሳብ አያያዝና ገንዘብ አጠቃቀም</u>

### 26. <u>የኅብረት ሥራ ማህበር ስም ስያሜ እና አርማ ትርጉም</u>

1) በዚህ የአደረጃጀት መመሪያ መሠረት የሚደራጅ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የራሱ የሆነ መጠሪያ ስም ይኖረዋል፡፡ የሚሰጠው የስም ስያሜ በአንድ የምዝገባ ክልል ውስጥ ከአንድ በላይ ስም ሊሆን አይችልም፡፡

2) በአንድ የሥራ ክልል ውስጥ አስቀድሞ የተሰጠ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ስም በስራ ክልሉ ለተደራጀ ለሌላ ኅብረት ሥራ ማህበር መጠሪያ ሆኖ ሊሰየም አይችልም፡፡

3) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 9 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ የሚወሰን አርማ፣ የአርማ ትርጓሜ እና ማህተም ይኖረዋል፡፡

4) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ስም፣ አርማና ማህተም ስራ ላይ መዋል የሚችለው ሦስተኛ ወገኖች ቅሬታ ያላቀረቡ መሆኑ በህግ ሲረጋጋጥ አግባብ ላለው ባለስልጣን ቀርቦ ሲመዘገብ ብቻ ነው፡፡

5) የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ማህተም የኅብረት ሥራ ማህበሩን ስምና አርማ የያዘ ሆኖ ማህተሙ የግርጌው ክብ እና የራስጌው አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ሊሆን ይችላል፡፡

6) በማህተሙ ላይ የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ እንደ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነትና ደረጃ የተለያየ ቢሆንም በአገር ውስጥ እና በውጭ አገራት የሚጠቀሙበትን ሊውስን ይችላል፡፡

7) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማህተሙ የላይኛው ክፍል የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሙሉ ስም በአካባቢው የሥራ ቋንቋ ሆኖ ከታች የፌደራል የሥራ ቋንቋ ያለው እና መሀሉ የኅብረት ሥራ ማህበሩን አርማ የያዘ ይሆናል፡፡

8) በሥራ ባህሪያቸው በዓለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ የሚሳተፉ ኅብረት ሥራ ማህበራት ማህተም የላይኛው ክፍል የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሙሉ ስም በአካባቢው የስራ ቋንቋ ሆኖ ከታች በእንግሊዘኛ ቋንቋ ያለው እና መሀሉ የኅብረት ሥራ ማህበሩን አርማ የያዘ ሊሆን ይችላል፡፡

9) የኅብረት ሥራ ማህበራት አርማ ግልፅ ትርጉም ያለው ሆኖ ተግባራቸውን የሚገልፅ፣ የአካባቢውን ባህል፣ ታሪክ፣ እሴትና የወደፊት ተስፋን የሚያሳይ ሆኖ መቀረፅ ይኖርበታል፡፡

10) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በሚያመርተው ምርት ወይም በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ህጋዊነቱ ለማረጋገጥ የሚያገለግል የራሱን አርማና ማህተም መጠቀም አለበት፡፡ ሆኖም የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር አርማና ማህተም ተመሳሳይና አሳሳች መሆን የለበትም፡፡

11) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር አርማና ማህተም በኅብረት ሥራ ማህበሩ ማስታወቂያዎች፣ ደብዳቤዎች፣ ሌሎች መግለጫዎችና በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም በሚፈረሙ ሰነዶች ላይ ማህተም ማረፍ አለበት፡፡

12) የኅብረት ሥራ ማህበር ስም፣ አርማ እና ማህተም መለወጥ የሚቻለው በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ሆኖ አዲስ ስም፣ አርማ እና ማህተም አግባብ ባለው ባለስልጣን ቀርቦ ሲመዘገብ ብቻ ነው፡፡

13) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር አርማ እና ማህተም ለውጥ ጥያቄ ሲያቀርብ አግባብ ያለው ባለሥልጣን አጣርቶ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ያወጣል፡፡ ጋዜጣው ከወጣበት ቀን አነሰቶ በሰላሣ ቀን ወስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ የስም ለውጡን በሁለት ተከታታይ የስራ ቀን ውስጥ ያጸድቃል፡፡

14) ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው ባለሥልጣን ፍቃድ ሳያገኝ በስም፣ በአርማ እና በማህተም ላይ "የኅብረት ሥራ ማህበር" የሚለውን ስያሜ መጠቀም አይችልም፡፡

## 27. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ ክልል</u>

1) ማንኛውም በአዲስ የሚቋቋም ወይም በመከፈል ወይም በመዋሃድ የሚደራጅ የኅብረት ሥራ ማህበር የሚኖረው የሥራ ክልል በተመዘገበበት የሥራ መስክ፣ ዓላማ እና ተግባር በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በሚወሰነው መስራት ይሆናል፡፡
2) በአንድ የሥራ ክልል ውስጥ ተመሳሳይ የሥራ መስክ፣ ዓላማ እና ተግባር ያላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት አይነቶች ሊቋቋሙ አይችልም፡፡
3) የሥራ ክልሉም አወሳሰን አባላት በሚኖሩበት ወይም በሚሠሩበት ወሰን በማካለል ሊሆን ይችላል፡፡
4) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር አባላትን ተደራሽ ለማድረግ በሥራ ክልሉ ውስጥ የተለያዩ ቅርንጫፎችን ሊከፍት ይችላል፡፡
5) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከተመዘገበበት የሥራ ክልል ውጪ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዋና ጽ/ቤት ወይም ቅርንጫፍ መክፍት አይችልም፡፡ ሆኖም ለሥራ ቅልጥፍና ሲባል የዋናው ጽ/ቤት የአገልግሎት መስጫ ቅርንጫፍ አግባብ ካለው ባለስልጣን ሲፈቀድለት ብቻ ሊከፍት ይችላል፡፡
6) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የግብይት ተግባራት ላይ የተሰማሩ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለሥራ ቅልጥፍና ሲባል ከሥራ ክልላቸው ወጪ የተለያዩ መደራሻዎች ላይ የገበያ ትስስር ማድረግ የሚያስችል የጉዳይ ማስፈፀሚያ ወይም የአግልግሎት መስጫ ጽ/ቤት ወይም ሱቅ መክፈት ይችላሉ፡፡
7) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በሥራ ክልሉ ውስጥ ሊከፍተው የአገልግሎት መስጫ ቅርንጫፍ ወይም ከሥራ ክልሉ ውጪ የጉዳይ ማስፈፀሚያ ወይም የአግልግሎት መስጫ ጽ/ቤት ወይም ሱቅ ሲከፍት፡-

   ሀ) የጠቅላላ ጉባኤ ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል፣

   ለ) በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በሚገባ መካተት ይኖርበታል፣

   ሐ) አግባብ ላለው ባለስልጣን ማሳወቅና እውቅና ሊኖረው ይገባል፣

8) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተከፍቶ የነበረውን የጉዳይ ማስፈፀሚያ ወይም የአግልግሎት መስጫ ጽ/ቤት ወይም ሱቅ ወይም ቅርንጫፍ በተለያዩ ምክንያቶች የኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዲዘጋ ወይም ለማቆም ሲወስን፤

ሀ) የጠቅላላ ጉባኤ ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል፣

ለ) የሦስተኛ ወገኖች ቅሬታ አለመኖሩን በህግ ማረጋገጥ አለበት፣

ሐ) አስራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ አግባቡ ላለው ባለስልጣን በደብዳቤ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

9) በአንድ የሥራ ክልል ውስጥ በተለያየ የሥራ መስክ፣ ዓላማና ተግባር ላይ በተደራጁ ኅብረት ሥራ ማህበር ውስጥ ማንኛውም ሰው አባል መሆን ይችላል፡፡

10) በዚህ አንቀጽመሠረት የሚመሰረት የኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ ክልል የኅብረት ሥራ ማህበሩን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ መሠረት ያደረገ ይሆናል፡፡ ዝርዝር ሁኔታው በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 28. <u>የመስሪያ ቦታ መግለጫ</u>

1) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር እንደየስራ ባህሪው መሠረት ሲደራጅ ስራውን የሚያከናውንበት በምደባ፣ በግዥ ወይም በኪራይ ወይም በስጦታ የተገኘ የመስሪያ ቦታ ይኖረዋል፡፡

2) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ያገኘውን ህጋዊ የሆነ ቦታ መግለጫ አግባብ ላለው ባለስልጣን በማቅረብ ማስመዝግብ ወይም ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

3) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የመስሪያ ቦታ የአድራሻ ለውጥ የሚያደርግ ከሆነ የተደረገውን ለውጥ የሦስተኛ ወገኖች ቅሬታ አለመኖሩን በህግ ሲረጋገጥ አስራ አምስት ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አግባቡ ላለው ባለስልጣን በደብዳቤ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 29. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ አያያዝና ገንዘብ አጠቃቀም</u>

1) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ገቢና ወጪውን በተገቢ ሰነዶች በየዕለቱ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

2) የኅብረት ሥራ ማህበራት ለከፈሉት ማንኛውም ክፍያ ማስረጃ የመቀበል ለሰበሰቡት ገቢም በወቅቱ ህጋዊ ደረሰኝ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

3) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 29 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተገለፀው እንደተጠበቀው ሆኖ እንደየህብረት ሥራ ማህበሩ ዓይነትና ደረጃ የሚከተሉትን ደረሰኞች ሊኖሩት ይገባል፤

ሀ) የገቢ ደረሰኝ፣

ለ) የወጪ ደረሰኝ፣

ሐ) የዕለት ሺያጭ ደረሰኝ፣

መ) የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ፣

ሠ) የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ፣

ረ) የደሞዝ መክፈያ ሰነድ፣

ሰ) የንብረት ገቢ መረከቢያ ደረሰኝ

ሸ) የንብረት ወጪ ማስረከቢያ ደረሰኝ

ቀ) በመተዳደሪያ ደንባቸው በሚወስኑት መሰረት ሌሎች ደረሰኞች፣

4) ገንዘብ ወጪ እንዲሆን የሚፈቅድ የኅብረት ሥራ ማህበሩ አመራር አካል ገንዘብ አይሰበስብም፣ የሂሳብ ምዝገባ ሥራም አያከናውንም፡፡

5) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ገንዘብ ያዥ በየዕለቱ የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ በጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መቆጣጠሪያ ላይ በመመዝገብ ለሂሳብ ሹም ሪፖርት ያደርጋል፡፡

6) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ በጽሁፍ ካልተወከለ በስተቀር ማንም ግለሰብ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም በገንዘብ ተቀባነት ስራ ላይ ሊሰማራ አይችልም፡፡

7) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ገቢውንም ሆነ ወጪውን የሚፈፅመው በጠቅላላ ጉባዔ በፀደቀው በጀት መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡

8) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ከተለያዩ የመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የሚያገኘውን ስጦታና ድጋፍ በመዝገብ መዝግቦ መያዝ ይኖርበታል፡፡

9) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 29 ንዑስ አንቀፅ 8 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የተበረከተው ስጦታ በጥሬ ገንዘብ ከሆነ በኅብረት ሥራ ማህበሩ የገቢ ደረስኝ ተቆርጦ በቁጠባ ሂሳብ ውስጥ ገቢ መሆን ይኖርበታል፤

10) የተበረከተው ስጦታ በዓይነት ከሆነ በገንዘብ ተተምኖ በንብረት ገቢ ደረስኝ እና በንብረት ገቢ መዝገብ መመዝገብ ይኖርበታል፤ ይህንንም የተበረከተ ስጦታ በጠቅላላ ጉባዔ አስወስኖ ማስመዝገብ አለበት፡፡

11) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ለሚያከናውናቸው ተግባርት የሚያገለግሉ የሚከተሉትን መዛግብቶች ሊኖሩት ይገባል፤

ሀ) የገቢ መዝገብ፣

ለ) የወጪ መዝገብ፣

ሐ) የሂሳብ ሌጀር መዝገብ፣

መ) የሂሳብ ማመዛዘኛ መዝገብ፣

ሠ) የጥሬ ገንዘብ መቆጣጠርያ መዝገብ፣

ረ) በመተዳደሪያ ደንባቸው በሚወስኑት መሰረት ሌሎች መዛግብቶች፣

12) የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞችም ሆኑ ሌሎች ሂሳብ ነክ ሰነዶች በጥንቃቄ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ከጠፉ በአስቸኳይ ለሚመለከተው ህጋዊ አካል ማመልከት እና በመገናኛ ዘዴዎች ጭምር ማሳወቅ አለበት፡፡

13) የኅብረት ሥራ ማህበራት የልዩ ልዩ ኮሚቴ አባላት ለኅብረት ሥራ ማህበራቸው እና ለአባላት ለሚሰጡት አገልግሎት ምንም ዓይነት ክፍያ አይከፈልም፡፡ ሆኖም ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ጉዳይ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ከአመስት ኪሎሜትር በላይ ሲሄዱ በውስጠ ደንባቸው በሚወስኑት መሠረት የውሎ አበል ይከፈላቸዋል፡፡ የትራንስፖርት ወጪም በሚያቀርቡት ህጋዊ ደረሰኝ መሠረት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

14) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳባቸውን በየዕለቱ መመዝገብ፣ በየወሩ እና በየዓመቱ በመዝጋት ለኦዲት ዝግጁ ማድረግ አለባቸው፡፡

15) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ እና በዓመት የሂሳብ ሪፖርት ለስራ አመራር ኮሚቴ እና አግባብ ላለው ባለስልጣን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህንን ተግባር የሚያከናውን ባለሙያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

16) እንደየህብረት ሥራ ማህበሩ ዓይነት ለስራዎች አጋዥ የሆኑ የሚከተሉት ልዩ ልዩ የሂሳብ ቅፆች ሊኖሩት ይችላል፡፡

ሀ) የአዲስ እና የእንደገና አባልነት ጥያቄ ማመልከቻ ቅፅ፣

ለ) የንብረት ገቢ ማድረጊያ ቅጽ፣

ሐ) የንብረት ወጪ መጠየቂያ ቅጽ፣

መ) የብድር ውል ቅጽ፣

ሠ) የተመን ቅጽ፣

ረ) የውሎ አበል መጠየቂያ እና ማወራረጃ ፣

ሰ) ሠነድ ለሌላቸው የገንዘብ መክፈያ ቅጽ

ሸ) የቅድሚያ ወጪ መጠየቅያ ቅጽ፣

ቀ) በመተዳደሪያ ደንባቸው በሚወስኑት መሰረት ሌሎች ቅፆች፣

17) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለስራዎች አጋዥ የሆኑ የሚከተሉት ልዩ ልዩ ፎርሞች ሊኖሩት ይችላል፡፡

ሀ) የንብረት ግዥ መጠየቂያ ፎርም፣

ለ) የብድር ማመልከቻ ፎርም፣

ሐ) የአዲስ አባላት ማመልከቻ ፎርም፣

መ) የእንደገና ተመላሽ አባላት ማመልከቻ ፎርም፣

ሠ) ከአባልነት አባላት ሲሰናበት የሚሟላ ፎርም፣

ረ) የወራሽ መሰየሚያ ፎርም፣

ሰ) በመተዳደሪያ ደንባቸው በሚወስኑት መሰረት ሌሎች ፎርሞች፣

## 30. <u>የሂሳብ አካውንት ስለመክፈት</u>

1) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ባለው ባለስልጣን ድጋፍ ሲያገኝ በአቅራቢያው በሚገኝ ህጋዊ እና አዋጭ በሆነ የፋይናንስ ተቋም ወይም ባንክ ላይ እንደ ሁኔታው የዝግ፣ የተንቀሳቃሽ እና የቁጠባ የሂሳብ ቁጥር መክፈት ይኖርበታል፡፡

2) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ ከወሰኑት የገንዘብ መጠን በላይ በካዝና ወይም በእጅ ሊቀመጥ አይችልም፡፡

3) አግባብ ባለው ባለስልጣን በምስረታ ላይ ያለ ኅብረት ሥራ ማህበር ተመዝግቦ ስራ እስከሚጀምር ከአባላት በተወከሉ የመስራች ኮሚቴ አባላት የሚሰበሰበው የመመዝገቢያ እና የዕጣ ክፍያ በፋይናንስ ተቋም ወይም በባንክ በተከፈተው ዝግ የቁጠባ ሂሳብ ቁጥር እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ ሆኖም የመመዝገቢያ ክፍያው በምስረታ እና በምዝገባ ሂደት ለሚወጡ የተለያዩ ወጪዎች መሸፈኛ ሊውል ይችላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 30 ንኡስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የወለድ አልባ አሰራርን የሚከተሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት የመመዝገቢያና የዕጣ ክፍያ በወለድ አልባ የቁጠባ ሂሳብ እንዲቀመጥ በማድረግ ሊከፈት ይችላል፡፡

5) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በቋሚነት በምስረታ የጠቅላላ ጉባዔ ለሚመረጡ የሥራ አመራር ኮሚቴ በተወከሉ የጋራ ፊርማ እንዲንቀሳቀስ አግባብ ባለው ባለስልጣን ተገቢው ድጋፍ ይሰጣል፡፡

6) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በማናቸውም ጉዳይ የፋይናንስ ተቋም ወይም የባንክ ሂሳብ የሚያንቀሳቅሱ አካላት ሲቀየሩ የተንቀሳቃሽና የቁጠባ የሂሳብ ቁጥር አዲስ በተመረጡ የሥራ አመራር ኮሚቴ እና በተወከሉ አካላት የጣምራ ፊርማ የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡

7) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከላው የሥራ ባህሪ፣ የስራ ስፋት፣ ለአባላት እና ለገበያ ተደራሽነት ሲባል ጥናትን መሰረት በማድረግ በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ሲወሰን ከተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ወይም የባንክ ቁጥሩ ሊከፍቱ ይችላሉ፡፡

8) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ7 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በተለያዩ ባንኮች ውስጥ የተለያዩ የሂሳብ ቁጥር መከፈቱ የኅብረት ሥራ ማህበሩን አደጋ ላይ እንደሚያደርስ ሲያምንበት አግባብ ያለው ባለስልጣን እስኪጠራ ሊያዘገየው ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ምዝገባ እና የምዝገባ የምስክር ወረቀት

### 31. ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት የአመዘጋገብ ስርዓት

1) ለምዝገባ የሚቀርብ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለምዝገባ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶችን፣ አግባብ ባለው ባለስልጣን የሚወጡ የተለያዩ መመሪያዎች፤ ዓለም አቀፍ የኅብረት ሥራ መርሆዎች እና እሴቶችን ተገንዝበው እና አሟልተው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በሀገሪቱ በተፈቀደው የኅብረት ሥራ ህግ መሰረት ካልተመዘገበ በስተቀር ዬትኛውንም ቢዚነስ ወይም ንግድ ማከናወን አይችልም፡፡

3) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ለምዝገባ የሚቀርቡ ማናቸውም ማመልከቻ በተዘጋጀው ቅፅ እና አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚወስነው መንገድ ለምዝገባ መቅረብ አለበት ፡፡

4) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር ለምዝገባ ሲቀርብ በተጨማሪነት የምዝገባ ማመልከቻውን ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡

   ሀ) በጠቅላላ ጉባኤ አባላት ፊርማ የተረጋገጠ መተዳደሪያ ደንብ፤

   ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት ስምና አድራሻ፤

5) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ማንኛውም ከመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በላይ የሆነ የኅብረት ሥራ ማህበር ለምዝገባ ሲቀርብ በተጨማሪነት የምዝገባ ማመልከቻውን ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡-

   ሀ) የመስራች ኅብረት ሥራ ማህበራት ቃለ-ጉባኤ፣

   ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሀብትና ዕዳ መግለጫ፣

   ሐ) በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ዕቅድ፤

   መ) በጽሁፍ የተዘጋጀ የአደራጅ ባለሙያ ሙያዊ የምስክርነት ቃል እና አስተያየት፣

   ሠ) ለምዝገባ በሚቀርብ የመተዳደሪያ ደንብ ሠነድ ላይ ሕጋዊነቱን ለማረጋገጥ የቴምብር ማስለጠፍ ይኖርበታል፤

   ረ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም ለምዝገባ ሠርተፍኬት ለባንክ ገቢ የሆነበትን ደረሰኝ አንድ ኮፒ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

6) መዝጋቢው በልዩ ሁኔታ ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች ላለው ልጅ ዕድሜው ለመደራጀት እስኪደርስ ድረስ በሞግዚቱ አማካኝነት የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ሆኖ ለመቀጠል ሊፈቅድለት ይችላል፡፡ ሆኖም በሞግዚነት ስለሚደረግ አባልነት አፈፃፀም በተመለከተ ማንኛውም የኅብት ሥራ ማህበር በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ሊወስን ይችላል፡፡

7) አግባቡ ያለው ባለስልጣን ኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚመዘግብበት የፕሮቶኮል መዝገብ ይኖረዋል፡፡ የምዘገባ ፕሮቶኮል ናሙና እዝል ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዟል፡፡

8) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለምዝገባ የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡ ስለሚከፈለው የገንዘብ መጠን በእዝል ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዟል፡፡

9) ለምዝገባ የሚቀርብ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለምዝገባ የሚያግዙ አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶችን አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡

10) አግባብ ያለው ባለስልጣን የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ለተገልጋዩ ግልጽ በሆነ ቦታ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

11) የኅብረት ሥራ ማህበራት ከመመዝገባቸው አስቀድሞ በአደራጅ ባለሙያ ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

12) አደራጅ ባለሙያው የመደራጀት ጥያቄውን ተከትሎ ለማደራጀት ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ስለመደረጉ እና የኅብረት ሥራ ማህበሩ በመደራጀቱ ስለሚኖረው ጠቀሜታ በተመለከተ ሙያዊ የምስክርነት ቃሉን እና አስተያየቱን በጽሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

13) በኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት መመሪያ መሰረት እንዲመዘገቡ በአደራጅ ባለሙያ ተገምግሞ የቀረበውን የኅብረት ሥራ ማህበራት መረጃ መሰረት በማድረግ መዝጋቢው ባለሙያው የሚከተሉ ጉዳዮችን ያጠራል፡-

   ሀ) ለምዝገባ ጥያቄ የሚያቀርቡ ኅብረት ሥራ ማህበራትን በምዝገባ መገምገሚያ ቅጽ ላይ ሞልቶና ትክክለኛነቱ አረጋግጦ ማቅረብ አለበት፤

   ለ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ ያቀረበውን መረጃ ወደ ህጋዊ ሰውነት መመዝገቢያ መዝገብ ማስተላለፍ አለበት፤

   ሐ) በክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም በዞን ወይም በክፍለ ከተማ በመለየት የምዝገባ መለያ ቁጥር በቅደም ተከተል መስጠት አለበት፤

   መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አይነት፤ መለያ ቁጥር ወይም ኮድ መሰጠት አለበት፤

   ሠ) የምዝገባ ክፍያ የተፈጸመበት መረጃ ማያያዝ አለበት፤

   ረ) ስለመረጃው ትክክለኛነት የተሰጠበትን ቀን በማስፈር መዝጋቢው በፊርማ ማረጋገጥ አለበት፤

   ሰ) የምስክር ወረቀቱን በማዘጋጀት ከመተዳደሪያ ደንቡ ጋር በመሸኛ ደብዳቤ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ መስጠት አለበት፤

   ሸ) ለምዝገባ በሚያቀርብበት ጊዜ ከሚቀርበው መተዳደሪያ ደንቡ ጋር ቴምብር አብሮ መያያዝ ወይም መለጠፍ ይኖርበታል፡፡

## 32. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት መዝጋቢ አካላት</u>

1) መዝጋቢው አካል አንድን የኅብረት ሥራ ማህበር የማይመዘግበው መሆኑ ሲታወቅ የማይመዘግብበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከተመዘገበበት ዕለት ጀምሮ ሕጋዊ ህልውናው ይጀምራል፡፡

3) የአዋጭነት ጥናት ተዘጋጅቶ አዋጭ መሆኑ እና በሚደራጅበት አከባቢ መስራት የሚችል መሆኑ የተረጋገጠለት የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ላለው ባለስልጣን ቀርቦ ይመዘገባል፡፡

4) መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት፤ የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽኖች አስፈላጊውን መስፈርት ማሟላታቸው ሲረጋገጥ እንደየባህሪያቸው በወረዳ ወይም በዞን ወይም ክፍለ ከተማ ወይም በክልል ወይም በፌደራል ደረጃ ባሉ የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ቀርቦ ይመዘገባል፡፡

5) በሁለት ወረዳዎች መካከል የሚቋቋም መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች በዞን ወይም ክፍለ ከተማ ደረጃ በሚገኘው የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ቀርቦ ይመዘገባል፡፡

6) በሁለት ዞኖች ወይም ክፍለ ከተሞች መካከል የሚቋቋም ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር ደረጃ በሚገኘው የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ቀርቦ ይመዘገባል፡፡

7) በልዩ ባህሪያቸው ምክንያት በክልል ደረጃ መመዝገብ የማይችሉና በሁለት ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሚመጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚቋቋም ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ደረጃ ቀርቦ ይመዘገባል፡፡

8) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚመዘገብ ይሆናል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሁሉንም የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚወክል የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ በአገር አቀፍ ደረጃ ይመዘገባል፡፡ ለምዝገባው ማረጋገጫ ህጋዊ ሰርተፊኬት ይሰጠዋል፡፡

9) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ ለምዝገባ ሲቀርብ ማሟላት የሚገባው መስፈርቶች መካከል፤

ሀ) የመተዳደሪያ ደንብ፣

ለ) ስለሚከናወናቸው ጉዳዮች የያዘ የ5 አመት የስትራቴጂክ እቅድ፣

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ የሚመሩ ከሊጉ ጠቅላላ ጉባኤ የተወከሉ አመራሮች ስምና ፍርማ፣

10) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 10 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው ባለስልጣን በኅብረት ሥራ ማህበሩ የቀረበለትን የምዝገባ ማመልከቻ በተዘጋጀው የምዝገባ ቅጽ ወይም ፎርማት መሰረት መተዳደሪያ ደንብ እና የንግድ ስራ እቅድ በመመዝገብ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ በመዝጋቢው አካል የተረጋገጠ የመተዳደሪያ ደንቡን 1 ኮፒ ለተመዝጋቢው ኅብረት ሥራ ማህበር ይሰጠል፡፡

11) የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መሰረታዊ መረጃ አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚያዘጋጀው ቅጽ ወይም ፎርማት ተሰብስቦ በመዝገብ ላይ ቢያንስ በየሦስት አመቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡

12) የኅብረት ሥራ ማህበራት በየደረጃው ተደራጅተው አስፈላጊውን መስፈርት ሲያሟሉ ቋም የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡

13) ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጠው የምስክር ወረቀት እንዳስፈላጊነቱ ተመሳሳይ ወይም የተለያየ መልክ እና ይዘት ሊኖረው ይችላል፡፡

14) የኅብረት ሥራ ማህራትን የሚመዘግብ ማንኛውም መዝጋቢ ባለሙያ ለምዝገባ የቀረቡለትን ሠነዶችን መሠረት በማድረግ የሚመዝንበትን ቼክሊስት ማዘጋጅት አለበት፣

15) የምዝገባ ሠርተፊኬት ከመሰጠቱ በፊት ማንኛውም መዝጋቢ አካል ለመደራጀት የቀረበውን የኅብረት ሥራ ማህበር በአካል በመገኘት በተዘጋጀው ቼክሊስት መሰረት መገምገምና መመዘን ይኖርበታል፡፡

16) የኅብረት ሥራ ማህራትን የሚያደራጀው እና መዝጋው ባለሙያዎች ለምዝገባ ብቁ የሚያደርጋቸውን ግምገማ እና ምዘና በመቀናጀት ያካሄዳሉ፡፡

17) በተዘጋጀው የምዝገባ ማረጋገጫ ቼክሊስቱ መሰረት ለምዝገባ ብቁ መሆናቸው ሲረጋገጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀት መሰጠት አለበት፡፡

## 33. <u>ስለ የምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>

1) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው ወደ ስራ ከመግባታቸው አስቀድሞ በአዋጅ ቁጥር 985/2009 ዓ.ም በተደነገገው መሰረት አግባብ ካለው ባለስልጣን የምዝገባ ሰርተፊኬት ማግኘት አለባቸው፡፡

2) ማንኛውም በአዲስ የተደራጀ የኅብት ሥራ ማህበር በጠቅላላ ጉባኤ አባላት በተመረጡ የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት አማካይነት ለምዝገባ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በማሟላት የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ እንዲሰጠቸው አግባብ ላለው ባለስልጣን ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡

3) ማንኛውም በጋራ ተደራጅቶ ለመስራት የተዘጋጀ ግለሰብ ወይም የኅብረት ሥራ ማህበር የሚቋቋምበትን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲችልና በህግ ፊት ተቀባይነት እንዲኖረው አግባብ ባለው ባለስልጣን ተመዝግቦ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

4) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የምዝገባ መስፈርቶችን አስቀድሞ በሚሟላት አግባብ ባለው ባለስልጣን ለመመዝገብ ከተፈቀደለት ቋሚ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚደራጅ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የምዝገባ መስፈርቱን ሲያሟላ የምዝገባ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

6) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ (1 እና 2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን በሥራ ቦታ ወይም ጽ/ቤት ውስጥ ግልፅ በሆነ ቦታ እንዲታይ ሆኖ መቀመጥ አለበት፡፡

## 34. ጊዜያዊ የምዝገባ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት በየደረጃው ተደራጅተው አስፈላጊውን መስፈርት ካላሟሉ ለአንድ አመት ብቻ የሚቆይ ጊዜያዊ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡

2) ጊዜያዊ ምስክር ወረቀት ያገኘ ኅብረት ሥራ ማህበር በተመዘገበበት የጊዜ ገደብ ውስጥ  ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ያለው መብት እና ግዴታ ይኖረዋል፡፡

3) በኅብረት ሥራ ማህበራት በአዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 10 (8) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዘጠኝ ወራት ውስጥ የተጓደሉትን መስፈርቶችን አሟልቶ  ቋሚ የምሰክር ወረቀት ካልወሰደ ተጨማሪ 3 ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡

4) በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተጓደሉትን መስፈርቶች ካሟላ ተገቢውን ክፍያ ፈጽሞ የቋሚነት የምስክር ወረቀት በማግኘት ነባሩን ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

5) በዚህ አንቀጽመሠረት የጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያገኘ ኅብረት ስራ ማህበር በአንድ ዓመት ውስጥ ተፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ በቋሚነት ካልተመዘገበ ከአንድ አመት በኋላ  በህግ ፊት ተቀባይነት አይኖርም፡፡ አግባብ ባለው ባለሥልጣን የኅብረት ሥራ ማህበሩን በማፍረስ ህልውናውን እንዲያጣ ያደርጋል፡፡

6) በአዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 2 /ሀ/ እስከ /ሰ/ የተደነገገው እንደጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽአንቀጽ 33 ን/አንቀጽ 3 ከ (ሀ-ቀ) መሰረት ለምዝገባ የቀረቡትን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ያላሟላ ኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ያለው ባለስልጣን ከአንድ ዓመት በላይ ላልበለጠ ጊዜ የሚያገለግል ጊዜያዊ የምዝገባ የምስክር ወረቀት በመስጠት የተቀሩትን መስፈርቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ማሟላት አለበት፡፡

7) በተቀመጠለት የአንድ አመት ጊዜ ገደብ ውስጥ የቀሩትን መስፈርቶች ሳያሟለ የቀረ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ህልውናውን እንዳጣ ስለሚቆጠር የተረከበውን ጊዜያዊ የምዝገባ የምስክር ወረቀት በወቅቱ መመለስ ይኖርበታል፡፡

8) በዚህ አንቀጽመሰረት ህልውናውን የሚያጣ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የማፍረስ ሂደት ተፈጻሚ የሚሆነው በአዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 55 እስከ አንቀጽ 60 በተደነገገው መሠረት መሆን አለበት፡፡

## 35. ምትክ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

1) ኅብረት ሥራ ማህበራት ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ጥያቄ የሚቀርበው የምስክር ወረቀቱ ሲጠፋ ወይም ሲበላሽ ወይም የስም ለውጥ የሚደረገው ሆኖ የሚከተሉት ተሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡

ሀ) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የምዝገባ ምስክር ወረቀት ሲጠፋበት በሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው ባለስልጣን ሲያሳውቅ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በህግ አካል የተረጋገጠ መረጃ መቅረቡን አጣርቶ ምትክ የምዝገባ መስክር ወረቀቱን አጽድቆ በሁለት ተከታታይ የስራ ቀን ውስጥ ይሰጣል፡፡

ለ) የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ የተበላሸ ከሆነ የተበላሸውን የምስክር ወረቀት አግባብ ያለው ባለስልጣን ሲያረጋግጥ፣ ከሁለት ተከታታይ የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ይሰጣል፡፡

ሐ) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ የፀደቀ የስም ለውጥ ጥያቄ ሲያቀርብ አግባብ ያለው ባለሥልጣን አጣርቶ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ያወጣል፡፡ ጋዜጣው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ሰላሳ ቀን ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ የስም ለውጡን አጽድቆ ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን በሁለት ተከታታይ የስራ ቀን ውስጥ ይሰጣል፡፡

መ) ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ለመስጠት የቀረበው ጥያቄ አሳማኝ ካልሆነ አግባብ ያለው ባለስልጣን ከሁለት ተከታታይ የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ የማይሰጥበትን ምክንያት በመግለጽ በጽሑፍ ለኅብረት ስራ ማህበሩ ያሳውቃል፡፡

## 36. <u>ደረጃን መሰረት ያደረገ የምዝገባ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ</u>

1) ለምዝገባ የሚቀርብ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በተዘጋጀው የመመዘኛ መስፈርት መሰረት የአፈጻጸም ደረጃቸውን የሚገልጽ የተለያየ ቀለም ያለው የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡

2) የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያገኙት የምስክር ወረቀት እንዳስመዘገቡት ውጤት ዓይነት የሚከተሉትን ቀለም ያለው የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ሊሆን ይችላል፡-

ሀ) በደረጃ “ሀ” የሚለዩት “አረንጓዴ” ቀለም መልክ ያለው የምስክር ወረቀት፣

ለ) በደረጃ “ለ” የሚለዩት “ቢጫ” ቀለም መልክ ያለው የምስክር ወረቀት፣

ሐ) በደረጃ “ሐ” የሚለዩት ደግሞ “ቀይ” ቀለም ያለው ላይ የምስክር ወረቀት፣

3) በሚሰጣቸው የምስክር ወረቀት መሰረት ደረጃቸውን የሚመጥን ጥቅማ ጥቅምና የድጋፍ ፓኬጅ የሚያገኙ ይሆናል፡፡

4) የአረንጓዴ ቀለም ያለው የምስክር ወረቀት የሚያገኙ ኅብረት ሥራ ማህበራት፤

ሀ) የተቋቋሙበትን መሠረታዊ ዓላማና ተግባር በላቀ ደረጃ ያሳኩ፣

ለ) አባላትን በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ማድረግ የቻለ፣

ሐ) የአባላትን መሰረታዊ የሆኑ ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ችግሮቻቸውን የፈቱ፣

መ) በአካባቢ ልማት እና ዕድገት ላይ ባደረጉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሕብረተሰቡን ችግሮች በከፍተኛ ደረጃ ያቃለሉ፣

ሠ) መንግስት ላስቀመጣቸው የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ግቦች ስኬት የድርሻቸውን በከፍተኛ ደረጃ በመወጣት ላይ ያሉ፣

ረ) ከአባላቱ ያለው የጋራ ግንኙነትና ትስስር እና አባላቱ አብረው ለመስራት የሚያሳዩት የተጠናከረ ቁርጠኝነት ያላቸው፣

5) ብጫ ቀለም ያለው የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት የተቋቋሙበትን መሠረታዊ ዓላማ በዚህ አንቀጽአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 4 (ሀ-ረ) በተገለፀው መሰረት በመካከለኛ ደረጃ ያሳኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

6) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 5 በተገለፀው መሰረት ከሁለት ተከታታይ ጊዜ በላይ ሳይሻሻል ከዝቅተኛው የቢጫ ጫፍ ላይ የቆየ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በሚቀጥለው ወደ ቀይ ዝቅ ይደረጋል፣

7) የተቋቋሙበትን መሠረታዊ ዓላማ ማሳካት ያልቻሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ቀይ ቀለም ያለው የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

8) ቀይ ቀለም ያለው የምስክር ወረቀት ከሁለት ተከታታይ ጊዜ በላይ ሳይሻሻል ይዘው የሚገኝ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በየደረጃው የሚገኘው አግባብ ያለው ባለስልጠና ጥናት ላይ በመመስራት የማፍረስ ወይም የማዋሃድ ውሳኔ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

9) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 8 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀይ ቀለም ያለው የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት የማፍረስ ወይም የማዋሃድ ውሳኔ የሚተላለፈው፤

ሀ) ከተቀመጠው መስፈርት መሰረት የኅብረት ሥራ ማህበሩ በስራ ላይ የሌለ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ) የማፍረስ ሕግን ተከትሎ ያልፈረሰ ግን በራሱ የፈረሰ፣

ሐ) በተቋቋመበት አላማና ተግባር ላይ አለመኖሩ ሲረጋገጥ፣

መ) ለአባላት ምንም ዓይነት የኢኮኖሚ ጠቀሜታ እና አገልግሎት የማይሰጥ ሲሆን፣

ሠ) አፈፃፀሙን ለማሻሻል የማይቻል ደረጃ ላይ ሲገኝ፣

ረ) ለማጠናከር ምንም አማራጭ ሁኔታ ሳይኖር ሲቀር፣

ሰ) ከአባላት ጋር ምንም ዓይነት  ግንኙነት የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሸ) የሥራ አመራር ኮሚቴ አካላት በሥራ ላይ ከሌሉ፣

## 37. የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማሳደስ

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር147/91 መሠረት የተደራጀ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ይህ የአደረጃጀት መመሪያ ከወጣ ጊዜ ጀምሮ በ1 አመት ጊዜ ውስጥ በአዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ምዝገባቸውን ማሳደስ ይኖርባቸዋል፡፡

2) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 37 ንኡስ አንቀጽ (1) ስለ ምዝገባ የምስክር ወረቀት እድሳት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኅብረት ሥራ ማህበራት የተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት በየሶስት ዓመቱ ይታደሳል፡፡

3) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 37 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቋሚ የምስክር ወረቀት የአገልግሎት ዘመን ከምስረታ በኋላ ወይም የምሰክር ወረቀቱ ከታደሰ ከሦስት ዓመት በላይ አያገለግልም፡፡

4) የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ የአገልግሎት ጊዜ ከማብቃቱ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በየደረጀው ለሚገኘው አግባብ ላለው ባለስልጣን ቀርቦ መታደስ አለበት፡፡

5) በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ የማይታደስ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ሕጋዊ የምስክር ወረቀቱን በሕግ ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ስለሆነም አግባብ ባለው ባለስልጣን ሕግን ተከትሎ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ ሊነጥቅ ይችላል፡፡

6) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማሳደስ የሚከተሉትን መሟላት አለበት፡፡

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የተሻሻለ የመተዳደሪያ ደንብ ሦስት ቅጂ፣

ለ) የሦስት አመት ስትራቴጂክ እቅድ፣

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን አጠቃላይ አቋም የሚገልፅ ያለፉት ሦስት አመታት አጭር የጽሁፍ መግለጫ፤ መግለጫው በእዝል ውስጥ ተመላክቷል፡፡

መ) በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የዘመኑ ከኦዲት ሪፖርቱ ውስጥ የትርፍና ኪሳራ እና የሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመሳከረ ኮፒ፣

ሠ) የብቃት ደረጃ ዕውቅና ማረጋገጫ ሠርተፊኬት፣

ረ) የቀጣይ ሦስት ዓመት ዕቅድ፣ የሦስት አመቱ አቅድ ፎርማቱ በእዝል ውስጥ ተመላክቷል፡፡

ሰ) ለዕድሳት የሚከፈለውን ገንዘብ ገቢ ያደረገበት ደረሰኝ፣

ሸ) የአባላትን ቁጥር የሚገልፅ መረጃ፣

ቀ) በተከታታይ ላለፉት ሦስት አመታት ኪሳራ ያላሳየ ስለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ፣

ቀ) ባላፉት ሦስት አመታት በአማካይ የአባላት የግብይት ተሳትፎ የተሻሻለ መሆኑን የሚሳይ መረጃ፤

7) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 37 ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላሳደሰ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ባለው ባለሥልጣን የሚከተሉት እርምጃዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

ሀ) ከመንግስት የሚያገኛቸውን ማናቸውም ድጋፎች ይቋረጣሉ፣

ለ) በምዝገባ ምስክር ወረቀቱ የሚያደርጋቸው ማናቸውም ውሎች እና ስምምነቶች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፣

ሐ) አግባብ ያለው ባለስልጣን የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ ህጋዊነት የሌለው መሆኑን የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ሊያሳውቅ ይችላል፣

8) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 37 ንዑስ አንቀፅ 7 (ከሀ-ሐ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ እርምጃ ተከትሎ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማሳደስ ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ አግባብ ያለው ባለስልጣን ሕግን ተከትሎ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን እንዲመልስ ያደርጋል፡፡

9) የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት መመሪያ መሰረት በማድረግ አግባብ ያለው ባለስልጣን ለነባር የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደገና ስለሚመዘገብበት ሁኔታና የጊዜ ገደብ በሚዲያ ወይም በጽሁፍ መሳወቅ ኖርበታል፡፡

10) አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚያስቀምጠው አሰራር መስፈርት መሰረት የምዝገባ ሠርተፊኬት እንደገና ስለማደስ፤

ሀ) የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ጥሪ ያስተላልፋል፣

ለ) ጥሪ ወይም ደብዳቤ የደረሰው ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ቀርቦ ሠርተፊኬቱን ማሳደስ ይኖርበታል፣

ሐ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ አማካኝነት የእድሳት ጥያቄ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፣

11) አግባብ ላለው ባለስልጣን የምዝገባ ሠርተፊኬት ለማሳደስ የሚሰሩ 3 አባላት ያሉት የእድሳት ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

## 38. <u>የእድሳት ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት</u>

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ መመርመሩን ያረጋግጣል፣

2) እድሳት የሚደርጉ የኅብረት ሥራ ማህበራትን አጠቃላይ የሀብትና እዳ መግለጫ መረጃ ተጣርቶ መቅረቡን ያረጋግጣል፤

3) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት መረጃ ተጣርቶ መቅረቡን ያረጋግጣል፣

4) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን መረጃ መቅረቡን ያረጋግጣል፣ ይመዘግባል፤

5) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ በአዲስ መልኩ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣

6) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚያግዙ ረቂቅ የሥራ እቅድ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣

## 39. <u>የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚደረግ ክፍያ</u>

1) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለምዝገባ በሚቀርብበት ጊዜ የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 እና ለማስፈጸም በወጣው ደንብ መሰረት ሆኖ የምከፈለው የምዝገባ ክፍያ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) በአዲስ ለሚደራጅ የኅብረት ሥራ ማህበር ቋሚ የምዝገባ ሠርተፍኬት ለማግኘት ብር 100.00

ለ) ምትክ የምዝገባ ሠርተፍኬት ለማግኘት ብር 200.00

ሐ) ጊዜያዊ የምዝገባ ሠርተፍኬት ለማግኘት ብር 50.00

መ) ለምዝገባ ሠርተፍኬት ዕድሳት ብር 100.00

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በስሙ በባንክ ገቢ የሆነበትን ደረሰኝ አንድ ኮፒ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

## 40. የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለሚከለከልበት ሁኔታ

1)ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በሚከተሉት ምክንያቶች ምዝገባ ይከለከላል፡-

ሀ) በአከባቢው አስቀድሞ በተመሳሳይ ስምና አርማ የተመዘገበ ኅብረት ሥራ ማህበር ያለ መሆኑ ከተረጋገጥ፤

ለ) እንደ አስፈላጊነቱ የራሱ የሆነ የፕሮጀክት ጥናት የሌለው ከሆነ፤

ሐ) በአዋጅ ቁጥር 985/2009 እና በዚህ አንቀጽመሰረት ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ያላሟላ ከሆነ፤

መ) ዓላማው የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ወይም አግባብ ባለው ባስልጣን የወጡ መመሪያዎችን የሚጻረር ከሆነ ተመዝግቦ የምስክር ወረቀት ማግኘት አይችልም፡፡

## 41. የምዝገባ የምስክር ወረቀትን ስለማገድ

1) በዚህ አንቀጽመሠረት የተመዘገበ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በአዋጅ 985/2009 መሠረት አለመስራቱን አግባብ ባለው ባለስልጣን ሲረጋገጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ሊያግድ ወይም ሊነጥቅ ይችላል፡፡ ሆኖም የምስክር ወረቀት በምን ምክንያት እንደሚያግድና እንደሚነጥቅ ለጠቅላላ ጉባዔ ያሳውቃል፡፡

2) የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በአዋጅ ቁጥር 985/2009 መሰረት በሚከተሉት ሁኔታዎች ምክንያት ከስራ ይታገዳል፡-

ሀ) ቀደም ሲል ያቀረባቸው የመመዘኛ መስፈርቶች የተጭበረበሩ ወይም ያልተሟሉ መሆኑን በክትትል እና ግምገማ ወቅት ከተረጋገጠ፤

ለ) የሚጠበቅበትን ትክክለኛ የሆነ መረጃ ለመዝጋቢ አካላት ያላቀረበ ከሆነ፣

ሐ) የወጡ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን አክብሮ የማይገኝ ከሆነ፤

መ) በአባላት መብትና ጥቅም ላይ ወይም በአገር ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑ ተረጋግጦ ሲቀርብ፣

ሠ) መንግስት ፖሊሲ ጋር የማይጣጣም ሲሆንና እንዲታገድ ሲወሰን፣

ረ) ተገቢው ድጋፍ እየተደረገለት የእድሳት ጊዜውን ያሳለፈ ወይም የሚጠበቅበትን ግዴታ ያልተወጣ፣

3) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 2 ከ(ሀ-ረ) በተደነገገው መሰረት በእግዱ ላይ ቅሬታ ያለው የኅብረት ሥራ ማህበር እግዱ እንዲነሳለት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን አግባብ ላለው ባለስልጣን ማቅረብ ይርበታል፡፡ እግዱ እንዲነሳለት በወቅቱ ካላቀረበ አግባብ ያለው ባለስልጣን የመሰረዝ ሂደቱ ይጀመራል፤

4) ኅብረት ሥራ ማህበሩ የታዩበት ጉድለቶች እስኪስተካከሉ ድረስ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም፡፡ በዚህን ጊዜ በምዝገባ የምስክር ወረቀቱ በመጠቀም የሚደረጉ ማናቸውም ውሎች እና አሰራሮች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

5) አግባብ ያለው ባልስልጣን የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ በምን ምክንያት እንደታገደ እና የታዩ ጉድለቶችን በመግለጽ በ15 ቀናት ውስጥ ዕገዳ ለተደረገበት የኅብረት ሥራ ማህበር በደብዳቤ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

6) እገዳ የተደረገበት የኅብረት ሥራ ማህበር የታገደበትን ምክንያት የሚገልፅ ደብዳቤ ከደረሰበት ዕለት አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የታዩ ጉድለቶችን በማስተካከል ማሳወቅ አለበት፣

## 42. የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከመዝገብ ስለመሰረዝ

1) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የምዝገባ ምስክር ወረቀት በምከተሉት ምክንያቶች ከመዝገብ ሊሰረዝ ይችላል፡-

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው በማታለል ወይም የሃሰት ማስረጃ በማቅረብ መሆኑ ሲታወቅ፣

ለ) የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ከተሰጠው ዓላማ ውጪ ለሌላ ተግባር ሲገለገልበት ወይም እንዲገለገሉበት ለሌላ አካል አስተላልፎ ከተገኘ፣

ሐ) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 እና በዚህ አንቀጽአንቀጽ 37 በተደነገገው መሰረት ካልታደሰ፣

መ) ከኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ፣ ደንቦች፣ እና መመሪያዎች ውጪ ሲሰራ ከተገኘ፣

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ህልውናውን ያጣ መሆኑን አግባብ ባለው ባልስልጣን ሲረጋገጥ፣

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በዚህ አንቀጽአንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 1 ከ ሀ - መ ከተዘረዘሩት ድርጊቶች መካከል አንድ ወይም ከዚያ በላይ ያሉ ድርጊቶችን መፈጸሙ አግባብ ባለው ባለስልጣን ሲረጋገጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

3) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ባለው ባለስልጣን የመፍረስ ሕጉን ተከትሎ ከመዝገብ ሲሰረዝ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን መመለስ ይኖርበታል፡፡

4) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለሚሰረዝበት የኅብረት ሥራ ማህበር እንዲያውቀው አስቀድሞ በጽሁፍ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

5) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ባለው ባለስልጣን ከምዝገባ ሲሰረዝ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን በዕለቱ መመለስ አለበት፡፡

6) የምስክር ወረቀቱን የሚመልስ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ሲገለገልባቸው የቆየውን የራስጌና የግርጌ ማህተም አያይዞ መመለስ አለበት፡፡

7) የምስክር ወረቀቱን የሚመልስ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ሲገለገልባቸው የቆየውን በስሙ የተከፈተውን ማንኛውም የባንክ ሂሳብ ቁጥር ማዘጋት አለበት፡፡ ስለመዘጋቱም ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 43. ስለማህበረሰብ ተፋሰሶች ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ምዝገባ

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 አንቀጽ 10 ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ምዝገባ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማህበረሰብ ተፋሰሶች ላይ ለሚደራጁት በተጨማሪ በማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1223/2012 አንቀጽ 10 መሰረት በማድረግ መዝገብ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

2) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 139 ንዑስ አንቀጽ 18 ላይ ስለ ማህበረሰብ ተፋሰሶች ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ምዝገባ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚጠበቅባቸውን ግዴታ አሟልተው ለምዝገባ የሚመጡ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች በኅብረት ሥራ ማህበራት፤

ሀ) በተለየ መዝገብ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

ለ) የተለየ የምዝገባ ምስክር ወረቀት (ሠርተፊኬት) መስጠት ይኖርበታል፡፡

ሐ) ሁሉንም መስፈርት ያላሟሉ ሆነው ሲገኙ በአዋጅ 985/2009 መሠረት ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት (ሠርተፊኬት) የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የኅብረት ሥራ ማህበር አባልነት መስፈርቶች፣ መብትና ግዴታ

### 44. ለአባልነት የሚያበቁ መስፈርቶች

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 24 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባልነት መስፈርት በተጨማሪነት የሚከተሉትን ያካትታል፤

   ሀ) በሕግ መብቱ ያልተገፈፈ እና የአዕምሮ መታወክ የሌለበት፣

   ለ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ ክልል የሚኖር ወይም የሚሰራ፣

   ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ፣ ውስጠ ደንብ፣ ልዩ ልዩ የአፈጻጸም መመሪያዎችን እና የጠቅላላ ጉባኤ የፀደቁ ውሳኔዎች ለመፈፀም ፍቃደኛ የሆነ፣

   መ) በተመሳሳይ ሌላ ኅብረት ሥራ ማህበር አባል ያልሆነ፣

   ሠ) ቀድሞ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ከሚያከናውነው ዓላማና ተግባር ጋር የጥቅም ግጭት በሚኖረው ተግባር ላይ ያልተሰማራ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው አንደተጠበቀ ሆኖ አስቀድሞ ለፌዴሬሽኑ አባል የሆነ ዩኑዬን አባል ያልሆነ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር የኅብረት ሥራ ማህበራት የፌዴሬሽን አባል መሆን ይችላል፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚሁ ተግባር አግባብ ካለው ባለሥልጣን ደጋፊ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይኖርበታል።

### 45. የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት መብት

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 25 (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አባል የሚከተሉትን መብቶች ይኖሩታል፡፡

   ሀ) በጠቅላላ ጉባኤ ሰብሰባ ላይ በመሳተፍ አቋምን ዲሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ በፈቃደኛነት ማራመድ፣

   ለ) አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበራቸው አስፈላጊውን መረጃ የማግኘት

   ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ማንኛውም ጥያቄ፣ ቅሬታና አስተያየት የማቅረብና መልስ የማግኘት፣

   መ) አባላት ኅብረት ሥራ ማህበሩ በሚሰጣቸው ስልጠናዎች ላይ ያለ ልዩነት የመሳተፍ፣

   ሠ) አባልነት ሲቋረጥ የተከፈለውን የዕጣ ዋጋ መልሶ የመካፈል፤

   ረ) አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ተወካይ መሾም፣

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አባል በራሱ ወይም በተወካዮቹ አማካኝነት በህግ የተሰጠውን መብቶቹን ያገኛል፣

## 46. የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት ግዴታ

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 25 (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አባል የሚከተሉትን ግዴታዎች ይኖሩታል፡፡

ሀ) የጠቅላላ ጉባኤው በሚወስናቸው ውሳኔዎች ላይ በወቅቱ በመገኘት ተገቢውን ተሳትፎ ማድረግ፣

ለ) አባላት ለኅብረት ሥራ ማህበራቸው የተሻለ እና ጥራት ያለው ምርት ወይም አገልግሎት በወቅቱ የማቅረብ፣

ሐ) አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበራቸው የተበደሩትን ብድር የመክፈያው ጊዜ ከማለፉ በፊት መመለስ፣

መ) በጠቅላላ ጉባኤ አባላት ውሳኔ የታቀዱ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ድጋፍና ክትትል የማድረግ፣

ሠ) አባል የሆኑ ቅጥር ሠራተኞች እንደ ማንኛውም አባል የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት መወጣት፣

ረ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ኪሳራ የመካፈል፣

ሰ) አባላት የኅብረት ሥራ ማህበሩ የውስጥ ሰላም እንዲረጋገጥ የማድረግ፣

ሸ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ መረዳትና ማክበር፤

ቀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ጥቅም፣ ገጽታ፣ አሠራር ወይም አፈጻጸም ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችል ማንኛውንም ድርጊት ወይም ግድፈት የማስወገድ፤

በ) ለኅብረት ሥራ ማህበሩ አመራር ከፍተኛ ትብብር ማድረግ፣

ተ) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ጋር የሚያደርገውን ማንኛውንም የውል በታማኝነት የማክበር

ቸ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረቶች የመጠበቅ፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ-ቸ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ግዴታውን የማይወጣ ማንኛውም አባል የኅብረት ሥራ ማህበሩ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በሚወሰነው መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፣

## 47. የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ከአባልነት ስለመሰናበት

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 26 ከንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አባል ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚሰናበተው በተጨማሪነት በሚከተሉት ጉዳዮች ይሆናል፤

ሀ) አባል ግለሰብ ሲሞት

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሲፈርስ፣

ሐ) የዲሲፕሊን ጉድለት፣

መ) አባል የሚፈለግበትን የብድር ዕዳ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ፣

ሠ) ለሦስት ተከታታይ መደበኛ ስብሰባ ያለ በቂ ምክንያት ያልተሳተፈ፣

ረ) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓላማና ተግባር ጋር የሚፃረር ተግባር የፈፀመ፣

ሰ) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚገዙ ወይም የሚሸጡ ንብረቶችን የግል ጥቅም ለማግኘት ሲል ከገበያ ዋጋ በታች የሸጠ ወይም ከገበያ ዋጋ በላይ የገዛ ወይም እንዲሸጥ ወይም እንዲገዛ ያደረገ፣

ሸ) በተለያየ ምክንያት በእጁ የገባውን የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረት ለግል ጥቅሙ ያዋለ ወይም እንዲውል ያደረገ፣

ቀ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም ጉቦ ወይም መደለያ የሰጠ ወይም የተቀበለ፣

በ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገንዘብ ሆን ብሎ ያጎደለ ወይም ሁኔታዎችን ያመቻቸ፣

ተ) ለኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚያቀርበውን ምርት ወይም የአገልግሎት ዋጋ በማይገባው ሁኔታ ለማግኘት ጥራቱን ያጓደለ ወይም መጠኑን የቀነሰ፣

2) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 47 ንዑስ አንቀፅ 1 (መ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕዳውን ለመክፍል ፈቃደኛ ካልሆነ በክልል ከሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም በፌዴራል ከሆነ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠይቆ ዕዳውን እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

## 48. አዲስ አባላትን እና የቀድሞ አባላትን እንደገና ስለመቀበል

1) የቀድሞ አባላት ዳግም ወደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለመመለስ በተዘጋጀው የአባልነት ማመልከቻ ቅፅ መሠረት ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ጥያቄውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2) አባሉ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት አባል ከመሆኑ በፊት የሚከተሉት ጉዳዮች የሚጣሩ ይሆናል፤

ሀ) የአባልነት ጥያቄ አቀራቢው በኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ ክልል ውስጥ ስለመገኘቱ፣

ለ) በሌላ ኅብረት ሥራ ማህበር የብድር ዕዳ የሌለበት ስለመሆኑ መረጃ ሲያቀርብ፣

ሐ) ቀደም ሲል ከኅብረት ስራ ማህበሩ የተሰናበተበት ምክንያት በተዘጋጀው ፎርም መሠረት ዝርዝር መረጃ በማመሳከር መሙላት፣

መ) ዳግም ወደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚመለስበት ምክንያት በተዘጋጀው ፎርም መሠረት መሙላት፣

3) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ የአባልነት ጥያቄ ላቀረበው አካል አባል የመሆን ወይም ያለመሆን ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

4) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 26 ከንዑስ አንቀፅ 4 እስከ 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞ አባላት ዳግም እንዲመለሱ በሥራ አመራር ኮሚቴ ሲፈቀድላቸው በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተወሰነውን መመዝገቢያ እና ዝቅተኛውን የዕጣ ዋጋ ክፍያን መፈጸም አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 48 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አዲስ ወይም ዳግም የተመለሱ የቀድሞ አባላት የሚከፍሉት የመመዝገቢያ ክፍያ ቀድሞ በጠቅላላ ጉባዔ የተወሰነው ብቻ ይሆናል፡፡

6) በኅብረት ሥራ ማህበሩ በአዲስ አባልነት ተቀባይነት ካገኘበትና ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ መብትና ግዴታዎቹ ተጠብቀው እንደ ማንኛውም አባል ኅብረት ሥራ ማህበሩ በሚሰጣቸው አገልግሎት መጠቀም ይችላል፤

## 49. <u>የመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት መነሻ ቁጥር አወሳሰን</u>

1) በኅብረት ሥራ ማበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 2 እና 3 እና በአንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት ወይም በማምርት እና አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የተሰማሩ ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የመነሻ ቁጥር እንደሚከተሉትን ይሆናል፤

   ሀ) በእንሰሳት እና እንሰሳት ተዋፅኦ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የመነሻ ቁጥር 80 ሰው ይሆናል፡፡

   ለ) በሰብል እና የደን ውጤቶች የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የመነሻ ቁጥር 100 ሰው ይሆናል፡፡

   ሐ) በአከባቢ መሰረት አድረገው የሚደራጁ የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት የመነሻ ቁጥር 250 ሰው ይሆናል፡፡

   መ) ተቋምን መሰረት አድረገው የሚደራጁ የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት የመነሻ ቁጥር 100 ይሆናል፡፡

   ሠ) በአከባቢ መሰረት አድረገው የሚደራጁ በገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት የመነሻ ቁጥር 100 ሰው ይሆናል፡፡

   ረ) ተቋምን መሰረት አድረገው የሚደራጁ በገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት የመነሻ ቁጥር 80 ሰው ይሆናል፡፡

   ሰ) በመኖሪያ ቤቶች የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁ አባላት የመነሻ ቁጥር በገጠር 50 በከተማ 24 ይሆናል፡፡

   ሸ) የሁለገብ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁ አባላት የመነሻ ቁጥር 250 ይሆናል፡፡

   ቀ) በአትክልትና ፍራፍሬ እና በመስኖ ሥራዎች ላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁ አባላት የመነሻ ቁጥር 50 ይሆናል፡፡

   በ) የተለያዩ ቀሚ እና አላቂ ሀብቶችን መሰረት አድርገው የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ባለው ሀብት እና በአዋጭነት ጥናት መሰረት የመነሻ ቁጥሩን አግባብ ያለው ባለስልጣን ይሰናል፡፡ ሆኖም መነሻ ቁጥሩ ከ10 ሰው ማነስ አይችልም፡፡

2) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 49 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአዋጅ 985/2009 አስቀድሞ የተደራጁ አባላት የመነሻ ቁጥር እንዳስፈላጊነቱ አዋጭነቱን መሰረት በማድረግ የአባላት ቁጥር እንዲጨምር አግባብ ያለው ባለስልጣን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 50. <u>የአባላት መዝገብ ስለ ማደራጀት</u>

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 28 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአባላት መዝገብ በተጨማሪነት የሚከተሉትን ይይዛል፤

   ሀ) የጋብቻ ሁኔታ፣

ለ) የቤተሰብ ብዛት፣

ሐ) መደበኛ ስራ፣

መ) የገዛው ዕጣ በዓይነት ወይም በገንዘብ፣

ሠ) ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ከሆነ የአባል ኅብረት ሥራ ማህበር፤ ስም፣ የግለሰብ አባላት ብዛት፣ ፆታ የቤተሰብ ብዛት፣ ካፒታል፣ ቁጠባ፣ ተቋቋመበት እና የፈረሰበት ቀንና ዓመተ ምህረት፡፡ የአባላት መዝገብ ፎርም በመመሪያው የእዝል ክፍል ውስጥ ተያይዟል፡፡

2) በመተዳደሪያ ደንቡ የተወሰኑ ሌሎች ዝርዝሮች፡፡

## 51. ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት በውክልና ድምጽ አሰጣጥ

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀፅ 3-6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን የጠቅላላ ጉባኤ አባላት በውክልና ድምፅ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

2) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አባላቱ በራሳቸው ሙሉ ፍላጎትና እምነት መሰረት የተወካዮችን ታማኝነት፣ ውሳኔ ሰጭነት፣ ባላቸው የነቃ ተሳትፎ፣ በምሳሌነታቸው እና በሌሎች ተዛማጅ መስፈርቶች በመነሳት በጠቅላላ ጉባዔ ላይ የሚሳተፉ አባላትን ሊወክሉ ይችላሉ፡፡

3) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ቁጥር ከ500 በላይ ከሆነ የጠቅላላ ጉባኤ በውክልና ሊካሄድ ይችላል፡፡ ሆኖም በመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር አንድ ተወካይ የሚወክላቸው አባላት ቁጥር ከፍተኛው ከ500 ሰው በላይ ሊሆን አይችልም፣

4) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ስለ ጠቅላላ ጉበኤ ውክልና የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ውክልናን መሰረት አድሮጎ የሚካሄድ የማንኛውም የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር የጠቅላላ ጉባዔ አባላት ብዛት ከፍተኛው 1000 አባላት ሊበልጥ አይችልም፣

5) የሚደረገው የጠቅላላ ጉባኤ ውክልና አሰጣጥ እንደየኅብረት ሥራ ማህበራቱ አባላት መጠን የሚወሰን ሆኖ ግልፅነት ያለው አሳማኝና በጥናት ላይ የተመሰረት መሆን አለበት፣

6) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የአባላት ቁጥር ከተጠቀሰው በላይ የሚሆን ከሆነ ለዚህ ተግባር ሊሆን የሚችል ቴክኖሎጅ በመዘርጋት እና ቴክኖሎጅውን በመጠቀም የጠቅላላ ጉባዔ ማካሄድ ይቻላል፡፡ ስለ አፈፃፀሙና አጠቃቀሙ በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ ሊወስኑ ይችላሉ፣

7) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ዝርዝር የውክልናውን አካሄድ በተመለከተ በጠቅላላ ጉባዔ ተወስኖ በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ በማካተት ተግባራዊ መደረግ አለበት፣

8) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 6 እና 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ጠቅላላ ጉባኤ የሚመሰረተው ከእያንዳንዱ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር አንድ ተወካይ የሚኖረው ሲሆን እንደየኅብረት ሥራ ማህበራቱ የአባላት ብዛት ተጨማሪ ተወካይ የሚኖረው ይሆናል፡፡ የተጨማሪ ተወካዮችም አወካከል ዝርዝር በመመሪያው እዝል ውስጥ ተያይዟል፡፡

9) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 51 ንዑስ አንቀጽ 8 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አባል የሚሆን ሌላ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን የሚኖረው የጠቅላላ ጉባኤ ውክልና ከአስራ አንድ ሊበልጥ አይችልም፣

10) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 6 እና 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን የጠቅላላ ጉባኤ የሚመሰረተው ከእያንዳንዱ አባል የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አንድ ተወካይ የሚኖረው ሲሆን እንደየኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን የአባላት ብዛት ተጨማሪ ተወካይ የሚኖረው ይሆናል፡፡ የተጨማሪ ተወካዮችም አወካከሉ በመመሪያው እዝል ውስጥ ተያይዟል፡፡

11) በልዩ ባህሪያቸው በቀጥታ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን አባል የሚሆኑ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት እያንዳንዳቸው ሁለት ተወካይ ይኖራቸዋል፡፡

12) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ውሳኔ የሚተላላፈው በአባላት በአብላጫ ድምፅ ሆኖ የምልዓተ- ጉባዔ ወይም ኮረም መሟላት ይኖርበታል፡፡ የምልዓተ- ጉባዔ ወይም ኮረም መሰረት ያደረገ የድምጽ አሰጣጥ ሂደትን በተመለከተ እንደየኅብረት ሥራ ማህበራት አይነት እና ደረጃ በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ ሊወሰኑ ይገባል፡፡

13) ተወካዮች በስብሰባዎች ጊዜ የሚሰጡት የውሳኔ ድምፅ የወከላቸውን ሰዎች መብት ከግምት በማስገባት ሊሆን ይገባዋል፡፡

14) ተወካዮች ወሳኝ በሆኖ ጉዳዮች ላይ ድምፅ በሚሰጥበት ሂደት የኅብረት ሥራ ማህበራት ስራ አመራር ኮሚቴ ለአባላት ተደራሽ በሚሆን ሁኔታ በመኖሪያቸው ወይም በስራቸው ቦታ ከተወካዮቻቸው ጋር በመቀናጀት ድምፅ የሚሰባሰብበት ወይም ሌሎች በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረቱ የድምፅ አሰጣጥ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ ይችላል፡፡

15) የጠቅላላ ጉባዔ ሰብሰባ በኅብረት ሥራ ማህበራት ተወካዮች አማካኝነት በውክልና ድምፅ የሚሰጥ ቢሆንም የድምፅ አሰጣጡ የዲሞክራሲያዊ መርሆዎች በጠበቀ ሁኔታ መከናወኑን ኅብረት ሥራ ማህበራት ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

16) በማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ውስጥ የሚተላለፉ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡ ሆኖም የድምፅ አሰጣጡ እኩል በእኩል ከሆነ የጉባዔ ሰብሳቢ የሚሰጠው ድምፅ ወሳኝነት ድምፅ ይሆናል፡፡

17) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ጋር በተለያዩ ሁኔታዎች ተጣምረው የሚሰሩ አባል ያልሆኑ ግለሰቦች ድምፅ የመስጠት መብት የላቸውም፡፡

18) የጠቅላላ ጉባዔ ተወካይ በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት በማንኛውም ወቅት ወክልናው ተነስቶ በሌላ ሊተካ ይችላል፡፡

19) በኅብረት ሥራ ማህበራት መተዳደሪያ ደንብ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር በመደበኛ ወይም በአስቸኳይ ጉባዔ የሚተላለፉ ውሳኔዎች በሰብሰባው መገኘት ካለባቸው አባላት አብላጫ ድምፅ የሚወሰን ይሆናል፡፡

20) የተወካይ አባላት አመራረጥን እና የተወካይ አባላት ተግባርና ሃላፊነት በተመለከተ በኅብረት ሥራ ማህበሩ በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የሚወሰን ይሆናል፣

## ክፍል ሰባት

## ስለኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባዔ፣ የሥራ አመራር ኮሚቴ፣ ስራ አስኪያጅ እና ተቀጣሪ ባለሙያዎች

### 52. የጠቅላላ ጉባኤ አቋም

1)ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት አቋም ይኖሩታል፤

ሀ) ጠቅላላ ጉባኤ ማለት እያንዳንዱ አባል ወይም ተወካይ በግንባር ወይም በአካል የሚገኝበት ሰብሰባ ነው፣

ለ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጉዳይ ላይ ጠቅላላ ጉባኤ የሚያስተላልፈው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

ሐ) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር መደበኛ ጉባዔ ሊኖረው ይገባል፡፡ ሆኖም እንዳስፈላጊነቱ አስቸኳይ እና ልዩ የጠቅላላ ጉባዔ ሊኖረው ይችላል፡፡

መ) የጠቅላላ ጉባዔ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ከፍተኛ ስልጣኑን በከፊል ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ሆኖ የሚጠበቅበትን ክፍያ ካላጠናቀቀ በቀር በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ወይም በሥራ አመራር ኮሚቴ ምርጫ ላይ መሳተፍአይችልም።

3) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤው ከመደረጉ በፊት ባሉት አስራ አምስት ቀናት ውስጥ አዳዲስ አባላትን ማስገባት የለበትም።

## 53. የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 32 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር የሚከተሉትን በተጨማሪነት ይይዛል፤

ሀ) ያለፉውን ጊዜ የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባዔ በማድመጥ ሪፖርቱን ያፀድቃል፡፡

ለ) በስራ አመራር ኮሚቴ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያላቸው አባላት ጉዳይ በጠቅላላ ጉባዔ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያቀርባል፡፡ ሆኖም ቅሬታው የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ከመደረጉ ቢያንስ ሁለት ቀናት በፊት ለስራ አመራር ኮሚቴ ፀሐፊ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፣

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበር የአማካሪ ምክር ቤት፣ የስራ አመራር ኮሚቴ እና ቁጥጥር ኮሚቴዎችን የመምረጥ እንዲሁም ስልጣኑን ተጠቅሞ ከኃላፊነት ማንሳት መወሰን፣

መ) የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ያሉባቸውን የኢንቨስትመንትን፣ የጥሪት ክምችት እና የብድር ፍላጎት ተገቢውን ውሳኔ መስጠት፣

ሠ) አግባብ ካለው ባለስልጣን ውጭ ባሉ ኦዲተሮች ሂሳባቸውን ሲያስመረምሩ በሚደረጉ ስምምነት ሰነዶች ላይ የኦዲተሮች የስራ ኃላፊነት እና የክፍያ ሁኔታ በጠቅላላ ጉባዔ የሚፀድቅ ይሆናል፡፡ ሆኖም ስለ ኦዲተሮች የስራ ኃላፊነት እና የክፍያ ሁኔታ አሰራር በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ሊወሰን ይገባል፡፡

ረ) ከጠቅላላ ጉባዔው በኦዲት ግኝቱ እና ባልተካተቱ የሂሳብ ርዕሶች ላይ ለተነሱ ጥያቄዎች ኦዲተሩ ምላሽ ይሰጣል፣

ሰ) ከሥራ አመራር ኮሚቴ በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት በኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ አባላት በፈጠሩት ጥፋት የሚቀጡበት እና የሚሰናበቱበት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣

ሸ) አባላት፣ ቅጥር ሠራተኞች ትምህርት እና ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፣

ቀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ አሲኪያጅ ቅጥር ያፀድቃል፡፡

በ) እንደአስፈላጊነቱ ልዩ ለሆኑ ተግባራት ወይም ፕሮጀክቶች በኮሚቴ አባልነት የሚሰሩ ከጠቅላላ ጉባዔ አባላት በመምረጥ የሚያከናውኑትን ተግባር እና የጊዜ ቆይታ ይወስናል፡፡

ተ) አዳዲስ አባልትን ይቀበላል፣ ችግር ያለባቸውን ወይም በፍላጎታቸው መሰረት አግዶ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ያሰናብታል፣

ቸ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዓመታዊ በጀት፣ የንግድ ሥራ ዕቅዶች እና ስትራቴጂክ ዕቅዶችን ያፀድቃል፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ-በ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ጠቅላላ ጉባኤ ደረጃ በሚወሰኑ ጉዳዮች አስቀድሞ አባል መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በጉዳዮቹ ላይ በመወያየት ጽድቆ እንዲመጣ ማድረግ ይኖርበታል፣

3) በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን የጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር መሰረት በተላለፉ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ቅረታውን ማቅረብ ይችላል፣

4) የጠቅላላ ጉባኤ ወይም የሥራ አመራር ኮሚቴ የስብሰባ ቀን፣ ቦታ፣ ሰዓት እና አጀንዳ የሚገልጽ ግልጽ አጭር ማስታወቂያ ቢያንስ ከአስራ አምስት ቀናት በፊት ማሳወቅና መጥራት አለበት፣

## 54. <u>የስራ አመራር ኮሚቴ አባል የምርጫ መስፈርት፣ ተጠሪነት</u>

1) በኅብረት ሥራ ማበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በመተዳደሪያ ደንባቸው በሚወስኑት የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ምርጫ መስፈርት ላይ በተጨማሪነት የሚከተሉት ሊያካትት ይችላል፤

ሀ) የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል የሆነ፣

ለ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደርያ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱትን የአባልነት ግዴታዎች በብቃት የሚወጣ፣

ሐ) የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ በመስራት መወጣት የሚችል፣

መ) ሰዎችን ለመርዳት ፅኑ ፍላጎትና ተቆርቋሪነት ያለው፣

ሠ) ቀደም ሲል በምግባረ ብልሽነት ወይም በእምነት ማጉደል ወንጀል ክስ የሌለበት፣

ረ) በስነ-ምግባር ወይም በእምነት ማጉደል በክስ ላይ ያልሆነ፣

ሰ) የትምህርት ደረጃ ለመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ቢያንስ 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ ሲሆን ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ቢያንስ10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ፣

ሸ) የተማረ የሰው ሃይል በማይገኝበት ቦታ ለመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ቢያንስ ማንበብና መፃፍ የሚችል ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ፤

ቀ) የሚሰጣቸውን ትምህርትና ስልጠና ለመውሰድ ፈቃደኛ የሆኑ፣

በ) በመልካም ስነ ምግባሩ እና በታማኝነቱ በአባላት የተመሰከረለት፣

ተ) የስራ አመራር ኮሚቴ አባል ውሳኔ በመስጠት ሂደት ያለባቸውን ተጠያቂነት በአግባቡ የተሩዱ፣

ቸ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አመራር ሆኖ ለመመረጥ ቢያስን ለአንድ የሥራ ዘመን በአባልነት መቆየት ይኖርበታል፣

ነ) የሚሰጠውን ተግባር ተቀብሎ ለመተግበር ቁርጠኛ የሆነ፣

2) አባላት በማንነታቸው፣ በኢኮኖሚ አቅማቸው እና የፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት ከመመረጥ አይከለከሉም፣

3) የስራ አመራር ኮሚቴ ምርጫ የሚያከናውኑ ሦስት አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባዔ ይመረጣል፡፡

4) ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሲመሩ የነበሩ ነባር አመራር አካላት የምርጫውን ስነስርዓት እንደያከናውኑ ስልጣናቸውን ለአስመራጭ ኮሚቴ ያስረክባሉ፡፡ ሆኖም አግባብ ያለው ባለስልጣን በምርጫው ሂደት ላይ ጥርጣሬ ካለው አስመራጭ ኮሚቴውን ሊያስመርጥ ይችላል፡፡

5) ለሁለተኛ ጊዜ ተመርጠው ጊዜያቸውን የጨረሱ አመራር አካላት ዳግም መመረጥ አይችሉም፡፡ ሆኖም ግን ከአንድ ጊዜ እረፍት በኋላ ድጋም ሊመረጡ ይችላሉ፣

6) የምርጫውን ስነ-ስርዓት እንዲሳካ አግባብ ያለው ባለስልጣን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

7) ለኮሚቴ አባልነት ምርጫ የሚወዳደሩ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለመምረጥ እንዲቻል በሚፈለጉ የኮሚቴ አባላት ብዛት ላይ በተጨማሪ እንደየ ኅብረት ሥራ ማህበራቱ ተጨባጭ ሁኔታ ዕጩዎች ተጠቁመው እንዲወዳደሩ ይደረጋል፡፡

8) የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ብዛት በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪ ደንብ ውስጥ የሚወሰን ሆኖ ቁጥሩ የሚቋቋሙ የንዑሳን ኮሚቴ ዓይነትና ብዛት ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ ሆኖም ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ሊቀ-መንበር ውጭ ሌሎቹ የአመራር ኮሚቴ አባላት የንዑሳን ኮሚቴ አባላት ሰብሰቢ ሆነው ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

9) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሚመሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ቁጥር ለውሳኔ አሰጣጥ አመቺ እንዲሆን ከ5 እስከ 11 አባላት መብለጥ የለበትም፡፡ ሆኖም የሥራ አመራር ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባዔ አማካኝነት ምርጫ ሲያካሄድ ሁለት ተጠባባቂ የሥራ አመራር ኮሚቴ ተመርጠው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የኮሚቴ አባላት በሚጓደልበት ወቅት የሚተኩ ይሆናል፡፡

10) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በየዓመቱ በሚያካሂደው ጉባዔ የሥራ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ወይም የተጓደሉ የኮሚቴ አባላትን ይተካል፡፡

11) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከቀድሞ የሥራ አመራር የኮሚቴ አባላት ከተመረጡበት ከሦስተኛ የሥራ ዘመን ጀምሮ ባለው የመጀመሪያ ዓመት ቢያንስ አንድ ሦስተኛው በአዲስ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ይተካሉ፡፡

12) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 54 ንዑስ አንቀፅ 9 በተገለፀው መሠረት ከሁለተኛው የምርጫ ዘመን የመጀመሪያ ዓመት ጀምሮ በአዲስ የተመርጡ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ሳይተኩ እስከሚቀጥለው ሦስተኛው የምርጫ ዘመን በአመራርነት ሊቆዩ ይችላሉ፡፡

13) እርክክቡ እስኪፈጸም ድረስ አግባብ ያለው ባለስልጣን የባንክ አካውንቱ እንዳይንቀሳቀስ በማድረግ በተሸሩና በተመረጡ ኮሚቴ መካከል የስልጣን ርክክብ ሶስት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡ ሆኖም ነባሩና አዲስ የተመረጠው የሥራ አመራር ኮሚቴ አግባብ ያለው ባለስልጣን፣ ቅጥር ሠራተኞች እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት በታዛቢነት በተገኙበት የሥራ ርክክብ ሊያደርግ ይችላል፣

14) ነባር የኮሚቴ አመራር ለተተኪ የኮሚቴ አባላት ሥራዎች ያሉበትን ዝርዝር መረጃ የመስጠት እና ለአንድ ወር ሥራውን የማለማመድ ግዴታ አለባቸው፡፡

15) የማንኛው የሥራ አመራር ኮሚቴ የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሆኖ ጠቅላላ ጉባዔው ካመነበት ለሁለተኛ ጊዜ ሊመረጥ ይችላል፡፡ ሆኖም አንድ ሰው ከሁለት የሚርጫ ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፡፡

## 55. <u>የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) በኅብረት ሥራ ማበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 35 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ በተጨማሪነት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

ሀ) በማንኛውም ጊዜ የኅብረት ሥራ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች የኅብረት ሥራ ማህበሩን ወክሎ ይከሳል፣ ይከራከራል፣ ውሎችን ይዋዋላል:: ሆኖም የሚያደርጋቸው ውሎችና ስምምነቶች በገንዘብ የሚሆን ከሆነ በመተዳደሪያ ደንባቸው በጠቅላላ ጉባዔ ከተቀመጠው የገንዘብ ጣሪያ በላይ ሊሆን አይገባም፡፡

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሂሳብ ሰነዶች እንዲሚሉ ያደርጋል፡፡

ሐ) ማንኛውንም የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገቢዎች በማህበሩ ገቢ ደረሰኝ ብቻ መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል፣ አወጣጡን ይቆጣጠራል፣

መ) በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ የሀብትና ዕዳ መግለጫ ሪፖርት ያዳምጣል፣ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሂሳብ ጤነኛነት ያረጋግጣል፡፡

ሠ) አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም እሱ ውክልና በሰጠው የውጭ ኦዲተር አማካኝነት የኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዲመረመር ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ረ) የሥራ አመራር ኮሚቴ በኦዲት ሪፖርት ላይ በመወያየት ለጠቅላላ ጉባዔ እንዲቀርብ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

ሰ) የጠቅላላ ጉባዔ እና ኦዲተሩ ከሰጡት የሪፖርት ግብዓት በመውሰድ የቴክኒክ እና ሌሎች አስተዳደራዊ ማስተካከያዎችን ይወስዳል፣

ሸ) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 አንቀጽ 26 ንዑስ 4 ላይ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የአዲስ ወይም የዳግም የአባልነት ማመልከቻ መርምሮ ውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣

ቀ) በአባሉ ፈቃድ ከአባልነት የመሰናበት ጥያቄ ተቀብሎ ውሳኔ ይሰጣል፣ ሆኖም በጥፋት ለሚሰናበት የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ውሳኔ እንዲሰጥበት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣

በ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በተገለፀው መልኩ መብትና ግዴታቸውን በአግባቡ እየተወጡ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

ተ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ፣ የውስጠ ደንብ ሌሎች መመሪያዎችን አግባብ ባለው ባለስልጣን በተዘጋጁ ረቂቅ ሞዴል መሠረት ያዘጋጃል፣ በጠቅላላ ጉባኤ አጸድቆ ስራ ላይ ያውላል፡፡

ቸ) በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የተሰጣቸውን የተሻሻሉ መተዳደሪያ ደንብ፣ የውስጠ ደንብ እና ሌሎች እንዲመዘገቡ የሚጠየቁ ሰነዶችን አግባብ ላለው ባለስልጣን በማቅረብ ያስመዘግባል፣

ነ) አግባብ ያለው ባለስልጣን የተሸሻሉ አንቀጾችን መቀበሉንና መመዝገቡን ሲያሳውቀው ሥራ ላይ ያውላል

ኘ) ለኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚጠቅሙ አዳዲስ አሰራሮችን በማጥናት፣ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ሲጸድቅ ስራ ላይ ያውላል፡፡

አ) እንዲሸጥ የተወሰነውን ዕጣ በተያዘለት ጊዜ መሸጡን ያረጋግጣል፣ አባላት እንዲገዙ ያስተባብራል እንዲሁም ለጋራ ኢንቨስትመንት የሚውል ተጨማሪ ዕጣ በጠቅላላ ጉባዔ አስወስኖ ይሸጣል፡፡

ወ) የተሸጠው ተጨማሪ ዕጣ ለታሰበለት ዓላማ እና ለአባላት ተጠቃሚነት ሥራ ላይ ማዋሉን ያረጋግጣል፡፡

ከ) የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት የስራ አስኪያጅ አስፈላጊነት ላይ ስምምነት ከደረሱ የጠቅላላ ጉባዔው አስፈላጊውን በጀት ሲፈቀድለት አወዳድሮ ይቀጥራል፤ ያሰናብታል፡፡

ዘ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና በውሰጠ ደንብ መሰረት ይበደራል፣ ለአባላት ያሰራጫል፣ ብድርንም በወቅቱ እንዲመለስ ያደርጋል፡፡

ዥ) ሥራ አስኪያጅ እና የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ሥራቸውን በኃላፊነት እና በተጠያቂነት መወጣታቸውን ይከታተላል፣

ጠ) በመተዳደሪያ ደንብ፣ በውስጠ ደንብ፣ በሌሎች መመሪያዎች እና አሰራሮች ላይ ለአባላት እና ለአመራር አካላት ግንዛቤ እንዲፈጠር ትምህርት እና ስልጠና ይሰጣል፡፡

ጨ) የአባላት ዕጣ እና ጥቅም ወይም ዕዳ ወራሽነታቸው በህግ ለተረጋገጠላቸው የአባል ወራሾች ያስተላልፋል፣

የ) በኅብረት ሥራ ማህበሩና በአባላት መካከል አለመግባባት ሲኖር ወደ ሽምግልና ዳኝነት ከመሄዱ በፊት የሚያግባባ የመፍትሄ ሀሳብ ያፈላልጋል፣

ደ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ በአዋጅ፣ በመተዳደርያ ደንብ፣ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ውጭ በሚሰሩት ሥራ ምክንያት በኅብረት ሥራ ማህበሩ ላይ በሚደርስ ኪሳራ ወይም ጥፋት ወይም ጉድለት በጋራ ወይም በግል ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

ጀ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ ላይ በሚደርስ ጉዳት፣ ኪሳራ እና ጥፋት ያደረሱ አካላት ለህግ ያቀርባል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

ገ) አግባብ ካለው ባለስልጣን ውጭ ባሉ ኦዲተሮች ሂሳባቸውን ሲያስመረምሩ በሚደረጉ ስምምነት ሰነዶች ላይ የኦዲተሮች የስራ ኃላፊነት እና የክፍያ ሁኔታ ይወስናል፣

ጰ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ በመተዳደሪ ደንቡ መሰረት ንብረት ለማፍራት ወይም ንብረት ለማስወገድ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያጸድቃል፣

ፀ) ሌሎች በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ-ጠ) ያሉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ ባህሪውን መሰረት በማድረግ ተጨማሪ ተግባርና ሃላፊነቱን በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ሊያስቀምጥ ይችላል፣

3) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ-ጠ) ድንጋጌ እና በራሱ መተዳደሪ ደንብ ከተቀመጠው ተግባርና ሃላፊነት ውጭ መስራት አይችልም፣

## 56. የሥራ አመራር ኮሚቴ ሊቀ መንበር ተግባርና ኃላፊነት

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሊቀ-መንበር በጠቅላላ ጉባዔ አባላት በቀጥታ የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለጠቅላላ ጉባኤ እና ለሥራ አመራር ኮሚቴ ነው፡፡

2) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 35 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አመራር ኮሚቴው ሊቀ-መንበር የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፣

ሀ) የጠቅላላ ጉባኤ እና የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ ስብሰባን በኃላፊነት ይመራል፣

ለ) የሂሳብ ሰነዶች እና ቼክ ላይ በጣምራ ይፈርማል፣

ሐ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል ወይም መልስ ይሰጣል፣

መ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም ውል ይዋዋላል፣

ሠ) ሌሎች በመተዳደሪያ ደንብ የሚወሰኑ ተግባርና ኃላፊነት እና ከጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፣

## 57. የሥራ አመራር ኮሚቴ ምክትል ሊቀ መንበር ተግባርና ኃላፊነት

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ምክትል ሊቀ-መንበር በጠቅላላ ጉባዔ አባላት የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ነው፣

2) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 35 እና በዚህ አንቀጽአንቀፅ 46 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አመራር ኮሚቴው ሊቀ-መንበር የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፣

ሀ) ሊቀ-መንበሩ በማይኖርበት ጊዜ ሊቀ-መንበሩን ተክቶ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ስራ ይመራል፡፡

ለ) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል በተጨማሪ በመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት የአንድ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሰቢ ሆኖ ኃላፊነቱን ይወጣል፡፡

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጠውን ሌሎች ሥራዎች ደርቦ ይሰራል፣

## 58. <u>የሥራ አመራር ኮሚቴ ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ፀሐፊ በጠቅላላ ጉባዔ አባላት የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ነው፣

2) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ፀሐፊ በጠቅላላ ጉባዔ አባላት የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

ሀ) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ሊቀመንበር ጋር በመመካከር የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣ ከሌሎች የኮሚቴ አባላቶችም አጀንዳዎችን ይሰበሳባል፣

ለ) የስብሰባው ጥሪዎችንና አጀንዳዎች ለአባላት ይልካል፣ መድረሱን ያረጋግጣል፣

ሐ) የጠቅላላ ጉባኤ እና የሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፤ ያዘጋጃል፣

መ) የተለያዩ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የጽህፈት ሥራዎችን ያከናውናል፣

ሠ) የቅጥር ሰራተኞች በሌላቸው የኅብረት ሥራ ማህበሩን ማህተም፣ ቃለ-ጉባኤ፣ መዛግብትና ሰነዶችን በአግባቡ ይይዛል፤ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ጽ/ቤትና ቢሮ ያደራጃል፣

ረ) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል በተጨማሪ በመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት የአንድ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሰቢ ሆኖ ኃላፊነቱን ይወጣል፣

ሰ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጠውን ሌሎች ሥራዎች ደርቦ ይሰራል፡፡

## 59. <u>የሥራ አመራር ኮሚቴ ገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ገንዘብ ያዥ በጠቅላላ ጉባዔ አባላት የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ነው፣

2) ገንዘብ ያዥ በጠቅላላ ጉባዔ አባላት የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

ሀ) የቅጥር ሰራተኞች በሌላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ገቢዎችን በገቢ ደረሰኝ ይሰበስባል፣

ለ) የቅጥር ሰራተኞች በሌላቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት ለሥራ የሚያስፈልግ ወጪዎችን በሊቀመንበሩ በደብዳቤ ሲታዘዝና በማህበሩ የወጪ ማዘዣ ሰነድ ሲጸድቅለት ይከፍላል፣

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ገንዘብ ያዥ የኮሚቴ አባል የተቀጣሪ ገንዘብ ያዥ የየዕለቱን ሥራ በቅርበት በተሰጠው የሥራ ድርሻ ዝርዝር መሰረት መስራቱን ይከታተላል፡፡

መ) ኅብረት ሥራ ማህበር ማንኛውንም የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገንዘብና ሰነዶችን ይጠብቃል፣

ሠ) በወጪና በገቢ ሂደት ወቅት የወጪና የገቢ ደጋፊ ሰነዶች መኖራቸውን ያረጋግጣል፣

ረ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ አሰራር በመተዳደሪያ ደንብ፣ በውስጠ ደንብ እና በሌሎች መመሪያዎች መሰረት መከናወኑን የመፈጸም ግዴታ አለበት፣

ሰ) የቅጥር ሰራተኞች በሌላቸው የኅብረት ሥራ ማህበሩን በሂሳብ ሰነዶች፣ በባንክ ቼኮች ላይ ከሊቀመንበሩ ጋር በጋራ ይፈርማል፣

ሸ) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል በተጨማሪ በመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት የአንድ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሰቢ ሆኖ ኃላፊነቱን ይወጣል፣

ቀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጠውን ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎችን ያከናውናል፣

3) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ገንዘብ ያዥ ሆነው የሚመረጡት በገንዘብ አያያዝ የተሻለ ልምድና ተሞክሮ እንዲሁም በስነምግባራቸው በአባላት ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፣

## 60. <u>የሂሳብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) ቅጥር ሂሳብ ባለሙያ በሌለበት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ ሹም በጠቅላላ ጉባዔ አባላት የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል፤

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሂሳብ በትክክል ያዘጋጃል፣ ይከታተላል፣

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት፣ ብድር፣ ካፒታል፣ ገቢና ወጪ ሙሉ በሙሉ መዝግቦ ያስቀምጣል፣

ሐ) የሂሳብ መዝገቦችና ሌሎች የሂሳብ ሰነዶች ይጠብቃል፣

መ) ማንኛውም ወጪ በትክክል መታዘዙን ያረጋግጣል፣

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የፋይናንስ ሪፖርት ወርሀዊ የሂሳብ ሪፖርት በተዘጋ ከ3 እስከ 5 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፣

ረ) ከገንዘብ ያዥ ጋር በቅርበት በመስራት የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገንዘብ በአግባቡ እንዲጠበቅ ያደርጋል፣

ሰ) ከሊቀመንበሩ እና ከገንዘብ ያዥ ጋር በመሆን በጣምራ በሂሳብ ሰነዶችና በቼክ ላይ ይፈርማል፣

ሸ) የተቀጣሪ ሂሳብ ሰራተኛ የየዕለቱን ሥራ በተሰጠው ዝርዝር የሥራ ድርሻ መሰረት መስራቱን ይከታተላል፡፡

ቀ) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል በተጨማሪ በመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት የአንድ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሰቢ ሆኖ ኃላፊነቱን ይወጣል፣

በ) የሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

2) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ ሹም ሆነው የሚመረጡት በሂሳብ አያያዝ የተሻለ ልምድና ተሞክሮ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፣

3) የኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ ሰነዶችን እና ሌሎች መዛግብትን አግባብ ያለው ባለስልጠና በሚመራው መንገድ መያዝ አለበት፣

4) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ ከተዘጋ በኋላ በተቻለ ፍጥነት የሂሳብ መዛግብት፣ ትርፍ እና ኪሳራ ሂሳብ፣ ሀብትና ዕዳ እና ሌሎች የሂሳብ መግለጫዎችን በየጊዜው ማዘጋጀት አለበት።

## 61. <u>ሌሎች የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት</u>

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሌሎች የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ ሲሆን ተጠሪነታቸው ለኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ነው፣

2) በማንኛውም የሥራ አመራር ኮሚቴ ተግባራት እና ውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ከሌሎች የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት በእኩል የመሳተፍ ድምፅ አላቸው፡፡

3) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል በተጨማሪ በመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት የአንድ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሰቢ ሆኖ ኃላፊነቱን ይወጣል፡፡

4) በሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 62. <u>የቁጥጥር ኮሚቴ አባል ምርጫ መስፈርት፣ ተጠሪነት</u>

1) በኅብረት ሥራ ማበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 36 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ምርጫ መስፈርት፣ ተጠሪነት እና የሥራ ዘመን ላይ በተጨማሪነት የሚከተሉት ያካትታል፤

ሀ) የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ለ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደርያ ደንብ ውሰጥ የተጠቀሱትን የአባልነት ግዴታዎች በብቃት የሚወጣ፣

ሐ) የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ተግባብቶ እና ተባብሮ በመስራት መወጣት የሚችል፣

መ) መልካም ስነ-ምግባርና ተቆርቋሪነት ያለው፣

ሠ) ቀደም ሲል በምግባረ ብልሽነት ወይም በእምነት ማጉደል ወንጀል ክስ የሌለበት፣

2) በመተዳደሪያ ደንባቸው ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ የሆነ የቁጥጥር ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

3) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር 3 ወይም 5 አባላት ያሉት የቁጥጥር ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

4) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከኃላፊነታቸው የሚለቁ አባላትን የሚተካ ተጠባባቂ አንድ የኮሚቴ አባል በጠቅላላ ጉባዔ ማስመረጥ ይቻላል፡፡

5) የቁጥጥር ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ፀሐፊና አባል ይኖሩታል፣

## 63. <u>የቁጥጥር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) በኅብረት ሥራ ማበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 37 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የቁጥጥር ኮሚቴ በተጨማሪነት የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ያካትታል፤

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች በቁጥጥር ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ በአጀንዳ መልክ በማንሳት ጉዳዩን ይመረምራል፤ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የውሳኔ ሃሳብ በቃል ወይም በጽሁፍ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያሳውቃል፡፡

ለ) ስራ አስኪያጅ እና የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ሥራቸውን በኃላፊነት እና በተጠያቂነት መወጣታቸውን ይከታተላል፣

ሐ) የሥራ አመራር ኮሚቴ ከተለያዩ አካላት ጋር የሚያደርጋቸውን ውሎችና ስምምነቶች በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔና በመተዳደሪያ ደንብ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

2) ተዓማኒና ትክክለኛ ሂሳቦች እና የህብረት ሥራ ማህበሩ ንብረቶች እና እዳዎች ትክክለኛ መዝገብ እንዲይዝ ወይም እንዲቀመጥ ማድረግ;

## 64. <u>የኅብረት ሥራ ማህበር የቁጥጥር ኮሚቴ ሰብሳቢ ተግባር እና ኃላፊነት</u>

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የቁጥጥር ኮሚቴ ሰብሳቢ በጠቅላላ ጉባዔ አባላት በቀጥታ የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለጠቅላላ ጉባኤ እና ለቁጥጥር ኮሚቴ ነው፣

2) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 37 እና በዚህ አንቀጽአንቀፅ 53 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቁጥጥር ኮሚቴ ሰብሳቢ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

ሀ) በስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት ያለድምፅ የውሳኔ ሃሳቦችን ይሰጣል፣

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች በስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ አጀንዳ ሆነው እንዲነሱ ጥረት ያደርጋል፡፡

ሐ) በስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ የሚያነሳቸው ሃሳቦች በቃለ-ጉባኤ መዝገብ ላይ ይመዘገባሉ፣

መ) በስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ የተነሱ አጀንዳዎች እና የተደረሰባቸውን ውሳኔዎች ሪፖርት በቁጥጥር ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባዎች ላይ ለሌሎች የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ያቀርባል፣

ሠ) የቁጥጥር ኮሚቴ ክትትል ሊደረግባቸው የሚገባቸውን ሥራዎች ፕሮግራም በማውጣት ክትትልና ቁጥጥር ያደረጋል፤ የታዩ ክፍተቶች ለስራ አመራር ኮሚቴ በቃልና በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

ረ) ሌሎች በጠቅላላ ጉባዔ ክትትል እንዲያደርግ የተሰጠውን ተጨማሪ ሥራ ያከናውናል፡፡

## 65. ስለሌሎች የንዑሳን ኮሚቴ አባላት ምርጫ መስፈርት፣ ተጠሪነት

1) በኅብረት ሥራ ማበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 38 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የንዑሳን ኮሚቴዎች በተጨማሪነት የሚከተሉትን መስፈርት ያካትታል፤

ሀ) የንዑሳን ኮሚቴዎች አባላት የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል የሆኑና የአባልነት ግዴታቸውን የሚወጡ፣

ለ) የተሰጠውን ኃላፊነት ተግባብቶ እና ተባብሮ ለመስራት ዝግጁ የሆነ፣

ሐ) ሰዎችን ለመርዳት ፅኑ ፍላጎትና መልካም ስነ-ምግባር ያለው፣

መ) በተመረጠበት የንዑስ ኮሚቴ ውስጥ በቂ ግንዛቤና ልምድ ያለው፣

ሠ) ቢያንስ ማንበብና መፃፍ የሚችል፣

2) የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያቋቁሟቸው ንዑሳን ኮሚቴዎች እንደየኅብረት ሥራ ማህበራቱ ዓይነትና ባህሪያት እንዲሁም በመተዳደሪያ ደንባቸው በሚወስኑት መሠረት ይሆናል፡፡
3) በማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ሊቀ-መንበሩን ሳይጨምር የእያንዳንዱ የንዑሳን ኮሚቴ ሰብሳቢዎች ይሆናሉ፡፡
4) ማንኛውም የንዑሳን ኮሚቴ አባላት በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚወስነው መሠረት ቁጥራቸው ከ 3 ያልበለጡ የተለያዩ ተግባርና ኃላፊነት ያላቸው ንዑሳን ኮሚቴዎች ይኖሩታል፣
5) እያንዳንዱ የንዑሳን ኮሚቴዎች ሰብሳቢ፣ ፀሐፊና አባል ይኖሩታል፣
6) በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከኃላፊነታቸው የሚለቁ አባላትን የሚተካ ተጠባባቂ አንድ የኮሚቴ አባል በጠቅላላ ጉባዔ ማስመረጥ ይቻላል፡፡
7) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የንዑስ ኮሚቴ አባላት ሲጓደሉ በተጠባባቂነት የተመረጠ ማንኛውም ግለሰብ ሊታካ የሚችለው ለአንድ የምርጫ ዘመን ብቻ ይሆናል፡፡

## 66. የንዑሳን ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

1) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የንዑሳን ኮሚቴዎች በመተዳደሪያ ደንባቸው የሚወስኑት እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፤

ሀ) በመተዳደሪያ ደንብና በውስጠ ደንብ ውስጥ ለንዑስ ኮሚቴው የተሠጡትን ተግባርና ኃላፊነት ያከናውናል፡፡

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የንዑስ ኮሚቴ የሥራ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ለስራ አመራር ኮሚቴ ያጸድቃል፡፡

ሐ) በዕቅዱ መሠረት የሥራው መርሃ ግብር እና የመደበኛ ስብሰባ ጊዜው ይወስናል፤ ለስራ አመራር ኮሚቴ ያሳውቃል፡፡

መ) በንዑስ ኮሚቴው የሥራ ድርሻ ላይ የተሰጡ የሥራ አመራር ኮሚቴ አስተያየቶችን እና የሥራ መመሪያዎችን በመወያየት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ሠ) የንዑስ ኮሚቴውን የሥራ እንቅስቃሴና ያጋጠሙ ማነቆዎችን ለስራ አመራር ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣

ረ) በንዑስ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ የሚነሱ ሃሳቦች በንዑስ ኮሚቴው ቃለ-ጉባኤ መዝገብ ላይ ይመዘገባል፣

ሰ) ሌሎች በስራ አመራር ኮሚቴ አባላት የሚሰጡ ስራዎችን በተጨማሪነት ያከናውናል፡፡

2) እንደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ ባህሪና የሥራ ስፋት የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት እያንንዳቸው የንዑሳን ኮሚቴዎችን በሰብሳቢነት ይመራሉ፣

## 67. የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቁጥጥር ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ አባላትን ከኃላፊነት ስለመሰናበት

1) ማንኛውም የኮሚቴ ተመራጭ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥመው ከኮሚቴ አባልነት ለመሰናበት ከፈለገ ለሥራ አመራር ወይም ቁጥጥር ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፣
2) የሥራ አመራር ወይም የቁጥጥር ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ ጥያቄው በቀረበ በ30 ቀናት ውስጥ በጹሁፍ መልስ መሰጠት ይኖርበታል፣
3) ማንኛውም የኮሚቴ ተመራጭ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ደንብ የሚጻረር ደርጊት ከፈጸመ ተጠሪ በሆነበት በሥራ አመራር ወይም በቁጥጥር ኮሚቴ ወይም በንዑስ ኮሚቴ ከሥራው ታግዶ ለጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ ውሳኔ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡
4) የተጓደሉ የኮሚቴ አባል የተጓደለበትን ምክንያት እና ቀድሞ በጠቅላላ ጉባኤ ምርጫ በተጠባባቂነት ከተመረጡ የኮሚቴ አባላት ይተካል፡፡
5) በተተኪነት ሲሰሩ የቆዩትን የኮሚቴ አባላት ወይም ቀድሞ ተተኪ የሌለውና አዲስ ሊመረጥ የሚገባው ከሆነ በዓመታዊ የመደበኛ ስብሰባ የሥራ ሪፖርት ይቀርባል አዲስ የኮሚቴ አባል እንዲመረጥ ያደርጋል፡፡
6) አንድ የኮሚቴ አባል ካለ በቂ ምክንያት ለሦስት ተከታታይ ጊዜ ካልተገኘ ከኮሚቴ አባልነቱ በራሱ ፈቃድ እንደተሰናበተ ተቆጥሮ በቦታው በተጠባባቂነት ቀድሞ በጠቅላላ ጉባኤ በተመረጡ አባላት የሚተካ ይሆናል፡፡ የጠቅላላ ጉባኤ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡
7) የተጓደሉ የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቁጥጥር ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ ከተጠባባቂ አባለት ተክቶ ማሰራት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም የሚተካ ሰው የማይኖር ሆኖ ሲገኝ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ሳይጠበቅ ከአባላት ውስጥ የተሻለ እንቅስቃሴ ያለውን በጊዜያዊነት ወክሎ ሊያሰራ ይችላል፡፡ ሆኖም ከአንድ አመት በላይ ተወክሎ መስራት አይቻልም፡፡
8) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከአባላት መካከል ስለተወከለው አባል የጠቅላላ ጉባኤ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡ ስለ አወካከሉ በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ የሚገለጽ ይሆናል፣

## 68. የስራ አስኪያጅ አቀጣጠር፣ ተግባርና ኃላፊነት

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር አንቀፅ 39 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ስራ አስኪያጅ በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

ሀ) በጠቅላላ ጉባዔ እና የሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጠውን አመራር መሠረት በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ረቂቅ ስትራቴጂክ ዕቅድና በጀት እንዲሁም ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፡፡

ለ) ዕቅዱ በጠቅላላ ጉባዔ ሲጸድቅ በተያዘለት ጊዜና በጀት ይፈፅማል፡፡ ያስፈፅማል፡፡

ሐ) የሚያከናውናቸው ተግባራት በመተዳደሪያ ደንብ እና በስራ ዝርዝር ውስጥ እንዲካተት ያደርጋል፣

መ) በጠቅላላ ጉባዔ በጀት ሲፈቀድለት በቂ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች ይቀጥራል፣

ሠ) የቀጠራቸው ባለሙያዎች በሚያዘጋጀው የስራ ዝርዝር መሠረት ኃላፊታቸውን እየተወጡ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ረ) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ተልዕኮ አንፃር የሥነ-ምግባር ባህሪያት መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

ሰ) የስራ አመራር ኮሚቴ ሰብሰባ ላይ ያለ ድምፅ በመሳተፍ ሙያዊ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

ሸ) በኅብረት ሥራ ማህበር አባላት መካከል የጥቅም ግጭት ሊያስነሱ የሚችሉ ጉዳዮች አሰራር እንዲዘረጋ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣

ቀ) ወቅታዊ፣ አስተማማኝና ተከታታይነት ያለው መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

በ) የጠቅላላ ጉባዔ ላይ የቀረቡ የውስጥ እና የውጭ ኦዲት ሪፖርት አስተያየቶችን በማሰባሰብ ቀጣይ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው ያደርጋል፡፡

ተ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ካልሆኑ ሌሎች አካላት ጋር የሚያደርጋቸውን የሥራ እንቅስቃሴ በተለየ ሁኔታ መረጃ መያዝ ይጠበቅበታል፣

ቸ) የአባላትን የባለቤትነት ስሜት የሚያሳድጉ ተግባራትን አቅዶ መስራት ይኖርበታል፣

ነ) የተሻለ ተሳትፎ ላደረጉ አባላት ማበረታቻ የሚያገኙበትን አሰራር እንዲዘረጉ ሃሳቡን ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፡፡ ሲፈቀድ ሥራ ላይ ያውላል፡፡

ኘ) የስትራቴጂካዊ የተግባራት አፈፃፀም፣ የፋይናንስ ቁመና እና አስተዳደራዊ ክንውኖች ተአማኒነቱን በጠበቀ ሁኔታ በፅሁፍ ለአባላት እንዲደርስ ያደርጋል፣

አ) ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለአባላት ገለፃ ያደርጋል፣

ከ) የውስጥ ቁጥጥሩ እንዲሻሻል የሚረዱ መረጃዎችን ለቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በማቅረብ የሚታዩ የአሰራር ክፍተቶች መፍታት እንዲቻል ተገቢውን እገዛ ይሰጣል፡፡

ወ) ጥራቱን የጠበቀ የሥራ ሪፖርት እና የፋይናንስ መግለጫ ለሥራ አመራር ኮሚቴ፣ ለቁጥጥር ኮሚቴና አግባብ ላለው ባለስልጣን በጥራት፣ በጊዜ፣ በመጠን ያቀርባል፡፡

ዘ) የማህበሩን የዕለት ተዕለት ሥራ የሚያንቀሳቅሱ የሥራ ክፍል ኃላፊዎች እና ተቀጣሪ ባለሙያዎች እንደ አስፈላጊነቱ አጥንቶ ያቀርባል፤ ሲፈቀድ በሠራተኛ አስተዳደር መመሪያ መሠረት ቅጥር ይፈፅማል፡፡

ዠ) ለሥራ ክፍል ኃላፊዎች እና ቅጥር ባለሙያዎች ቴክኒካዊ ብቃቱን ተጠቅሞ የዕለት ተዕለት ተግባራትን መሠረት ዝርዝር የስራ ድርሻ ያወጣል፤ አፈጻጸማቸውንም በየጊዜው ይገመግማል ወይም እንዲገመገም ያደርጋል፣

2) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የምክትል ስራ አስኪያጅ፣ የክፍል ኃላፊዎች እንዲሁም ሌሎች የቅጥር ሠራተኞች ወይም ባለሙያዎች አቀጣጠር፣ ምልመላ፣ ተፈላጊ የትምህርት ዝግጅት፣ የትምህርት ደረጃ፣ ተፈላጊ የስራ ልምድ፣ ሥልጣንና ተግባራቸው እንዲሁም የሥራ ዘመናቸውን በሚወጣው የሰው ኃይል አስተዳደርና ልማት መመሪያ መሠረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፡፡

3) በኅብረት ሥራ ማህበሩ በሰጠው ልዩ ውሳኔ ካልሆነ በስተቀር የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ አባል ወይም የቅጥር ሰራተኛ የቅርብ ዘመድ የሆነ ሰው በማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ውስጥ አይቀጠርም ወይም አይሾምም፣

## 69. <u>የሥራ ክፍል ኃላፊዎች እና ቅጥር ሠራተኞች አቀጣጠርና አስተዳደር</u>

የኅብረት ሥራ ማህበራት የቅጥር ሠራተኞች አቀጣጠርና አስተዳደር በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሰው ኃይል አስተዳደርና ልማት መመሪያ መሰረት የሚፈፀም ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1)የቅጥር ሠራተኞች የኅብረት ሥራ ማህበሩን ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ስራዎች ይሰራሉ፣

2)የተለያየ ሙያና ደረጃ ያላቸው የቅጥር ሰራተኞች ያላቸውን ክህሎትና እውቀት አሟጦ መጠቀም፤

3)የአባላት ቁጥር እንዲያድግ ተግቶ መስራት፣ የተሸጡ እጣዎች በወቅቱ እንዲያልቁ መስራት፣

4)አባላት የውስጥ የካፒታል አቅም በራሳቸው በአባላት እንዲያድግ ማድረግ፣

5)የገበያ መረጃዎችን በመፈላለግና በሚገባ በማደራጀት ለኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ተደራሽ ማድረግ፣

6)የቅጥር ሰራተኞች የኅብረት ሥራ ማህበሩ መረጃ በሚገባ በመያዝ አገልግሎት መስጠት፣

7)የኅብረት ሥራ ማህበሩ በዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ በመጠቀም ሂሳብ በየእለቱ መመዝገብ፣ በየወሩ መዝጋትና በሚገባ በመያዝ ለኦዲት ዝግጁ ማድረግ፣

8)ለአባላት ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ በማሳደግ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፣

9)ሁሉንም አባላት ባለቤትንተ በመቀበል በእኩል በማየትና ፍትሃዊ የሆነ አገልግሎት መስጠት፣

10) የኅብረት ሥራ ህግና የተለያዩ የውስጥ አሠራሮችን ጠንቅቆ በማወቅና አክብሮ መስራት፣

11) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዓላማ፣ የአባላትን ፍላጎት እንዲሁም የአመራሩን ውሳኔዎች በአግባቡ በመረዳትና የቡድን ስሜት ፈጥሮ መስራት፣

12) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴዎች በተመለከተ አመራር አካሉ፣ አስፈፃሚና ባለድርሻ አካላት አስፈላጊውን ውሳኔ፣ ድጋፍና ዕገዛ መስጠት እንዲችሉ ሪፖርትና መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግ፤

13) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሃብትና ንብረትን በአግባቡ መጠበቅ፣ መረጃዎችን አደራጅቶ መያዝና ከማህበሩ ዓላማ ውጪ ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል ማድረግ፣

14) የአባላት የተሳትፎና የተጠቃሚነት ድርሻቸው እንዲያድግ ከአመራር አከላት ጋር በመሆን ጠንክሮ መስራት፤

15) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ዕድገትና የአባላት ተጠቃሚነት ዕድገት ተጣጥሞ እንዲሄድ ሀላፊነታቸውን መወጣት፤

16) የኅብረት ሥራ ማህበር አመራር አካላትን ባለቤትነታቸውንና የበላይ ተቆጣጣሪነታቸውንና ውሳኔ ሰጭነታቸውን ዕውቅና በመስጠት በሙያ መደገፍ፤

17) የኅብረት ሥራ ማህበር ሥራ አስኪያጆች ለቅጥር ሠራተኞች የሥራ የሃላፊነትና ተጠያቂነትን በግልፅ ለይቶ በመስጠት ማሰራት፤

## ክፍል ስምንት

## የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት፣ አሰራር ማሻሻል እና በደረጃ በመለየት ማዘመን

### 70. ስለኅብረት ሥራ ማህበራት ድርጅታዊ መዋቅር፤

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት በጥናት ላይ በመመስረት ከእድገታቸው፣ ከአባላት፣ ለመንግስት፣ ከባለድርሸ አካላት ፍላጎት አንፃር እና ከጊዜው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት መዋቅራዊ አደረጃጃታቸውን ሊዘረጉ ይችላሉ፡፡

2) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር መዋቅራዊ አደረጃጃት የተቋቋመለትን ዓላማና ተግባር ለማሳካት የሚያስችልና በጠቅላላ ጉባዔ አባላት አብላጫ ድምፅ የጸደቀ መሆን ይኖርበታል፡፡

3) መዚህ መመሪያ መሰረት ሥራ ላይ የሚውለው የኅብረት ሥራ ማህበሩ ድርጅታዊ መዋቅር በየደረጃው ያሉ ኮሚቴዎችንና ለሥራው የሚያስፈልጉ ባለሙያዎችን አጠናቅሮ የያዘ፣ የተጠሪነት እርከኖችንም ከላይ ወደ ታች ወይም ወደጎን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል፡፡

4) የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደሚሰማሩበት የሥራ መስክ ወይም አገልግሎት ወይም እንደየዕድገት ደረጃቸው መሰረት ድርጅታዊ መዋቅራቸውን አስፈላጊነቱ በየጊዜው እየታየ ሊያሻሽሉ ይችላሉ፡፡

5) የኅብረት ሥራ ማህበራት ተልኳቸውን በማሳካት የሚጠበቅባቸውን ሁሉ አቀፍ ውጤት በሚፈለገው ደረጃ ማሳካት እንዲችሉ መዋቅራዊ አደረጃጀታቸው፤

ሀ) የቢዝነስ እውቀትና ክህሎትን መሰረት ያደረገ፣

ለ) የተሰማሩበተን የስራ መስክ የስራ ፍሰት እና የአባላትን እና የባለድርሻ አካላትን ፍላጎት ማዕከል ያደረገ፣

ሐ) የሙያ ልህቀትን፣ እውቀትና ክህሎትን ከውጤት ጋር ያስተሳሰረ እና ስኬትን መሰረት ያደረገ፣

መ) የአመራር አካላትን የመምራት ሚና እና ባለቤትነት የሚያረጋግጥ፣

ሠ) ከቅጥር ሰራተኞች ጋር በቅርበት እየተገናኙ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ስኬት የሚያስመዘግብ፣

6) የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚኖራቸው አደረጃጀት ያልተንዛዛ መዋቅራዊ ሰንሰለት ኖሮት የሁሉንም አካላት ፈጠራ እና የዕውቀት ሽግግር የሚያበረታታ መሆን አለበት፡፡

7) የኅብረት ሥራ ማህበራት መዋቅራዊ አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት፣ ተጠያቂነት እና የመወሰን ስልጣንን ለአመራር አካላትና ለቅጥር ሠራተኞች እንደአግባቡ የሚሰጥ መሆን አለበት፣

8) መዋቅራዊ አደረጃጀቱ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተወዳዳሪና አርአያ እንዲሆኑ ተግባሮቻቸውን ብቃትና ክህሎት ባለው የተማረ የሰው ኃይልና አመራር መምራት አለባቸው፣

9) መዋቅራዊ አደረጃጀቱ ያለውን የሥራ ዝርዝር ከሚፈልገው የብቃት ክህሎት፣ ከስራዎች ውስብስብነት እና ካለው የትምህርት ዝግጅት ጋር በማጣጣም የኅብረት ሥራ ማህበራትን ደረጃ የሚመጥን የሰው ሃይል ማደራጀት ይችላሉ፣

10) የኅብረት ሥራ ማህበራት መዋቅራዊ አደረጃጃታቸውን ምቹ እና ሳቢ አድርገው በማዘመን የሚታዩ የመፈፀምና የማስፈፀም የአቅም ማነቆዎችን መፍታት ይኖርበታል፣

11) መዋቅራዊ አደረጃጀቱ ተልዕኮ ሊሸከሙ የሚችሉ በቂ ችሎታ፣ ልምድ እና የሥራ ላይ ተነሳሽነት ያላቸውን ባለሙያዎች መሳብና ማቆየት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፣

12) ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጧቸውን የኢንቨስትመንት፣ የሜካናይዜሽን፣ አግሮ-ኢንዱስትሪ  እና የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን፣ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች የሚመሩ እና የሚያስተዳድሩ እንዲሁም የተለያዩ ጥናቶችን የሚያካሄዱ አደረጃጀቶች መፈጠር ይኖርበታል፡፡

## 71. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ስለማሻሻል፤</u>

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ተልዕኮ ለማሳከት እንዲቻል የአደረጃጀት ማሻሻያው ትኩረት የሚያደርገው፤

ሀ) በተግባራትና በፈጻሚዎች መካከል ጠንካራ ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሰራር መፍጠር የሚያስችል ተቋማዊ አደረጃጀት መዘርጋት፣

ለ) በትንሽ የሰው ኃይል ውጤታማ እና እርስ በርስ የሚመጋገቡ ተግባራትን ማከናወን የሚያስችል አሰራርን መከተል፣

ሐ) የሰራተኞችን የስራ ክህሎት በአግባቡ በመጠቀም ጥራትና ውጤታማነትን የሚያጎለብት ዲፓርትመንትን መሰረት ያደረገ ዘዴን መጠቀም፣

መ) የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት ውስንነት ያለባቸውን ድርጅታዊ መዋቅሮች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማሻሻል፣

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለዘረጋቸው ድርጃታዊ መዋቅሮች የሚያስፈልጉ ተግባርና ኃላፊነቶችን ለይቶ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 72. የኅብረት ሥራ ማህበራት የአሰራር ስርዓት ስለማሻሻል፤

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ አንፃር ያሉ አሰራሮች ላይ የታዩ ችግሮችን በጥናት ፈትሾ በአዳዲስ ዘመናዊ አሰራሮች ማሻሻል ይኖርበታል፡፡
2) የኅብረት ሥራ ማህበራት መርህና ተልዕኮን መሰረት ያደረገ፣ ተጨባጭ ውጤትን የሚያሳካ፣ የተሻሉ መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ውስጠ ደንቦች፣ ማኑዋሎችን በማሻሻል ስራ ላይ ማዋል ይኖርበታል፡፡
3) ጤናማ ኅብረት ሥራ ማህበራትን መፍጠር የሚያስችሉ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን በጥናት በመለየት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡
4) የስራ ክፍሎች፣ ቡድኖች እና ሠራተኞች እርስ በርስ የሚናበቡ፣ የሚቀናጁ፣ መማማርና የጋራ ዕድገትና ተጠቃሚነትን መርህ እንዲኅሎብት የሚያደረጉ የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት ይኖርበታል፣
5) አባላት የሚፈልጉትን የተለያዩ የኢንቨስትመንት፣ የሜካናይዜሽን፣ አግሮ-ኢንዱስትሪ እና የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን በስፋትና በጥራት ተደራሽ ለማድረግ የሚስፈልጉ የአሰራር ስርዓቶችን በመፈተሽ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 73. የኅብረት ሥራ ማህበራት የሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት ስለማሻሻል፤

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባር የቢዝነስ እውቀትን ከኅብረት ሥራ ጽንሰ-ሃብና ልዩ ባህሪ ጋር አጣምረው በያዙ፣ የተሻለ የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ ባላቸው እና ተወዳዳሪ በሆኑ ባለሙያዎች /ፕሮፌሽናልስ/ መተግብር አለበት፡፡
2) የኅብረት ሥራ ማህበራት ያላቸውን አቅም መሰረት በማድረግ ሠራተኛን ለማቆየትና በስራ ላይ ለማትጋት የሚያግዝ ግልፅ የክፍያ እና የማበረታቻ አሰራር ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

## 74. የኅብረት ሥራ ማህበራትን በደረጃ መለየት

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት ባላቸው ተልዕኮ እና በሚያከናውኑት ተግባራት መሰረት የተሻለ አገልግሎት እና ትኩረት ማግኘት እንዲችል አግባብ ያላው ባለስልጣን በሚያዘጋጀው መስፈርት መሰረት በደረጃ ይለያሉ፡፡
2) የኅብረት ሥራ ማህበራት በደረጃ የመለያ መስፈርት መሰረት ግምገማ የሚካሄደው በየደረጃው ባለው አግባብ ባለው ባለስልጣን በሚያቋቁሟቸው የባለሙያዎች ቡድን አማካይነት ይሆናል፡፡
3) የሚቋቋመው የባለሙያዎች ቡድን እንደየአደራጅ ተቋሙ የሰው ኃይል ብዛት የሚለያይ ሆኖ በሙያው የተሸለ ክህሎት ያላቸው ሦስት መዛኝ ባለሙያዎችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡
4) የሚዘጋጁት በደረጃ የመለያ መስፈርቶች እንደየኅብረት ሥራ ማህበራቱ አይነትና ደረጃ የሚለያይ ሆኖ መስፈርቶቹ በየጊዜው የሚሻሻሉ ይሆናል፡፡
5) በባህሪአቸው በተቀመጠው የመመዘኛ መስፈርት ለመመዘን አስቸጋር የሚሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ካጋጠሙ መመዘኛ መስፈርቱ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡
6) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 74 ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተዘጋጀው የኅብረት ሥራ ማህበራት የደረጃ መለያ መስፈርት አተገባበር ላይ የታዩ ክፍተቶችን በጥናት በመለየት በየሦስት ዓመቱ እንደአስፈላጊነቱ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡
7) በተዘጋጀው የኅብረት ሥራ ማህበራት መመዘኛ መስፈርት ላይ ለሚመለከታቸው መዛኝ ባለሙያዎች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡
8) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሚመዘነው የበጀት ዓመቱ ተጠናቆ ኦዲት ከተደረገ በኋል ይሆናል፡፡
9) አንድ የኅብረት ሥራ ማህበር ተመዝኖ ደረጃ ከተሰጠው በኋላ በቀጣይ የሚመዘነው የመጀመሪያው የምዘና ውጤት ከተሰጠ ከሦስት ዓመት በኋላ ይሆናል፡፡

## 75. የኅብረት ሥራ ማህበራት ደረጃዎች እና የደረጃ መለያ መስፈርቶች

1) የኅብረት ሥራ ማህበራትን በደረጃ ለመለየት የተመረጡ ደረጃ መለያ መስፈርቶች ትኩረት የሚደርገው በዋናነት፤

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት ተሳትፎ፣

ለ) የሚያገለግሏቸው አባላት ብዛት፣

ሐ) የሥራ ስፋት፣

መ) በምርት ላይ እሴት መጨመር፣

ሠ) የግብርና ቴክኖሎጅዎች አቅርቦት፣

ረ) የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነት፣

ሰ) በተማረ የሰው ኃይል ተግባሮቻቸውን የመምራት፣

ሽ) የማህበራዊ ተሳትፎ፣

ቀ) የትርፍ ክፍፍል፣

በ) ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ፣

ተ) ባላቸው የካፒታል ዕድገት፣

ቸ) ሌሎች ተያያዥ ተግባራት፣

2) የኅብረት ሥራ ማህበራትን በደረጃ ማስቀመጥ ካስፈለጉባቸው ምክንያቶች መካከል የሚጠቀሱት፤

ሀ) የተለዩበትን ደረጃ መሠረት በማድረግ ደረጃቸውን የሚመጥን ድጋፍና ክትትል ለማድረግ፣

ለ) ደረጃቸውን የገናዘበ አቅም ግንባታ አገልግሎት ለመስጠት፣

ሐ) አቅማቸውን ያገናዘበ ቁጥጥር ለማድረግ፣

መ) ራዕይና ተልዕኳቸውን እንዲያሳኩ በተለየ መልኩ ለማገዝ፣

ሠ) ኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚደግፉ አቅም ገንቢዎች እና ባለድርሻ አካላት የሚሰጧቸው ድጋፍ እና አገልገሎት ቀልጣፋ፣ ወጭ ቆጣቢ እና ተደራሽ እንዲሆን በማስፈለጉ ነው፡፡

3) የኅብረት ሥራ ማህበራት በደረጃ መለያ መስፈርት መሰረት ተገምግመው በሚያገኙት ውጤት መሠረት ደረጃቸው የሚለይ ይሆናል፡፡

4) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 75 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ-ተ) ላይ በተቀመጠው በደረጃ መለያ መስፈርት መሰረት የሚገመገም ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሚያገኘው ደረጃ “ሀ” ወይም ደረጃ “ለ” ወይም ደረጃ “ሐ” ይሆናል፡፡ ሆኖም እያንዳንዱ ደረጃ በየጊዜው እያተሻሻለ እንዲሄድ ትኩረት ተሰጥቶ የሚደገፍ ይሆናል፡፡

5) በመለያ መስፈርቱ ተገምግመው በደረጃ “ሐ” ላይ የተለዩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ደረጃቸውን ከ “ሐ” ወደ “ለ” እና በሂደትም ወደ “ሀ” ለማሻሻል ድጋፍና ክትትል ይደረግላቸዋል፣

6) በተመሳሳይ መልኩ በደረጃ “ለ” ላይ የሚመደቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በቀጣይ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ እና በሚደረግላቸው ድጋፍ ወደ ደረጃ “ሀ” እንዲያድጉ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡

7) በ “ሀ” ደረጃ የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት የተሻለ ተግባር በመፈጸም የላቀ አፈፃፀም ውስጥ መግባት እንዲችሉ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

## 76. ስለኅብረት ሥራ ማህበራት የደረጃዎች መግለጫ

1) በተቀመጠው የደረጃ መለያ መስፈርት መሰረት ያገኙት ጠቅላላ ውጤታቸው 80 ከመቶ እና ከዚያ በላይ የሆነ ነጥብ ላገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጥ ደረጃ “ሀ” ነው፡፡

2) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 71 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ ውጤታቸው ከ55---79.99 ከመቶ የሆነ ነጥብ ላገኙት የሚሰጥ ደረጃ “ለ” ሲሆን ጠቅላላ ውጤታቸው ከ 25---54.99 ከመቶ የሆነ ነጥብ ላገኙት የኅብረት ሥራ ማህበራት ደረጃ “ሐ” የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

3) በደረጃ “ሀ” ከተለዩት ውስጥ ከ90 ከመቶ በላይ ያመጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ወደ ሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲሰፋ የሚደረግ ይሆናል፡፡

4) በደረጃ “ለ” ከተለዩ ውስጥ ውጤታቸው ከ70 እስከ 55 በመቶ በታች ያመጡት የኅብረት ሥራ ማህበራት ውጤታማ እንዲሆኑ መሰረታዊ ችግራቸውን በመለየት ልዩ ድጋፍ ይሰጣቸዋል፡፡

5) በደረጃ “ሐ” ከተለዩ ውስጥ ከ55 በመቶ በታች ውጤት ላስመዘገቡ ቀጣይነት ያለው ድጋፍና ክትትል በማድረግ እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡

6) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 76 ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከ25 ከመቶ ነጥብ በታች የሚያገኙ የኅብረት ሥራ ማህበር ሆነው ሊቀጥሉ ስለማይችሉ አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚወስነው መሰረት ሕጉን ተከትሎ እንዲፈርሱ ወይም እንዲወሃዱ ይደረጋል፡፡

7) በተቀመጠው የደረጃዎች መለያ መስፈርት መሰረት በሚያገኙት ውጤት ከ95 ከመቶ ባላይ የሚያገኙ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች ተለይተው ወደጫፊ የወጡ (outlier) ተብለው ይለያሉ፡፡

8) በአፈፃፀማቸው ከተቀመጠው የመመዘኛ ስታንደርድ በላይ የሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት የበለጠ ሀብትና ጊዜ ማባከን ሳያስፈልግ ራሳቸውን ችለው እንዲቆሙ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 77. የኅብረት ሥራ ማህበራት በደረጃ የሚለይ አስተግባሪ ኮሚቴ ስለማደራጀት፣

1) የኅብረት ሥራ ማህበራትን በደረጃ ለመለየት አምስት አባላት ያሉት አስተግባሪ ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ፣

2) የአስተግባሪ ኮሚቴ አባላት በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ደረጃ የሚቋቋሙ ሆናል፣

3) የአስተግባሪ ኮሚቴ አባላት የሚመረጡት ከእያንዳንዱ የቴክኒክ የስራ ክፍሎች ይሆናል፣

4) የአስተግባሪ ኮሚቴ ሆነው መመረጥ የሚችሉት ቢያንስ በአካባቢው ከ2 ዓመት በአከባቢው የሰራ እና ኅብረት ሥራ ማህበራትን በሚገባ የሚያውቅ መሆን ይኖርበታል፣

5) የአስተግባሪው ኮሚቴ ኅብረት ሥራ ማህበራት በደረጃ ከተለዩ በኃላ ሃላፊነቱ የሚያበቃ ይሆናል፣

6) አስተግባሪ ኮሚቴው ተጠሪነቱ በየደረጃው ላለው የኅብረት ሥራ ማስፋፊ አካላት ሃላፊዎች ይሆናል፡፡

7) የአስተግባሪው ኮሚቴ የሚያከናውናቸው ተግባራት እንደ መደበኛ ስራ ተቆጥረው በእቅድ ውስጥ የሚዙ ይሆናል፡፡

## 78. የአስተግባሪ ኮሚቴው ተግባርና ሃላፊነት

1) በየደረጃው ያለው የኅብረት ሥራ ማህበራት በደረጃ መለያ አስተግባሪ ኮሚቴ የትግበራ እቅድ እና ሌሎች የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን ያከናውናል፣

2) በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረዥም ጊዜ በደረጃ የሚለዩ የመሰረታዊ፣ የዩኒዬን እና ፌዴሬሽን የኅብረት ሥራ ማህበራትን ይለያል፣

3) በየደረጃው የሚቋቋመው አስተግባሪ ኮሚቴ እርስ በራሱ የሚናበብ የራሱ የሆነ የማስተግበሪያ የጋራ እቅድ ይኖረዋል፣

4) በየደረጀው የሚቋቋመው አስተግባሪ ኮሚቴ ከታችኛው እርከን ላይ ለተቋቋሙት አስተግባሪ ኮሚቴዎች ስለ አተገባበሩ ግንዛቤ ይፈጥራል፣

5) በየደረጃው ለሚቋቋመው አስተግባሪ ኮሚቴ በየጊዜው ሪፖርቶችን ቀርባል፣

6) ለደረጃ መለያ ትግበራ በተመረጡት ክልሎች ወይም ዞኖች ወይም ወረዳዎች የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራትን መረጃ ያደራጃል፣

7) በደረጃ ልየታው ላይ ለሚሳተፉ በየደረጃው ለሚገኙ የአስተግባሪ ኮሚቴ አባላት ስለ አተገባበሩ በቂ ኦረንቴሽን በመስጠት የጋራ መግባባት ላይ በመደረስ ወደ ስራ እንዲገቡ ደርጋል፣

8) የተለዩትን የመሰረታዊ፣ የዩኒዬን እና ፌዴሬሽን የኅብረት ሥራ ማህበራትን በደረጃ እንዲለዩ እና ያደርጋል፣

9) የደረጃ ልየታ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በተመረጡት የኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ በመገኘት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል፣

10) የተቋቋመው አስተግባሪ ኮሚቴ የተግባራቱን አፈፃፀም ሂደት ይገመግማል፣ በየደረጃው ላላው አከል የግምገማ ውጤቱን ሪፖርት ያደርጋል፣

11) የአስተግባሪ ኮሚቴ በደረጃ የመክፍል ተግባሩን እንዳጠናቀቀ ደረጃቸውን መሰረት ያደረገ ድጋፍና አገልግሎት ማግኘታቸውን በቀጣይነት ለሚከታተል እና የሥራ ክፍል በእጁ ያለውን አጠቃላይ መረጃዎችን እና ሠነድ ያስረክባል፣

# ክፍል ዘጠኝ

# ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ስብሰባዎች፤

## 79. የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አጠራር እና የስብሰባ ሥነ-ስርዓት

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 33 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የጠቅላላ ጉባዔ በዓመት መጀመሪያ እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ መደበኛ ጉባዔ ማካሄድ አለበት፡፡

2) የኅብረት ሥራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባዔ በሚጠራው ስብሰባ ላይ በዋናነት ትኩረት የሚሰጣቸው አጀንዳዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) በዓመቱ በመደበኛ የሚካሄደው ስብሰባ ዓመታዊና የስድስት ወር ዕቅድ፣ በጀት እና የሥራ አመራር እና የቁጥጥር ኮሚቴ ሪፖርት ያደምጣል፡፡ ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን አፈፃፀም ይገመግማል፡፡ የቀጣይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

ሐ) የሥራ አመራር ኮሚቴ እና ሌሎች ኮሚቴዎች የማተካኪያ ምርጫ እና የተጓደሉ የኮሚቴ አባላትን ይመርጣል፡፡

መ) የሚሻሻሉ የመተዳደሪያ ደንብ፣ የውስጠ ደንብ፣ መመሪያዎች እና አሰራሮች ላይ ተወያይቶ ይወስናል፡፡

3) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 79 ንዑስ አንቀፅ 2 (ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ ዓመት በኋላ በ 30 ቀናት ውስጥ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ የኦዲት ሪፖርት ቀርቦ አስተያየትና የመጽደቅ ተግባር ይፈፅማል፡፡

4) የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ በፊት ቢያንስ ከ15 ቀን ቀደም ብሎ የመወያያ አጀንዳ፣ የሰብሰባ ቀን፣ ቦታና ሰዓት በጥሪው ደብዳቤ ላይ ተጠቅሶ ሁሉም አባል ሊያውቀው በሚችለው የመገናኛ ዘዴ በማስተላለፍ ጥሪው እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

5) የስብሰባ ጥሪ የሚተላለፉባቸው መንገዶችም እንደየ ኅብረት ሥራ ማህበራቱ አባላት የመኖሪያ ቦታ ወይም የመስሪያ ቦታ በደብዳቤ ጥሪ በማስተላለፍ ወይም ህዝብ በሚያይበት ቦታ ማስታወቂያ በመለጠፍ ወይም ለህዝብ ተደራሽ በሆኑ ሚዲያዎች እና በማናቸውም አመቺ መገናኛ ዘዴዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

6) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የመፍረስ ወይም የመዋሃድ ወይም የመከፈል ፍላጎት በአባላት መካከል ከ2/3ኛ በላይ ድምፅ በልዩ ጉባዔ ሰብሰባ ሲገኙ የሚወሰን ይሆናል፡፡

7) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 33 ንዑስ አንቀፅ 4 (ሀ እና ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጠቅላላ ጉባዔ ለማካሄድ ጥሪ ሲደረግ ምልዓተ- ጉባዔው ባለመሟላቱ ሰብሰባው በወቅቱ ባይካሄድም በ15 ቀን ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ስብሰባውን በመጥራት በተያዘው አጀንዳ ላይ በሰብሰባው በተገኙ አባላት ማካሄድ ይቻላል፡፡

8) የስብሰባ ጥሪዎች የሚተላለፉባቸው መንገዶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

ሀ) ለእያንዳንዱ አባል የስብሰባ ጥሪ ደብዳቤ አዘጋጅቶ በማሰራጨት፣

ለ) ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው እና ለንባብ ግልፅ በሆነ ቦታዎች የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያዎችን መለጠፍ፣

ሐ) ባለው መንግስታዊ የአስተዳደር መዋቅሮችን በመጠቀም የስብሰባ ጥሪ ማስተላለፍ፣

መ) በስልክ፣ በጋዜጣ፣ በሬዲዮ እና በቴሌቪዥን የስብሰባ ጥሪ ማስተላለፍ፣

ሠ) በድምፅ ማጉያዎችን ተጠቅሞ የስብሰባ ጥሪ በማድረግ ይሆናል፡፡

ረ) እንደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ነባራዊ ሁኔታ ሌሎች የጥሪ አመራጮችን የሚጠቀም ይሆናል፣

9) የሥራ አመራር ኮሚቴ፣ የቁጥጥር ኮሚቴ እና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች የራሳቸው የሆነ መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባ ይኖራቸዋል፣ ዝርዝር አሰራሩ በኮሚቴዎቹ ውስጠ ደንብ ውስጥ ይወሰናል፣

10) በሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ላይ በሚደረግ ውሳኔ አሰጣጥ የኮሚቴ አባላቱ ሁለት አማራጮች ላይ እኩል ድምፅ ሲኖራቸው ሊቀ-መንበሩ የደገፈው ወገን ሃሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፣

11) በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ወይም ልዩ ጠቅላላ ጉባኤ ተገቢውን ማስታወቂያ በመስጠት በድጋሚ በተጠራው ስብሰባ ምልአተ ጉባኤ ለሁለተኛ ጊዜ እንደገና ተጠርቶ ካልተሟላ አግባብ ያለው ባለስልጣን ለመጨረሻ ጊዜ ይጠራል፡፡ አግባብ ያለው ባለስልጣን በጠራው ስብሰባ ላይ ምልዓተ-ጉባኤው ካልተሟላ ስብሰባው መጨረሻ ላይ በተገኙት አባላት ምልአተ ጉባኤ ይሆናል።

12) በሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ያለው ምልአተ ጉባኤ ከጠቅላላ የኮሚቴው አባላት አንድ ሶስተኛው ይሆናል።

13) አግባብ ያለው ባለስልጣን ወይም ተወካዩ በማንኛውም ጊዜ በኅብረት ስራ ማህበር ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ መገኘት የስብሰባውን ሂደት ይታዘባል፣ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣

14) የጠቅላላ ጉባኤ ወይም የሥራ አመራር ኮሚቴ የስብሰባ ቀን፣ ቦታ፣ ሰዓት እና አጀንዳ የሚገልጽ ግልጽ አጭር ማስታወቂያ ቢያንስ ከአስራ አምስት ቀናት በፊት ማሳወቅና መጥራት አለበት፣

## ክፍል አሥር

## የኅብረት ሥራ ማህበራት የካፒታል አመሰራረት እና የፋይናንስ ምንጮች

### 80. ስለ መመዝገቢያ ክፍያ አሰባሰብና አጠቃቀም

1) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ሲመሰረት የአዋጭነት ጥናቱን መሰረት በማድረግ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የመመዝገቢያ ክፍያ መጠን ይወስናል፤

2) ማንኛውም አባል ወደ ኅብረት ስራ ማህበሩ ሲገባ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የተወሰነውን የመመዝገቢያ ክፍያ መጠን በአንድ ጊዜ መክፈል አለበት፡፡

3) የመመዝገቢያ ክፍያ መሰብሰብ የሚጀመረው በዚህ አንቀጽአንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ምስረታ ጉባኤ ከተካሄደ በኋላ መሆን አለበት፡፡

4) በመመዝገቢያ ክፍያ የሚሰበሰበው ገንዘብ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ምስረታ እና ምዝገባ ሂደት ጋር ተያይዞ ለሚወጡ የተለያዩ ወጪዎች መሸፈኛ የሚውል ይሆናል፡፡

5) ለመመዝገቢያ የተከፈለ ገንዘብ በማንኛውም ምክንያት ለአባሉ ተመላሽ አይሆንም ጥቅምም ሊጠየቅበት አይችልም፡፡

6) መተዳደሪያ ደንብ ስሻሻል እስካልተለወጠ ድረስ በየጊዜው በአዲስ ገቢ አባላት ላይ የመመዝገቢያ መጠን አይለዋወጥም፡፡

## 81. ከኅብረት ሥራ ማህበር አባላት የሚሰባሰብ ዕጣ

1) የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በመተዳዳሪያ ደንቡ ውስጥ በወሰነው መሠረት አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበራቸው የሚገዙት ዕጣ በገንዘብ ወይም በዓይነት ሊፈፅም ይችላል፡፡

2) በዓይነት ስለሚገዛው የዕጣ ሁኔታ የኅብረት ሥራ ማህበራት በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ ሊገልፁት ይችላሉ፡፡

## 82. በጥሬ ገንዘብ የሚደረግ የዕጣ ግዢ ክፍያ

በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 27 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጥሬ ገንዘብ የሚደረግ የዕጣ ግዥ የሚከተሉትን በተጨማሪነት ሊካተት ይገባል፡፡

1) በምስረታ ጉባኤው እንዲሸጡ የታወጁ ዕጣዎችን የተከፈለ ዕጣ፤ ቃል የተገባ ዕጣ እና የሚሸጥ ዕጣ በሚል መደልደል ይገባል፡፡

2) ኅብረት ሥራ ማህበሩ በዕቅዱ መሰረት ቢያንስ ስራውን ለማስጀመር የሚያስችል መነሻ ካፒታል ከመስራች አባላት በተከፈለ ዕጣ (paid up share) በምስረታ ወቅት ከእያንዳንዱ አባል ዝቅተኛውን ወይም ቢያንስ አንድ አምስተኛው ከአባላት ይሰበሰባል፡፡

3) ለመሸጥ ከታወጀው (Perscribed share) ቀሪውን ዕጣ ወዲያውኑ ለመግዛት የገንዘብ እጥረት ያለባቸው መስራች አባላት በአራት ዓመታት የጊዜ ገደብ ውስጥ ቃል የተገባ ዕጣ (subscribed share) እንዲገዙ ስምምነት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት የተከፈለውን ዕጣ (paid up share) ገንዘብ ለዚሁ ተግባር ታስቦ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ በማድረግ የገቢ ደረሰኞቻቸውን ይዘው ለምዝገባ መቅረብ ይችላሉ፡፡

5) ኅብረት ሥራ ማህበሩ ቃል ገብተው በስምምነታቸው መሰረት የዕጣ ገንዘቡን ላልከፈሉ አባላት የጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ ስድስት ወር በፊት በጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ግን ገንዘቡን ሳይከፍሉ የጊዜ ገደቡ የተጠናቀቀ እንደሆን በስምምነታቸው መሰረት ይጠየቁበታል፡፡

6) ከምስረታ በኋላ ወደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለሚገቡ አዲስ አባላት እና ነባር መስራች አባላት ቃል ከገቡት ውጭ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ካፒታል አቅም ለማጎልበት እንዲቻል ክፍት የተደረገ የሚሸጥ ዕጣ (declared share) መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

7) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 27 (5 እና 6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አባላት የገዙት ዕጣ ከተቀመጠው ገደብ በላይ መሆኑ ተገቢው ማጣራት ተደርጎ ልዩነቱ ለአባሉ ያለወለድ እንዲመለስለት ይደረጋል፡፡

8) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 27 (7) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለአባላት እንዲሸጡ ተደልድለው በአባላት አቅም ማነስ ያልተሸጡ ዕጣዎች በጠቅላላ ጉባኤ እንደገና እንዲሸጡ ይወሰናል፡፡

9) የኅብረት ሥራ ማህበራት በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ በሚወስኑት መሠረት በሀብትና ዕዳ ምጣኔ “Leverage ratio” አማካኝነት ዕጣ ማሰባሰብ ይችላሉ፡፡

## 83. <u>በዓይነት የሚደረግ የዕጣ ግዢ ክፍያ</u>

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ እንዲሸጥ ከወሰኑት ዕጣ ውስጥ የአባሉን የአከፋፈል እና የአካባቢውን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በዓይነት የሚሸጠው ዕጣ እንደሚከተለው ይሆናል፤

ሀ) የአዋጭነት ጥናቱን መሰረት በማድረግ ለዕጣ ግዢ በዓይነት የሚውሉት ንብረቶች አባላት እንደየ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓይነት እና የሥራ ባህሪ በመነሳት በዓይነት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚሰጡ ዕጣዎችን እንዲገዙ ሊወስን ይችላል፡፡

ለ) ለዕጣ ግዢ የሚውሉት ንብረቶች ዓይነት የአባላት ምርት፣ ቤት፣ መጋዘን፣ መኪና፣ አነስተኛ የእጅ መሣሪያዎች፣ እንስሳት እና ሌሎች በኅብረት ሥራ ማህበራት በመተዳደሪያ ደንብ የሚወሰኑትንም ሊጨምር ይችላል፡፡

ሐ) የዕጣ ግዢ ክፍያን ለመፈጸም የንብረቶቹ ግምት ንብረቱ ባለበት ሁኔታ በወቅቱ የገበያ ዋጋ በባለሙያ ወይም ኅብረት ስራ ማህበሩ በሚያቋቁመው ገማች ኮሚቴ ተገምቶ እንደ የንብረቶች አይነት በመዝገብ መያዝ አለበት፡፡

መ) በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተገምቶ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መዝገብ ላይ የተመዘገበ ንብረት የገበያ ዋጋ በመለዋወጡ ምክንያት የንብረቱ ዋጋ ከተገመተበት በላይ ከፍ ወይም ዝቅ ሊል አይችልም፡፡

ሠ) የተያዘው ዋጋ ግምት ኅብረት ስራ ማህበሩ እና የንብረቱ ባለቤት የተስማሙበት ለመሆኑ በቃለ ጉባኤ ተይዞ መቀመጥ አለበት፡፡

ረ) አንድ አባል ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ዕጣ ለመግዛት በዓይነት ያስረከበውን ንብረት ወደ ዕጣ ለመቀየር እንዲቻል ስምምነት የተደረሰበትን የግምት ዋጋ ለአንድ ዕጣ ዋጋ በማካፈል ንብረቱ ሊገዛው የሚችለው የዕጣ ብዛት ከታወቀ በኋላ በቃለ ጉባኤ ተይዞ በሂሳብ መዝገብና በንብረት መዝገብ መመዝገብ አለበት፡፡

ሰ) የንብረቱ ግምታዊ ዋጋ ለአንዱ ዕጣ ዋጋ በሚከፈልበት ጊዜ አባሉ እንዲገዛ ከተፈቀደለት የዕጣ ብዛት እኩል ካልሆነና ሙሉ ዕጣ መግዛት ካልቻለ አባሉ ልዩነቱን በጥሬ ገንዘብ እንዲያሟላ መደረግ አለበት፡፡

ሸ) የንብረቱ ግምት አባሉ እንዲገዛ ከተፈቀደልት የዕጣ መጠን ወይም ከአስር በመቶ በላይ ከሆነ ልዩነቱ በጥሬ ገንዘብ ለአባሉ ሊመለስለት ይገባል፡፡

ቀ) ልዩነቱን ወዲያውኑ መክፈል ካልተቻለ የሚከፈል ሂሳብ ተብሎ በሂሳብ መዝገብ ላይ በአባሉ ስም ተመዝግቦ በሚደረገው ውል መሠረት መከፈል አለበት፡፡

በ) አባሉ በዓይነት ያስረከበው ንብረት ቋሚ ከሆነ ወደ ዕጣ ተለውጦ ባለቤትነቱ ወደ ኀብረት ሥራ ማህበሩ ተዛውሮ በኀብረት ሥራ ማህበሩ ስም የስም ዝውውር እና ምዝገባ መካሄድ አለበት፡፡

2) አባሉ ባስረከበው ንብረት ምትክ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ እና የሼር ሠርተፊኬት ማግኘት አለበት፡፡

3) ማንኛውም አባል ለዕጣ ግዢ ባስረከበው ንብረት ላይ የንብረት ባለቤትነት ጥያቄ ሊያነሳ አይችልም፡፡

## 84. <u>ስለተጨማሪ ዕጣ ሽያጭ</u>

1) የኀብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኀብረት ሥራ ማህበራት ቀድሞ የታወጀውን ዕጣ ሸጠው ከጨረሱ አዲስ ዕጣ በጠቅላላ ጉባዔ አስወስኖ እኩል ዋጋና መጠን ያላቸው ዕጣዎች መሸጥ ይችላሉ፡፡
2) አዲስ ለአባላት የሚሸጥ ተጨማሪ ዕጣ ሙሉ በሙሉ በኀብረት ሥራ ማህበራት አዋጁ ውስጥ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ተሸጦ ማጠናቀቅ አለበት፡፡
3) የኀብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ አንቀፅ 35 ንዑስ አንቀፅ 3 በተደነገገው መሠረት አባላት ከተጣራ ትርፍ የሚያገኙትን ገንዘብ ለተጨማሪ ዕጣ ግዥ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ሊገዙ ይችላሉ፡፡
4) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 84 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት ተጨማሪ ዕጣ ለመሸጥ የሚታወጅባቸው የሚከተሉት ምክንያቶች ሲኖሩ ነው፡፡

ሀ) ኀብረት ሥራ ማህበሩ ለሚያዘጋጃቸው ፕሮጀክቶች የካፒታል እጥረት ሲያጋጥመው፣

ለ) ከውጭ የፋይናንስ ወይም የገንዘብ ተቋማት ብድር ከማፈላለግ በፊት የውስጥ የገንዘብ አቅም ማሳደጉ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው፣

ሐ) ቀደም ሲል በአባላት ተይዘው የነበሩ ዕጣዎች በአራት አመታት ውስጥ ተሸጠው በማለቃቸው ወይም በሌላ ልዩ ምክንያት ያልተሸጡ በጠቅላላ ጉባኤ እንደገና እንዲሸጡ ሲወሰን፡፡

## 85. <u>የመጠባበቂያ ሂሳብ አቀማመጥ እና አጠቃቀም</u>

1) የመጠባበቂያ ገንዘብ በኀብረት ስራ ማህበሩ ስም የቁጠባ ሂሳብ ተከፍቶለት የሚቀመጥ የካፒታል በመሆን ለአበዳሪ ተቋማት እንደብድር ዋስትና ሆኖ ሊታይ ይቻላል፡፡ ሆኖም የመጠባበቂያ ገንዘብ አጠቃቀም እንደሚከተለው ይሆናል፤

ሀ) የመጠባበቂያ ገንዘቡ የኀብረት ሥራ ማህበሩን ህልውና በማይነካ መልኩ የጠቅላላ ጉባኤው በየዓመቱ በሚቀርብለት የኦዲት ሪፖርት መሠረት ይወስናል፡፡

ለ) በመጠባበቂያ ከተያዘው ሂሳብ ውስጥ በጥናት ላይ ተመሥርቶ ሥራ ላይ እንዲውል ሊወስን ይችላል፡፡ ሆኖም ከ75 በመቶ በላይ ከመጠባበቂያ ሂሳብ ውስጥ ሥራ ላይ ሊውል አይችልም፡፡

2) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራ ላይ እንዲውል ለተወሰነ የመጠባበቂያ ገንዘብ መጠን የመድን ዋስትና እንዲገባለት በማድረግ ለሚከተሉት ተግባራት መጠቀም ይችላሉ፡፡

ሀ) ለአባላት የአጭር ጊዜ ብድር ወይም ለአንድ ምርት ዘመን ለግብዓት ግዢ፣ ለምርት ማምረቻ እና ማሰባሰቢያ ወጪዎች፣

ለ) ለአባላት ለአነስተኛ የንግድ እና የኢንቨስትመንት፣

ሐ) በጅምላ ለሚቀርቡ የጥሬ ዕቃዎች፣ የሸቀጥ ግዢ እና ከአባላት የምርት መሰብሰቢያ ቅድሚያ ክፍያ፡፡

## 86. ዕዳንና ካፒታልን ስለማጣጣም

1) በቁጠባ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ስጋት ለመቀነስ እና ለብድር የሚውል ገንዘብ ክምችት ለማሳደግ የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት በቁጠባ ዕጣ ምጥጥን ተግባራዊ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

2) ምጥጥኑም በጥናት ላይ ተመስርቶ እንደ አባላት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በመተዳደሪያ ደንብ ላይ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 87. የኅብረት ሥራ ማህበራት ፈንድ ማቋቋም እና አስተዳደር

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 45 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተወዳዳሪ በማድረግ አባላትን ያሳተፈ እና ተጠቃሚ የሚያደርግ የኅብረት ሥራ ፈንድ ይቋቋማል፡፡

2) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 87 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚሁ መሠረት ስለፈንዱ መቋቋም፣ አስተዳደር፣ ላይ ከዚህ የሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ለአባላት ከሚከፋፈለው ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ ውስጥ ሶስት በመቶ በየደረጃው ከተቋቋሙት ኅብረት ስራ ማህበራት በሚዘጋጀው የኦዲት ሪፖርት በግልጽ ተሰልቶ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

ለ) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 827 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) መሰረት ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ፈንድ የተቀነሰው ውስጥ ሃምሳ ከመቶ ፈንዱ እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን ከራሱ የቀነሰውን ሃምሳ ከመቶ በማጠቃለል ለተቋቋመው ፈንድ ይልካል፡፡

ሐ) በየደረጃው ካሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚቀነሰው የሶስት በመቶ ፈንድ በኦዲት ምርመራ ወቅት እራሱን የቻለ የሂሳብ ርዕስ እና መግለጫ ሊኖረው ይገባል፡፡

መ) በየደረጃው ባሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከኦዲት በኋላ ተቀንሶ የቀረው ሃምሳ በመቶ የኅብረት ሥራ ፈንድ በኅብረት ሥራ ማህበራት ፋይናንስ እና የሂሳብ አስተዳደር መመሪያ መሠረት የሚተዳደር ሆኖ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በሚወስነው መሰረት ሂሣቡም በተለየ ሁኔታ ለብቻው የሚያዝ ይሆናል፡፡

ሠ) በሀገር አቀፍ ደረጃ ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር እስከ ፌዴሬሽን ተሰባስቦ የመጣውን የኅብረት ሥራ ማህበራት ፈንድ የሚተዳደረው በኅብረት ሥራ ማህበራት ሊጉ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት መሠረት ሆኖ ሂሣቡም በተለየ ሁኔታ ለብቻው የሚያዝ ይሆናል፡፡

ረ) ህልውናቸውን ከሚያጡ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከማይከፋፈል የጋራ ገንዘብና ንብረት የሚሰበሰብ ገቢ እና ከመንግስት እና ከልማት አጋር አካላት በስጦታ፣ ድጋፍ እና ከመሳሰሉት ከሚገኝ ገቢ የፈንዱ አካል ይሆናል፣

ሰ) ኅብረት ሥራ ማህበራት በየደረጃው በሂደት ራሳቸውን ችለው በራሳቸው አቅም የኦዲት፣ የሕግ አገልግሎት፣ የአቅም ግንባታ፣ የጥናት እና ምርምር፣ የፕሮሞሽንና ኮሚኒኬሽን እና የመሳሰሉትን ወጪዎችን ለመሸፈን የሚረዳ የኅብረት ሥራ ፈንድ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 88. ከፋይናንስ ተቋማት የሚገኝ የፋይናንስ ምንጭ

1) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በጥናት ለቀረቡ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚሆን ከፋይናንስ ተቋማት ጋር የሚያደርጉት የብድር ስምምነት በኅብረት ሥራ ማህበራት መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በሚወስኑት እና አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

2) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ውጭ ባሉ የተለያዩ ኢንቨስትመንቶች ወይም የአክሲያን ገበያዎች አክሲዮን ግዥ መሳተፍ አይችልም፡፡

3) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 88 ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ መመሪያ መውጣት በፊት ከሌሎች ኢንቨስትመንቶች ወይም የአክሲዮኖችን የገዙ የኅብረት ሥራ ማህበራት ምን መሆን እንዳለበት አግባቢ ያለው ባለስልጣን ወደፊት መመሪያ የሚያወጣ ይሆናል፡፡

## 89. ከአባል ውጭ ስለሚገኝ ፋይናንስ

1) በኅብረት ስራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 አንቀጽ 23 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኅብረት ሥራ ማህበራት በመተዳደሪያ ደንባቸው በሚወስኑት መሠረት ግብዓት ለማሰራጨት፣ ምርት ለመረከብ፣ ተዘዋዋሪ ብድሮችን እና የፍጆታ ምርቶች ከአባላት ውጭ ለሚሰጡት አገልግሎት ተመጣጣኝ የአገልግሎት ክፍያ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

2) በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ ክልል ውስጥ የሚኖሩ አባል ላልሆኑ ሰዎች በአባልነት ወደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ እስኪመጡ ድረስ የሚሰጠውን ምርትና አገልግሎት በመተዳደሪያ ደንብ በሚሰነው መሠረት በተመጣጣኝ ዋጋ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

3) የግብርና ኅብረት ሥራ ማህበራት አባል ላልሆኑ ሰዎች የሚሰጡት አገልግሎቱ ከአንድ የምርት ዘመን በላይ ሊያልፍ አይችልም፡፡ ሆኖም አባል ያልሆኑ ሰዎች ከአንድ የምርት ዘመን በኋላ አባል ለመሆን ፍቃደኛ ካልሆኑ አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

4) በተለይ የሸማቾች እና ሁለገብ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት አባል ካልሆኑት ጋር የሚደረገው የምርትና አገልግሎት ግብይት አሰራር የተለየ የሂሳብ አያያዝና አመዘጋገብ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ሂሳባቸውም በተለየ ሁኔታ ኦዲት የሚደረግ ይሆናል፡፡

5) ከአባል ውጭ በመስራት የሚገኝ የትኛውም ትርፍ ለአባላት በትርፍ ክፍፍል አይሰጥም፡፡ ሆኖም ግን በመተዳደሪያ ደንባቸዋ በሚወስኑት መሰረት ለስራ ማስፋፊያና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች ሊያውሉት ይችላሉ፡፡

## ክፍል አሥራ አንድ

## በኅብረት ሥራ ማህበራት የትርፍ ክፍፍል እና የብድር አስተዳደር

### 90. የተጣራ ትርፍ አከፋፈል

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 45 ስለተጣራ ትርፍ አከፋፋልና አደላደል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኅብረት ሥራ ማህበራት በየዓመቱ ወጪ በመቀነስ እና ገቢ በማሳደግ ከሚሰጧቸው የምርትም ሆነ አገልግሎት ዋጋ ለአባላት ተመጣጣኝ ትርፍ በማስገኘት ተጨማሪ እርካታ ለመፍጠር መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

2) በማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ለአባላት የሚከፋፈለው የትርፍ ክፍፍል የገዛውን ዕጣ እና ያደረገውን ተሳትፎ መሠረት ማድረግ አለበት፡፡

3) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 90 ንኡስ አንቀጽ 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ባላቸው ልዩ ባህሪ ምክንያት አባላት ባላቸው ካፒታል ብቻ የትርፍ ክፍፍል ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

4) ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያደርጉት የትርፍ ክፍፍል ሲወስኑ እንደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓይነት እና የሥራ ባህሪ ለዕጣ ወይም ለተሳትፎ የሚከፈለው መጠን በኅብረት ሥራ ማህበራት መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ ከፍተኛውን ድርሻ ለተሳትፎ ወይም ለዕጣ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

5) ማንኛውም የአባላትን ተሳትፎ የሚያበረታታ የኅብረት ሥራ ማህበር የአባላትን ተሳትፎ መረጃ በአግባቡ በተሳትፎ መዝገባ በወቅቱ መዝግቦ የትርፍ ክፍፍሉን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

6) የኅብረት ሥራ ማህበሩ መጠባበቂያ ገንዘብ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ካፒታል 30 በመቶ በላይ ሲሆን ከተጣራ ትርፍ የሚቀነሰው መጠባበቂያ ገንዘብ ቀርቶ የተገኘው የተጣራ ትርፍ በመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ሙሉ በሙሉ ለአባላት ይከፋፈላል፡፡

7) እያንዳንዱ አባል ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የገዛውን የዕጣና የከፈለው የገንዘብ መጠን እንዲሁም የተሳትፎ መጠንና አመዘጋገቡ በዚህ አንቀጽመሰረት ስለመፈፀሙ በኦዲት ምርመራ ወቅት በመርማሪው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

8) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ለእያንዳንዱ አባል የትርፍ ክፍፍል ሲያከፋፍል እያንዳንዱ ግለሰብ አባል ከሚያገኘው ገቢ ላይ በሀገሪቱ የታክስ አከፋፈል ስርዓት መሰረት በመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበሩ አማካኝነት ተቀንሶ በአቅራቢያው ለሚገኝ ግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ገቢ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

9) አባላት በሚያገኙት የተጣራ ትርፍ አባሉ በጽሁፍ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ተጨማሪ ዕጣ ሊገዙበት ይችላሉ፡፡

10) ከአበዳሪ አካላት ወይም ከሌላ አካላት የሚቀርብ ማንኛውም የይገባኛል ጥያቄ ሳይመለስ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ለአባላት ምንም ዓይነት የትርፍ ክፍፍል አይደረግም፣

11) ከኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ወይም ፌዴሬሽን ከኦዲት በኃላ የተገኘውን የትርፍ ክፍፍል ድርሻ በተዘረጋው አሰራር መሰረት ለአባላት በወቅቱ ማስተላለፍ አለበት፣ ለአባላት የተላከ የትርፍ ክፍፍል ከአባላት ውሳኔ ውጭ ለሌላ ተግባር ማዋል አይቻልም፡፡

## 91. <u>የተጣራ ትርፍ ወይም ኪሳራ ስሌት አሰራር</u>

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በገዙት የዕጣ መጠን እና በተሳትፋቸው ላይ በመመስረት የትርፍ/ኪሳራ/ ክፍፍል ስሌት በሚከተለው መሰረት ይከናወናል፤

ሀ) የእያንዳንዱ አባል የዕጣ ድርሻ ለማስላት ለዕጣ ድርሻ ወይም ለተሳትፎ ሊውል የሚችለው የትርፍ መጠን በመተዳደሪያ ደንብ በተደነገገው የድልድል ስሌት መሰረት ይሆናል፡፡

ለ) የአንድ ብር የዕጣ ድርሻ ለማወቅ ለዕጣ ድርሻ የተመደበውን የገንዘብ መጠን ለጠቅላላ የዕጣ ሚዛን ድምር በማካፈል ስሌቱን መታወቅ አለበት፡፡

ሐ) የተገኘውን የአንድ ብር የዕጣ ተሳትፎ ድርሻ አባሉ በገዛዉ የዕጣ ድምር በማባዛት የእያንዳንዱን አባል የዕጣ ድርሻ በማግኘት ክፍፍሉ መፈጸም አለበት፡፡

| |
|---|
| የአንድ ብር የዕጣ ድርሻ = ለዕጣ ክፍፍል የተመደበ ገንዘብ ÷ ለጠቅላላ ዕጣ ድምር |
| የአንድ አባል የዕጣ ድርሻ = የአባሉ የዕጣ ድምር x በአንድ ብር የዕጣ ድርሻ |

መ) የተገኘውን የአንድ ብር የተሳትፎ ድርሻ አባሉ ባደረገው የምርት ግዥ ዋጋ ወይም ሺያጭ ዋጋ ወይም በቁጠባ ወይም ብድር መጠን በማባዛት የእያንዳንዱን አባል የተሳትፎ ድርሻ በማግኘት ክፍፍሉ መፈጸም አለበት፡፡

| |
|---|
| የአንድ ብር የተሳትፎ ድርሻ = ለተሳትፎ ክፍፍል የተመደበ ገንዘብ ÷ ለጠቅላላ የንግድ ልውውጥ መጠን |
| የአንድ አባል የተሳትፎ ድርሻ = የአባሉ የተሳትፎ ድምር x በአንድ ብር የተሳትፎ ድርሻ |

ሦ) የትርፍ ክፍፍሉ የሚካሄደው በአባላት የትርፍ ክፍፍል መክፈያ ቅጽ /ፔሮል/ በማዘጋጀት ይሆናል፣

ረ) የእያንዳንዱ አባል የዕጣ ድርሻ እና የተሳትፎ ድርሻ ለየብቻው በመስራት ጠቅላላ የትርፍ ድርሻ ተደምሮ መታወቅ አለበት፣

ሰ) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከኦዲት በኋላ የሚገኘውን የተጣራ ትርፍ በመተዳደሪያ ደንቡ በተደነገገው መሠረት መክፍል አለበት፡፡ አባላት በጥያቄያቸው ያሚያገኙትን የተጣራ ትርፍ ድርሻ ተጨማሪ ዕጣ ለመግዛት ወይም ገንዘቡን ለመውሰድ ከወሰኑ የገቢ ግብር ተቀናናሽ ሆኖ ሊከፈላቸው ይገባል፡፡

ሸ) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 91 ንዑስ አንቀፅ 1 (ሰ) በተደነገገው መሠረት ማንኛውም የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ከእያንዳንዱ ግለሰብ አባል ቆርጦ ያስቀረውን የገቢ ግብር በአቅራቢያው ለሚገኝ ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

ቀ) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 53 (ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ለአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ትርፍ በሚያከፋፍሉበት ጊዜ ከአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት የገቢ ግብር አይሰበስቡም፡፡

ሽ) በዕጣና በተሳትፎ የትርፍ /ኪሳራ/ ክፍፍል አከፋፈል የተጣራ ትርፍ ድርሻቸውን ያልወሰዱ አባላት ዝርዝራቸውን ለብቻው በሰነድ መዝግቦ በመያዝ ጠቅላላ ሂሳቡ በተከፋይ እዳ ተመዝግቦ ይያዛል፡፡

ቀ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ ኪሳራ በሚያጋጥመዉ ጊዜ በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ኪሳራ በሚያጋጥመዉ ጊዜ ከመጠባበቂያ ሂሳብ እንዲቀንስ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ኪሳራዉ ከመጠባበቂያ ሂሳብ ከተቀመጠው የሚበልጥ ከሆነ ከእንዳንዱ አባል ዕጣ ላይ ተቀንሶ ለኪሳራው ማቻቻያ ይሆናል፡፡

በ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ ኪሳራ በሚያጋጥመዉ ጊዜ ለእያንዳንዱ የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል በዕጣና በተሳትፎው መሰረት በማስላት የሚደርሰውን ኪሳራ ያሳውቃል፡፡

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ወይም ፌዴሬሽን ለአባላት ያከፋፈለው የትርፍ ክፍፍል ለእያንዳንዱ ግለሰብ አባል መድረሱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፣ የትርፍ ክፍፍሉን የወሰዱት አባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ለግለሰብ አባላት ስለመከፋፈላቸው የሚሳይ በቂ መረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

## 92. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት ንብረትና ገንዘብ የማይከፋፈል ስለመሆኑ</u>

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጁ 985/2009 አንቀፅ 64 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመጠባበቂያ ሂሣብ ውስጥ የተመዘገበ፣ በስጦታ ወይም በኅብረት ሥራ ማህበራት ፈንድ የተመዘገበ ሂሳብ ወይም በውርስ የተገኘ ወይም ከአባላት መመዝገቢያ ተሰብስቦ ጥቅም ላይ ያልዋለ ወይም ከቅጣት የተሰበሰበ ወይም ከአባላት ወጪ በተደረገ ልውውጥ የተገኘ ገንዘብ ከሆነ ሣይከፋፈል የወል ንብረት ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 92 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ የማይከፋፈል የኅብረት ሥራ ማኅበራት ንብረትና ገንዘብ አቀማመጥ እንደሚከተለው ይሆናል፤

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሲፈርሱ የማይከፋፈለው የጋራ ንብረት በተቋቋመው የኅብረት ሥራ ማህበራት ፈንድ ውስጥ ገቢ ይደረጋል፡፡

ለ) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በውህደት ወይም በመከፈል ወቅት የነበረው የማይከፋፈል የጋራ ንብረት በውህደት ወይም በመከፈል ለተቋቋሙት አዲስ ኅብረት ሥራ ማህበራት በማይከፋፈል የጋራ ንብረትነት ተመዝግበው ይተላለፋል፡፡

ሐ) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 92 ንዑስ አንቀፅ 1 እና በንዑስ አንቀፅ 2 (ሀ እና ለ) መሠረት የማይከፋፈል የኅብረት ስራ ማህበራት ንብረት እና ገንዘብ በማንኛውም መንገድ ለአባላትም ሆነ ለሌላው ወገን ለብድር ወይም ለዕዳ ክፍያ ወይም ዕዳን ለማቻቻል ወይም ለሽልማት እና ለመሳሰሉት ማዋል አይቻልም፡፡

## 93. <u>ስለብድር አገልግሎት</u>

1) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ለአባላት፣ ለመሰል እና አቻ ኅብረት ሥራ ማህበራት በመተዳዳሪያ ደንባቸው በወሰኑት መሠረት በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ የሚመለስ የገንዘብ እና የዓይነት ብድር አገልግሎት ሊሰጡ ወይም ሊወስዱ ይችላሉ፡፡

2) ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የሚያቀርቧቸው የብድር ዓይነቶች በመተዳደሪያ ደንባቸው እና የአባላትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ በወለድ ወይም ወለድ አልባ ሊሆን ይችላል፡፡

3) ለአባላት የሚቀርብ ብድር እንደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር ዓይነት፣ የብድር ዋስትና እና የብድር አመላለስ አሰራሮችን በመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት በጠቅላላ ጉባዔ አፀድቀው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

4) የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባለት የሰጡትን ብድር በገቡት ውል መሰረት በወቅቱ ሙሉ በሙሉ የማስመለስ ግደታ አለባቸው፡፡

## 94. <u>ስለብድር አሰጣጥ</u>

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት ወቅታዊ እና ተደራሽነት ያለው የተለያየ የብድር ዓይነት እና መጠን ለአባላት ማስራጨት ይችላሉ፡፡

2) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ለአባላት የሚያቀርበው ብድር በመጠየቂያ የተደገፈ፣ የብድር ወለድ መጠን እና የመክፈያ ጊዜ ሰሌዳ ሊኖረው ይገባል፡፡

3) ኅብረት ሥራ ማህበር ለአባላት የሚሰጡት የብድር የሚከተሉትን ሁኔታዎችን ያካትታል፤

ሀ) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ለአባላቱ እና ለሌሎች አቻ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰራጨው ብድር ጥናትን መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡

ለ) ለብድር የሚውል ገንዘብ ምንጭ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ካፒታል፣ ከአባላት ቁጠባ፣ መሰል ወይም ከሌሎች አቻ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚገኝ ብድር፣ ከመንግስት ከሚገኝ የበጀት ድጋፍ፣ ከተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት የሚገኝ ብድር እና ከሌሎች አቅም ገንቢዎች የሚገኝ ተዘዋዋሪ ፈንድ ሊሆን ይችላል፡፡

ሐ) የፋይናንሰ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት ከሚሰበስቡት ቁጠባ ጋር በሚደረገው ስምምነት መሠረት ከ70 እስከ 80 በመቶ ድረስ ለብድር ሊያውሉ ይችላሉ፡፡

መ) ከፋይናንስ የኅብረት ሥራ ማህበራት ውጭ ያሉ ለሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ግን ካፒታላቸው ለአደጋ እንዳይጋለጥ ሲባል ለአባላት ከራሳቸው ካፒታል ለብድር የሚያውሉ ከሆነ የካፒታላቸውን 70 ፐርሰንት መብለጥ የለበትም፡፡

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት ለሚሰጡት ብድር የሚያስከፍሉት የወለድ መጠኑን በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ የተወሰነ እና በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ መሆን አለባቸው፡፡

ረ) በወለድ አልባ ስርዓት መሠረት የብድር አገልግሎት ክፍያ የሚሰጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት ጋር በሚያደርጉት ስምምነት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

ሰ) የኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር ውል ሲዘጋጅም ሆነ በብድር መመለሻ ጊዜያት የብድር መክፈያ ጊዜ ሰሌዳ ለእያንዳንዱ ተበዳሪ አባል በጽሁፍ ወይም በሞባይል ወይም በኢሜል ወይም በማስታወቅያ በመጠቀም እንዲያውቁት ለያደርጉ ይችላሉ፡፡

## 95. ስለመበደር ወሰን

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት የገንዘብ አቅማቸውን ለማጠናከር ከአባላት፣ ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም ከአበዳሪ ተቋማት መበደር ይችላሉ፡፡

2) የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚበደሩት ብድር ካላቸው የካፒታል መጠን የማይበልጥ ሆኖ በጠቅላላ ጉባኤ መወሰን አለበት፣

3) ማንኛውም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ለሚበደረው ብድር የብድር መድን ዋስትና መግባት አለበት፡፡

4) በኅብረት ሥራ ማኅበር አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 47 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ብድር ለመበደር የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይገባዋል፡፡

ሀ) ጥሩ የብድር የመመለስ ታሪክ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፣

ለ) ተከታታይነት ያለው ኪሳራ የሌለበት፣

ሐ) በብድር የዋስትና መያዣ የሌለበት፣

መ) ብድሩ ለምን ጉዳይ እንደሚውል በግልፅ የሚያሳይ መረጃ የሚያቀርብ፣

ሠ) የተበደረውን ስራ ላይ ለማዋል ያለው ልምድ፣

ረ) የንግድ ሥራ ዕቅድ ያለው፣

ሰ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር አስተዳደር ታሪክ፣

ሸ) የፋይናንስ መግለጫዎች፣

ቀ) በቂ እና ተመጣጣኝ ዋስትና ማቅረብ የሚችል፣

በ) ከመንግስት ብድሩ ለታለመለት ዓላማ የሚውል እና በወቅቱ ስለመመለሱ ድጋፍ ማቅረብ፣

5) የኅብረት ሥራ ማህበራት በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የብድር አስተዳደር ስርዓት ሊኖራቸው ይችላል፣

## 96. ስለማበደር ወሰን

1) በኅብረት ሥራ ማኅበር አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 48 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተበዳሪ አባላት የሚከተሉትን ግዴታዎች ወይም መስፈርቶች የሚያሟሉ ሊሆኑ ይገባቸዋል፤

ሀ) ብድር በወቅቱ የመመለስ ታሪክ ያለው፣

ለ) ቀድሞ በብድር የተያዘ የዋስት መያዣ የሌለበት፣

ሐ) ብድሩ ለምን ጉዳያ እንደሚውል የሚገልፅ የጽሁፍ ጥያቄ፣

መ) የተበደረውን ስራ ላይ ለማዋል ያለው ልምድ፣

ሠ) የንግድ ሥራ ዕቅድ ያለው፣

ረ) በቂ ዋስትና ማቅረብ የሚችል፣

## 97. ስለዋስትና ዓይነት እና አማራጮች

በኅብረት ሥራ ማኅበር አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 49 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ለሚሰጠው የብድር አገልግሎት የሚጠይቀውን ዋስትና ዓይነት እና አማራጮቹን የሚከተሉትን ያካትታል፤

1) ኅብረት ስራ ማህበራት ለሚያበድሩት ገንዘብ ወይም የዓይነት ብድር ለዋስትና የተለያዩ አማራጮችን እንደየኅብረት ስራ ማህበራቱ ዕድገት፣ ዓይነት እና ባህሪያት በመያዣነት መጠቀም ይችላሉ፣

2) በዋስትና የሚያዙ ቋሚ ንብረቶች እና የገንዘብ ሰነዶች ትክክለኛነት በሚመለከታቸው አካላት መረጋገጥ አለበት፡፡

3) ማንኛውም የኅብረት ስራ ማህበር ለሚያቀርበው የብድር አገልግሎት በዋስትና የሚይዘውን ንብረት ወይም ገንዘብ ዕዳው በወቅቱ ካልተከፈለ ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በመሸጥ ወይም ገንዘቡን ለዕዳ ማካካሻነት በማዋል ዕዳውን የማስከፈል መብት አለው፡፡

4) የወለድ አልባ አገልግሎት በሚሰጡ ኅብረት ሥራ ማህበራት በመተዳደሪያ ደንብ በሚወስኑት መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

5) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ለሚሰጠው ብድር ተበዳሪዎችን የብድር ሕይወት ዋስትና እንዲገቡ አሰራሩን መዘርጋት አለበት፡፡

# ክፍል አሥራ ሁለት

# የኅብረት ሥራ ማህበር ልዩ መብቶች

## 98. ድርሻን እና ጥቅምን ስለማስከበር፣ ስለማቻቻልና ስለማስተላለፍ

1) በኅብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 26፣ 30፣ 40፣ 41 እና 42 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከካፒታል በፊት ለሰዎች ቅድሚያ ስለሚሰጡ አባላት ከአባልነት ስሰናበቱ ጥቅሞቻቸው ተከብሮላቸው ያለባቸው ዕዳ ተቻችሎ ይስተናገዳሉ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አባል ያስቀመጠውን ቁጠባ ወዲያው የማግኘት መብት ያለው ሲሆን ያለውን ዕጣ ማግኘት የሚችለው የኅብረት ሥራ ማህበሩ ኦዲት ተደርጎ ነው፡፡ ሆኖም የኅብረት ሥራ ማህበሩ ኪሳራ የሚያጋጥመው ከሆነ አባሉ ኪሳራውንም በሕጉ መሰረት የድርሻውን የሚካፈል ይሆናል፣

3) አንድ አባል በፍላጎቱ ወይም በህግ ውሳኔ ወይም በሞት ከተለየ ወይም ከአባልነቱ የተሰናበተ ከሆነ በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚፈልግበትን ዕዳ ከከፈለና ካቻቻለ በኋላ የሚቀረው ድርሻና ጥቅም ብቻ የሚከበርለት ይሆናል፣

4) አንድ አባል ያለው ጥቅሙ ወይም ድርሻው ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ውጭ ላለበት ዕዳ ወይም ተጠያቂነት ሊከበር፣ ሊያዝ ወይም ሊሸጥ አይችልም፣

5) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከአባሉ ላይ የሚፈልገው ዕዳ የሚኖር ከሆነ አባሉ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ ካለው ድርሻ ወይም ሌሎች ጥቅሞች ላይ በመቀነስ ዕዳውን ያቻችላል፣

6) የአባሉ ዕዳ ከሚቻቻለው ዕጣ ወይም ጥቅም በላይ የበለጠ ከሆነ በሥራ አመራር ኮሚቴ አማካኝነት ዋስ እንዲሸፍን ይደረጋል፡፡ ሆኖም ዕዳው በዋሱ የማይሸፈን መሆኑ ሲረጋገጥ ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ይደረጋል፡፡

7) አባሉ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ያለውን ድርሻና ጥቅም ማስተላለፍ የሚችለው አባሉ በሚያቀርበው ማመልከቻ ብቻ ነው፡፡

8) ማንኛውም አባል ድርሻውንና ጥቅሙን ማስተላለፍ የሚችለው ለኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ለሆነ ወይም ለመሆን ፈቃደኝነቱን ለገለጸ ወይም ለሌላ ሰው መሆን ይችላል፡፡

9) ወራሹ የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ለመሆን ከፈለገ በዚህ መመሪያና መተዳደሪያ ደንብ በሚወስነው መሰረት የአባልነት መስፈርቶችን የሚያሟላ ከሆነ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዲወረስ የተፈቀደለትን ድርሻና ጥቅሙ ታስቦለት በአዲስ አባልነት መመዝገቢያ በመክፈል የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ሊሆን ይችላል፡፡

## 99. <u>የመንግስት ድጋፍ</u>

በኅብረት ሥራ አዋጅ 985/2009 አንቀፅ 43 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት በተጨማሪነት ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት የሚከተሉትን ድጋፎች ያደርጋል፤

1) ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ከደረሱበት የዕድገት ደረጃ አንፃር የተለያዩ ድጋፍ ያደርጋል፣

2) የኅብረት ሥራ ማህበራትን አሰራር በቴክኖሎጂ በመደገፍ ማዘመን፣

3) ምርታማነት ሊጨምሩ የሚያስችሉ ልምዶች፣ አሰራሮች በማምጣት እንዲጠቀሙ ማድረግ፣

4) የውስጥ የፋይናንስ አቅማቸው እንዲያድግ የተለያዩ የፋይናንስ አማራጮች ወይም የኅብረት ሥራ ፈንድ መዘርጋት፣

5) የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እና ፕሮግራሞች በመቅረፅ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

6) የኅብረት ሥራ የትምህርትና ስልጠና ተቋም እንዲቋቋም ድጋፍ ማድረግ፣

7) ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት የሚያግዙ ምክረ ሃሳቦችን የሚሰጡ የአማካሪ ምክር ቤቶችንና አማካሪ ባለሙያዎችን ማቋቋም፣

8) ኅብረት ሥራ ማህበራት ቢዝነሳቸውን በማስፋፋት ውጤታማ እንዲሆኑና ለዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ድጋፍ ማድረግ፣

9) ምርትና አገልግሎት ጥራት ላይ መሠረት አሰራር መዘርጋት፣

10) የኅብረት ሥራ ማህበራትን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ትምህርትና ስልጠና፣

11) ለኅብረት ሥራ ማህበራት የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ድጋፍ፣

12) የአገር ውስጥ እና የውጭ የገበያ ትስስር ድጋፍ፣

13) የቁጥጥር እና ተከታታይነት ያለው የቴክኒክ ድጋፍ፣

## ክፍል አሥራ ሦስት

## የኅብረት ሥራ ማህበራት ግንኙነት አግባብ እና የዕቅድ አቀራረብ

### 100. ከአባላት ጋር የሚኖራቸው የግንኙነት ዓይነቶች

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚያደርጓቸው ማናቸውም እንቅስቃሴዎቻቸው ከአባላት፣ ከአደራጅ መ/ቤት፣ ከባለድርሻ አካላት፣ ከአቅም ገንቢዎች እና ሌሎች አካላት ጋር የተለያዩ ግንኙነቶችን ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

2) የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት ጋር የሚኖራቸው የግንኙነት ዓይነቶች በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ የሚገለፅ ሆኖ በዋናነት በሚከተሉት ጉዳዮች ዙሪያ ሊገናኙ ይችላሉ፤

ሀ) በዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ፣

ለ) በሪፖርት አቀራረብና መረጃ አሰጣጥ፣

ሐ) በትምህርትና ስልጠና አገልግሎት፣

መ) ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣

ሠ) በምርትና ፋይናንስ የግብይት አገልግሎት፣

ረ) የሒሳብ አያያዝ ሥርዓት፣

ሰ) በልምድ እና ተሞክሮ ልውውጥ፣

3) የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያቅዱት ማንኛውም እቅድ የአባላትን የፍላጎት ዳሰሳ መሰረት ያደረገ ሆኖ ከአባላት አቅም በላይ የሆኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመፍታት ላይ ትኩረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም አባላት ያላወቁት እና ያላጸደቁት እቅድ መኖር የለበትም፡፡

4) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የዋና ዋና ተግባራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በሩብ ዓመት አንድ ጊዜ በስራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 100 ንዕስ አንቀጽ 4 መሰረት ለኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ሆነ ለማንኛውም አካል የሚቀርብ ሪፖርት እንደየኅብረት ሥራ ማህበራት አይነት የሚለያይ ሆኖ ቢያንስ በሚከተሉት ተግባራት ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት፤

ሀ) የአባላት የግብይት ተሳትፎ፣

ለ) የምርት ግብይት አፈጻጸም፣

ሐ) የግብርና ምርት መሳደጊያ ግብዓቶች አቅርቦትና ስርጭት፣

መ) የሒሳብ ሪፖርት፣

ሠ) የፋይናንስ አቅርቦት፣

ረ) የቁጠባ አሰባሰብ፣

ሰ) የብድር አሰጣጥ፣

ሸ) የብድር እና ዕዳ አመላለስ፣

ቀ) የፍጆታ ምርት አቅርቦትና ስርጭት፣

በ) ያጋጠሙ ችግሮች፣

ተ) በተመረጡ ሌሎች ጉዳዮች፣

6) የኅብረት ሥራ ማህበራት ግልፅነትን ለመፍጠር ሲባል ዋና ዋና የተግባራት አፈፃፀም መረጃዎችን በየግማሽ ዓመቱ አባላት ሊያዩ በሚችሉባቸው ቦታዎች ላይ ሊለጥፉት ይችላሉ፡፡ አባላት ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራቸው ተገቢውን መረጃ በወቅቱ እንዲያገኙ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

7) አባላት እና ሌሎች አካላት የአፈጻጸም መረጃ በጠየቁ ጊዜ መረጃ ማግኘት አለባቸው፤ የተለያዩ ሚዲያዎች በመጠቀም መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

8) በሩብ ዓመት በስራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ የጸደቀ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለአደራጅ መ/ቤት መቅረብ አለበት፡፡

9) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሂሳብ መግለጫዎችን በወቅቱ በማዘጋጀት የሀብትና ዕዳ ሁኔታ ለአባላት ግልጽ ማድረግ አለባቸው

10) ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን የኅብረት ሥራ ጽንሰ ሃሳብ፣ ጠቀሜታና ፋይዳ፣ ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት እና ሌሎች በጥናት በተለዩ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ስልጠና የሚሰጡበት የጸደቀ በጀት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

11) ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላትም ሆነ ለአከባቢው ማህበረሰብ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በተለይ በቴክኖሊጂ አጠቃቀም፣ በተሻሻሉ የግብርና ዘዴዎች፣ በሜካናይዜሽን፣ በእሴት መጨመር፣ በፋይናንስ ትስስር እና በኅብረት ሥራ ጽንሰ ሀሳብ ላይ የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት አለባቸው፡፡ ለሚሰጡት የኤክስቴንሽን አገልግሎት ጥናት ላይ የተመሰረተ ተመጣጣኝ ክፍያ ሊያስከፍሉ ይችላሉ፡፡

12) አባላት ምርትን በጥራት፣ በብዛት እና በወቅቱ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ማቅረብ አለባቸው

13) የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የግብይት አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚከተሉት ግዴታዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል፤

ሀ) አባላት ለምርትና አገልግሎት የሚፈልጉትን ፋይናንስ የብድር አገልግሎት ማመቻቸት፣

ለ) ለአባላት የገበያ መረጃ መስጠት አለባቸው

ሐ) ለአባላት በምርት ጥራት እና በአጠቃላይ የግብይት አሰራር ላይ ግንዛቤ መፍጠር፣

መ) ጥራትን መሰረት ያደረገ ክፍያ ስርዓት መተግበር፣

ሠ) በምርት ዋጋ ትመና ላይ ለአባላት ግልጸኝነት መፍጠር፣

ረ) የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የፍጆታ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ፣

ሰ) በአባለት ምርት ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ ማቅረብ፣

ሸ) የአባላትን ምርት በማስተዋወቅ እና የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት ምርቱን መሸጥ፣

ቀ) የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ምርት በስፋት መሰብሰብ፣

14) አባላት ለኅብረት ሥራ ማህበራቸው ለማቅረብ በዕቅድ ያጸደቁትን ምርት አሟልተው በወቅቱ ማስገባት አለባቸው፤

15) አባላት ያላቸውን ዕጣ መጠን ማሳወቅ እና የዕጣ ምስክር ወረቀት መስጠት አለባቸው፤

16) የእርሻ መሳሪያዎችን እና የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በአንድ ማዕከል እንዲያገኙ ማድረግ፣

## 101. <u>በመሠረታዊ በኅብረት ሥራ ማህበራት እና ዩኒዬን መካከል ስለሚኖር ግንኙነት</u>

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን የዋና ዋና ተግባራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ለአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፣

2) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ለአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ባለሙያዎችን በመቅጠር የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን ለአበል ግለሰቦች አገልግሎት እንዲሰጡ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

3) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች አገልግሎት አሰጣጣቸውን ለማዘመን የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን ማሟላት አለባቸው፤

4) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች በጥናት ላይ በመመስረት ለመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ወሳኝ የሆኑ መሰረተ ልማቶችን እንደ መጋዘን፣ ጽ/ቤቶች እና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን እንዲሁም የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የመጠጥ ውሃ፣ የኤሌክሪክ ኃይል፣ መንገድ፣ ድልድዮች በዕቅድ እያጸደቁ ማሟላት አለባቸው፡፡

5) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አመራሮች የአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮችን መደገፍ፣ ማብቃት፣ ልምድን ማካፈል፣ የአመራርነት ክህሎት የሚያገኙባቸውን ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር አለባቸው፡፡

6) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ የአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን፣ ቅርንጫፎችን እና መሸጫ ሱቆችን በዕቅድ አፈጻጸም እና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የባለሙያ ድጋፍና ክትትል ማድረግ አለባቸው፣

7) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በዕቅድ ዝግጅትም ሆነ በእቅድ አፈጻጸም ግምገማ ላይ አባላትን በንቃት ማሳተፍ አለበት፣

8) ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች ወቅታዊ የሆኑ የተለያዩ መረጃዎችን በማሰባሰብና በመተንተን ለአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በማቅረብ በመረጃ ላይ የተመሰረተ የምርትና አገልግሎት ግብይት እንዲፈጸም ማድረግ አለባቸው፣

9) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒኖች የፋናንስ አቅም ለሌላቸው አባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ አያያዝ ባለሙያዎችን መቅጠር መደገፍ እንዲሁም በጀት በመመደብ ሂሳባቸውን ኦዲት ማስደረግ አለባቸው።

10) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን ለአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት እድገት ወሳኝ የሆኑ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የማቅረብ እና የተለያዩ ንብረቶች እና ማሽኖች መጠቀም የሚችሉበት አሰራር መዘርጋት ይገባል።

11) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን ለአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ በማካሄድ እንዲሁም የግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት ማቅረብ አለበት፣

## 102. <u>በኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን እና ዩኒዩን መካከል ስለሚኖር ግንኙነት</u>

1) የኅብርት ሥራ ፌዴሬሽን ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት አጋዥ የሆኑ ፕሮጀክትና ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ሀብት ያፈላልጋል፡፡
2) ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩኖች ለሚሰጧቸው ስልጠናዎች ምቹ የስልጠና ቦታዎችን በራሳቸው ወይም ከሌሎች አካላት ጋር በመቀናጀት ማመቻቸት አለባቸው፡፡ ሆኖም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ስልጠና የሚሰጡበት የራሳቸው የስልጠና ማዕከል ሊኖራቸው ይገባል፤
3) የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን የውጭ ሀገር ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በመቀመር በአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባራዊ እንዲደረግ ይደግፋል፤
4) የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማመንጨት ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩኖች እና መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲተገብሩ ድጋፍ ያደርጋል፡፡
5) የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የግብርና እና የኢንዱስትሪ የፍጆታ ምርቶችን በጅምላ እና በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ አለባቸው፡
6) የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን የማሽነሪ ጥገና አገልግሎት ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩኖች እና መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት መስጠት አለባት፤
7) የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን ከአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ የሚረከበውን ምርት በማቀነባበር ለገበያ ማቅረብ አለባቸው፣
8) የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን ጥናትና ምርምር ከሚያደርጉ አካላት ጋር በመቀናጀት በኅብረት ሥራ ማህበራ ጉዳይ ላይ ጥናትና ምርምር ያካሄዳል፡፡ ግብይትን ተደራሽ ለማድረግ ዓለም አቀፍ ግንኙነት ስራዎችን ይሰራል፤
9) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩኖች ለአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ ሰራተኛ በመቅጠር የሂሳብ ዝርጋታ አገልግሎት መስት አለባቸው፣
10) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩኖች በጀት በመመደብ የአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ሂሳብ ኦዲት እንዲደረግ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፣
11) በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን የሚገኙ የተለያዩ ንብረቶችና ማሽኖችን መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት መጠቀም ቢፈልጉ በዩኒዩኑ ውስጠ ደንብ በሚጸድቅ አሰራር መሰረት መጠቅም ይችላሉ፡፡
12) የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት የእርሻ መሳሪያዎችና የማሽነሪዎች መለዋወጫዎችን አቅርቦትና የጥገና አገልግሎት መስጠት አለባቸው፣
13) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን በተለይ ለአባል ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት ወሳኝ የሆኑ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ ተግባራዊ እንዲሆን
14) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ በማካሄድ ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ግልጽ ማድረግ አለባቸው፡፡
15) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ለአባላት ኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት መስጠት፣

## 103. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት እና አግባብ ያለው ባለስልጣን ግንኙነት</u>

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት አግባብ ያለው ባለስልጣን ጋር የሚኖራቸው የግንኙነት ዓይነቶች በመተዳደሪ ደንባቸው ውስጥ የሚገለፅ ሆኖ በዋናነት በዕቅድ ዝግጅት፣ በሂሳብ፣ ኦዲት፣ ህግ አገልግሎትና ብቃት ማረጋገጫ ምዘና ድጋፍና ክትትል፣ በግምገማና ግብረ-መልስ ሪፖርት፣ በቁጥጥር፣ በመረጃ ልውውጥ ዙሪያ ሊገናኙ ይችላሉ፤

2) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በጠቅላላ ጉባዔ የጸደቀ እቅድ እና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በየደረጃው ላለ አግባብ ያለው ባለስልጣን በወቅቱ ማቅረብ አለበት፡፡

3) በየደረጃው ያሉ አግባብ ያለው ባለስልጣን ለኅብረት ሥራ ማህበራት በዕቅድ ትግበራ እና በሪፖርት ዝግጅት ላይ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡፡

4) በየደረጃው ያለ አግባብ ያለው ባለስልጣን ኅብረት ሥራ ማህበራት የተሰማሩበትን የስራ መስክ እና ያሉበትን የአፈጻጸም ደረጃ መሰረት ያደረገ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር አለባቸው፡፡

5) በየደረጃው ያለ አግባብ ያለው ባለስልጣን ኅብረት ሥራ ማህበራት ህግና ስርዓት ተከትለው እንዲቀሳቀሱ ጠንካራ የድጋፍ አሰጣጥ ስርዓት ዘርግቶ መደገፍ አለባቸው፡፡

6) በየደረጃው ያለ አግባብ ያለው ባለስልጣን በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ የመረጃ ስርዓት ግንባታ እንዲጠናከር ሙያዊ ድጋፍ መስጠት አለባቸው፡፡

7) በየደረጃው የሚገኝ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ያለው ባለስልጣን የሚጠይቃቸውን አጠቃላይ የኅብረት ሥራ ማህበሩን መሰረታዊ መረጃ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ አግባብ ላለው ባለስልጣን ማስተላለፍ አለባቸው፡፡

8) አግባብ ያለው ባለስልጣን ለምርትና አገልግሎት፣ለግብይት እና ለኅብረት ሥራ ማህበራት እድገት የሚጠቅም መረጃ በፈለጉ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡

9) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዮኖችና ፌዴሬሽን በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ዓመታዊ እቅዳቸውን በማሳወቅ እንዲሁም የዋና ዋና ተግባራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ አግባብ ላለው ባለስልጣን በጽሑፍ ማቅረብ አለባቸው፡፡

## 104. <u>ኅብረት ሥራ ማህበራት እርስ በርስ የሚኖራቸው ግንኙነት</u>

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚኖራቸው የግንኙነት ዓይነቶች በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ የሚገለፅ ሆኖ በዋናነት ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የዓላማ፣ የመርህ እና እሴት አንድነትን መሰረት በማድረግ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በሚከተሉት ጉዳዮች፤

ሀ) በቴክኒካል ድጋፍ፣

ለ) በአሰራርና አመራር ልምድ ልውውጥ፣

ሐ) እርስ በርስ በመማማር፣

መ) በቅንጅት በመስራት፣

ሠ) በፋይናንስ ትስስር፣

ረ) በግብይት ትስስር፣

ሰ) በመረጃ ልውውጥ እና

ሸ) ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ የርስ በርስ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

2) አምራች እና የሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት በቅድ ዝግጅት ሂደት መረጃ መለዋወጥ ይኖርባቸዋል፡፡

3) አምራች እና የሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት እቅድ አፈጻጸማቸውን በጋራ የሚገመግሙበት ስርዓት ዝርግተው ተግባራዊ ያደርጋሉ

4) የኅብረት ሥራ ማህበራት የጋራ የምክክርና የውይይት ፎረም በማዘጋጀት የጋራ ተጠቃሚነትን ማሳደግ ይችላሉ፡፡

5) አምራችና ሸማች ኅብረት ማህበራት የጋራ ዓላማ፣ መርህ እና እሴትን መሰረት ያደረገ፣ በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ የተመሰረተ የመተጋገዝ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

6) ሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን የግብይት ፍላጎት በመለየት ከአምራች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ዘላቂ የግብይት ትስስር ውል በመግባት መተግበር አለባቸው፡፡

7) አምራች ኅብረት ሥራ ማህበራት በውላቸውን መሰረት ለሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት ምርት ማቅረብ አለባቸው፡፡

8) ሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራት በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ገንዘባቸውን በመቆጠብ ግንኙነታቸውን ማጠናከር ይችላሉ፡፡

9) የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በፋይናንስ፣ በግብይት እና በመሰረተ ልማት እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ እርስ በርስ በመደጋገፍና በመተባበር የኅብረት ሥራ ማህበራትን ችግር በራስ አቅም የመፍታት ግንኙነት ይኖራቸዋል፡፡

10) የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ለሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ስለ ፋይናንስ ግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ የቁጠባና ኢንቨስትመንት ግንዛቤ ከማሳደግ አንጻር የድርሻቸውን መወጣት አለባቸው፡፡

11) በኅብረት ሥራ ማህበራት እና በተለያዩ ባንኮች መካከል የሚኖራቸው ግንኙነት ለኅብረት ሥራ ማህበራት ለማምረትና ለግብይት የሚሆን ብድር በማመቻቸት ይሆናል፡፡

12) ኅብረት ሥራ ማህበራት ከዓላማቸው ውጭ በኢንቨስትመንት ስም ከተለያዩ ባንኮች ውስጥ አክስዮን እየገዙ ባለቤት መሆን የለባቸውም፡፡

13) በተለያዩ ኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ በተለያየ ምክንያት ያለአገልግሎት የተቀመጡ ገንዘቦች ስራ ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ በማመቻቸት መተግበር አለባቸው፡፡

## 105. ኅብረት ሥራ ማህበራት ከባለድርሻ እና ከአቅም ገንቢ አካላት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት ከባለድርሻ እና አቅም ገንቢ አካላት ጋር የሚኖራቸው የግንኙነት ዓይነቶች በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ የሚገለፅ ሆኖ በዋናነት በትምህርትና ስልጠና፣ በመሰረተ ልማት ግንባታ፣ በሰው ሃይል ቅጥር እና በቴክኖሎጂና እውቀት ሽግገር እና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ሊገናኙ ይችላሉ፡፡

2) ከባለድርሻ እና ከአቅም ገንቢ አካላት በጥናት በተለዩ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠት ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖራቸው ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

3) ባለድርሻ እና ከአቅም ገንቢ አካላት በኅብረት ሥራ ማህበራት ለሚከፈቱ የትምህርትና ስልጠና ማዕከላት የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ ግብዓቶችን በማሟላት ማጠናከር ይኖርባቸዋል፡፡

4) ባለድርሻ እና ከአቅም ገንቢ አካላት ላኅብረት ሥራ ማህበራት ትምህርትና ስልጠና ተግባራት የሚያግዙ የበጀትና ሎጀስቲክ ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

5) ባለድርሻ እና ከአቅም ገንቢ አካላት የኅብረት ሥራ ማህበራትን በመጋዘን፣ በጽ/ቤት፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ፣ በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት ግንባታ እና ሌሎች የመሰረተ ልማት ችግሮችን በማቃለል ሂደት ላይ በጋራ መስራት አለባቸው፡፡

6) ባለድርሻ እና ከአቅም ገንቢ አካላት በራሳቸው አቅም ሰራተኛ መቅጠር ለማይችሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ ባለሙያዎችን በመቅጠር ኅብረት ሥራ ማህበራት በተማረ የሰው ኃይል እንዲመሩ በመደገፍ ግንኙነታቸውን ማጠናከር አለባቸው፡፡

7) የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለመደገፍ በሀገሪቱ ሕግ ተመዝግቦ የሚሰራ ማንኛውም አቅም ገንቢ አካል ስለሚሰጠው ድጋፍ አስመልክቶ አግባብ ካለው ባለስልጣን ጋር በመግባባት አቅዶ መስራት ይኖርበታል፡፡

# ክፍል አሥራ አራት

# ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት እና ኢንስፔክሽን

## 106. ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት አገልግሎት

1) የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ ዘመን እንደ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ ባህሪ የሚለያይ ቢሆንም ከመስከረም እስከ ሰኔ ድርስ ያለው የሥራ ዘመን ይሆናል፣

2) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 50 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጤናማነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ዘመናው የሂሳብ አሰራር ስርዓት በመዘርጋት በኦዲት ተደራሽ በማድረግ በአባላት እና በሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ዘንድ የሚኖራቸውን ታማኝነት መገንባት ይኖርበታል፡፡

3) የኅብረት ሥራ ማህበራትን ተከታታይነት ያለው የፋይናንስ አስተዳደር፣ የስራ አመራር እና የማህበራዊ ኃላፊነት አፈጻጸም ደረጃ ያለበትን ሁኔታ አግባብ ባለው ባለስልጣን ኦዲት ይደረጋል፡፡

4) የኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ የፋይናንስ እና አሰራራቸውን የሚቆጣጠሩ ተቀጣሪ የውስጥ ኦዲተሮች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡

5) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 50 (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኅብረት ሥራ ማህበራት በግል ኦዲት ማካሄድ አቅሙ የሌለው ወይም በቀላሉ በአካባቢው የግል ኦዲት ተቋማት ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑ ሲረጋገጥ አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በውጭ አካለት ኅብረት ሥራ ማህበራቱን ኦዲት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

6) የኅብረት ሥራ ማህበራትን ኦዲት የሚያደርግ ማንኛውም አካል ከማንኛውም ጣልቃ ገብ አሰራር ነፃ ሆኖ የኦዲት ስራውን በነፃነት ማከናወን ይኖርበታል፡፡

7) የኅብረት ሥራ ማህበራትን ሂሳብ ለኦዲት ዝግጁ በማድረግ የሚደግፍ ባለሙያ ቢያንስ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል፣

ሀ) የሂሳብ ሰነዶችና መዛግብት

ለ) የመተዳደሪያ ደንብና የውስጥ ደንብ፣

ሐ) የሂሳብና የኦዲት ሌሎች የተግባራት ማስፈፀሚያ መመሪያዎች፣

መ) በኦዲት ወቅት የተሰጡ ሙያዊ አስተያየቶች እና ግብረ መልሶች እና የተሰጡ የማስተካከያ እርምጃዎች፣

ሠ) በውስጥ ኦዲት፣ በቁጥጥር ኮሚቴ እና በኢንስፔክተሮች የተገኙ ግኝቶችና የተሰጡ ግብረ መልሶች፣

ረ) ከተለያዩ አካላት ጋር የተደረጉ ውሎችና ስምምነቶች፣

ሰ)የሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ቃለ-ጉባዔዎችና ውሳኔዎች፣

ሸ) ለአባላት የሚቀርቡ እቅዶችና የአፈፃፀም ሪፖርቶች፣

8) በኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ እንዲዘረጋ ለማድረግ የሂሳብ ዝርጋታ ባለሙያ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፣

ሀ) በየእለቱ ሂሳባቸውን መመዝገቡንና በየወሩ ሂሳባቸው መዝጋት የሚችሉ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ይለያል፡፡

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበራት ካለፈው የበጀት አመት ማጠናቀቂያ ሂሳባቸውን ዘግተው ለኦዲት ዝግጁ ማድረጋቸውን ያረጋግጣል፡፡

ሐ) ኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳባቸው ለማስመርመር ዝግጁት ማድረጋቸውን ያረጋግጣል፣ በቂ በጀት መኖሩን ያረጋግጣል፡፡

መ) በፌዴራል ወይም በክልል ደረጃ ሂሳባቸውን ኦዲት ለማድረግ የተዘጋጁ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ዝርዝር መዝግቦ መረጃ ይይዛል፡፡ በወቅቱ ኦዲት እንዲደረጉ ዝርዝራቸውንም ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፡፡

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳባቸውን የሚዘረጋ ባለሙያ እንዲኖራቸው ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ በሕጉ መሰረት መከናወኑንም ይከታተላል፣

ረ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ ዝርጋታ ባለሙያ በየጊዜው የፋይናንስ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለአመራር አካላት ማቅረቡን ይከታተላል፣

ሰ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ ዝርጋታ ባለሙያ ያዘጋጀው የፋይናንስ ሪፖርት በሂሳብ መመሪያው እና ማንዋል መሠረት መሆኑን ይገመግማል፣ ተቀባይነት ያለው ለመሆኑ አስተያየት ይሰጣል፡፡

ሸ) ኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራ ለማሳካት አስፈላጊውን የሂሳብ ዝርጋታ ሥራ ላይ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 107. የኢንስፔክሽን ግብረ መልስ አጠቃቀም

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 52 (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በኢንስፔክሽን ግብረ መልስ መሠረት ህግ፣ ደንብና አሰራር መሠረት በአግባቡ እያከናወኑ መሆናቸውን አግባብ ባለው ባለስልጣን መረጋገጥ ይኖርበታል፤

2) በየደረጃው ያሉ ለኅብረት ሥራ ማህበራት በማጠናከር ድጋፍ የሚያደርጉ ባለሙያዎች በኢንስፔክሽን ምርመራ ውጤት የተሰጡ ሙያዊ አስተያየቶች እና ግብረ መልሶች ኅብረት ሥራ ማህበራት የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፡፡

3) የኅብረት ሥራ ማህበራት የኢንስፔክሽን የተሰጡ ግብረ መልስ ውጤቶች ለጠቅላላ ጉባዔ በማቅረብ በማጸደቅ ግልፅ በሆነ ስፍራ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

# ክፍል አሥራ አምስት

# ስለኅብረት ሥራ ማህበራት ውህደት እና መከፈል

## 108. ስለኅብረት ሥራ ማህበራት ውህድት

1) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በጥናት በተለዩ ወይም በታመነባቸው ምክንያቶች የመዋሃድ ጥያቄ ለጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ልዩ ውሳኔ ቀርቦ ከ2/3ኛ በላይ አብላጫ ድምፅ ካገኘ የመዋሃድ ተግባር የሚከናወን ይሆናል፤

2) መዋሃድ የሚችሉት ተመሳሳይ አላማና ተግባር ያላቸው እና በተመሳሳይ የአደረጃጀት እርከን ላይ ያሉ አቻ የሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት መሆን አለበት፣

3) ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ በተመሳሳይ የአደረጃጀት እርከን ላይ ኅብረት ሥራ ማህበራት ሲዋሃዱ አዲስ ኅብረት ሥራ ማህበር ይመሠረታል፡፡

4) በየደረጃው ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች ተመሣሣይ ዓለማና ተግባር ያላቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የሚዋሃድ ከሆነ መጀመሪያ መዋሄዱ አግባብነት ያለው መሆኑን በህጉ መሰረት መፈጸም አለበት፡፡

5) የሚደረገው የኅብረት ሥራ ማህበራት ውህደት የአባላትን ፍላጎት ወይም የህዝብን ጥቅም የሚጻረር መሆን የለበትም፡፡ የሚደረገውም ውህደቱም በሚዲያዎች አማካኝነት ሕዝቡ እንዲያውቀው ይፋ መደረግ አለበት፣

6) ለውህደት የሚቀርቡት በየደረጃው ያሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት በተናጥል በየራሳቸው ጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ድጋፍ ካላገኙ የውህደት ጥያቄው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

7) ብቁና ጠንካራ ሆነው ለመስራት እንዲችሉ ተመሣሣይ ዓላማና ተግባር ያላቸው፣ በአንድ የስራ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት በአንድ ላይ ሊዋሃዱ ይችላሉ፣

8) በሚዋኸዱበት ጊዜ ቀድሞ የነበረው ሕጋዊ የምስክር ወረቀት አግባብ ላለው ባለስልጣን በመመለስ ህልውናቸውን ያጣሉ፣

9) የኅብረት ሥራ ማህበራቱ ውህደቱን ከመፈፀማቸው አስቀድመው በፊት በልዩ የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መጽደቅ አለበት፣

10) የኅብረት ሥራ ማህበራቱ ከመዋሀዳቸው በፊት በተናጠል የሂሳብ ምርመራ በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበሩ እዳ ካፒታልና ንብረት መለየት አለበት፣

11) ከውህደቱም በኃላ የአባላት መብትና ግዴታ አዲስ በተመሰረተው ኅብረት ሥራ ማህበር ይከበርላቸዋል፣

## 109. <u>ውህደት የሚፈጸምባቸው ምክንያቶች</u>

1) ከሚከተሉት ሚክንያቶች በመነሳት ከሁለት በላይ የሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ውህደት ሊፈጥሩ ይችላሉ፡-

ሀ) የሚዋሀዱ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት ቁጥር በህግ ከተወሰነው የአባላት መነሻ ቁጥር በታች ሲሆን፣

ለ) የአካባቢውን ሀብት በጋራ ተቀናጅቶ በመጠቀም ብቃትን ለማሳደግ

ሐ) የተሻለ የስራ አመራር ስርዓት ለማምጣት፣

መ) የካፒታል መጠን ዝቅተኛ መሆን፣

ሠ) አቅም በመፍጠር የጋራ ፕሮጀክቶችን በአንድ ላይ ሆኖ ተግባራዊ ለማድረግ፤

ረ) ደካማ አፈጻጸም ያላቸውን በማዋሃድ ጠንካራ እና ውጤታማ የኅብረት ሥራ ማህበር ለመፍጠር፤

ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ

ሰ) የአገልግሎት አሰጣጥ አድማሳቸውን በማስፋት ቀልጣፋና ተደራሽ አገልግሎት በመስጠት የአባላትን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣

ሸ) ከመንግስት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተሻለ አገልግሎት እና ሙያዊ ድጋፍ ለማግኘት፣

ቀ) በአንድ የሥራ ክልል ውስጥ የሚኖረውን የሥራ ድግግሞሽ እና እርሰበርስ በመወዳደር የሚፈጠረውን የጥቅም ግጭት ለማስቀረት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 (ሀ- ቀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ውህደቱ ከአንድ የኅብረት ሥራ ማህበር ወደ ሌላ የኅብረት ሥራ ማህበር እዳ እንዳያስተላልፍ ሲባል ለሁሉም አበዳሪዎች ስለ ውህደቱ ቢያንስ ከሦስት ወራት አስቀድሞ በማስታወቂያ መጥራት አለበት።

3) የማንኛውም የሚዋሃዱ የኅብረት ሥራ ማህበራት አበዳሪዎች ውህደቱ እንዲካሄድ ከተወሰነው ቀን ቢያንስ አንድ ወር በፊት በጽሁፍ ውህደቱን ለሚያስፈጽመው አካል ጥያቄ ካቀረቡ ማንኛውንም እዳ ወይም ገንዘብ የማግኘት መብት አላቸው።

## 110. የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚከፈሉባቸው ምክንያቶች፣

ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ በሁለትና ከዚያ ባላይ ሊከፈል ይችላል፡-

1) የአባላቱ ቁጥር ብዙ ሆኖ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለሁሉም አባላት በቂ አገልግሎት ተደራሽ ሳይሆን ሲቀር፣
2) ከስራ ቦታ ስፋት የተነሳ ሌላ ተጫማሪ ቅርንጫፎችን ከፍቶ አገልግሎት ለመስጠት የማይቻል ሆኖ መከፈሉ የተሻለ አማራጭ መፍጠሩ ሲታመንበት፣
3) በመከፈሉ ዝቅተኛ እና ደካማ የሆነውን የአባላት ተሳትፎ ማሻሻሉ ሲታመንበት፣
4) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ከመልክዓ-ምድር አቀማመጥ ወይም በአስተዳደር አከላለል ምክንያት ለማስተዳደር እና ለአገልግሎት አሰጣት መከፈሉ አሳማኝ ሆኖ ሲገኝ፣
5) መከፋፈሉ ያለው ጠቀሜታ ሲታመንበትና በጥናት ሲረጋገጥ፣
6) አባላት ፍላጎት የተለያየ ሲሆንና ማሳካት ሳይቻል ሲቀር፣
7) አባላት መከፈሉን አምነውበት ጥያቄ ሲቀርቡ፣
8) የኅብረት ሥራ ማህበሩ በመከፈሉ የሚፈጠሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት የካፒታል አቅማቸው የማይዳከም ሲሆን፣
9) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ያለበት ሁኔታ ለአመራርና ለአስተዳደር የማይመች ሲሆን፣

## 111. የውህደት ወይም የመከፈል ልዩ ውሳኔ አፈጻጸም

1) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወደ ሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊዋሃድ ወይም ሊከፋፈል ይችላል፣
2) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 111 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የመዋሃድ ወይም የመከፈል ተግባር ከመፈፀሙ በፊት የአባላት ሁኔታ፣ የአባላት ሀብት፣ የብድር ዕዳ እና የመጠባበቂያ ገንዘብን በማጣራት የሁሉም ወገኖች ሂሳብ የማጣራት ሥራ የጋራ በማድረግ ሊዋሃዱ ወይም ለከፈሉ ይገባል፡፡
3) የኅብረት ሥራ ማህበራት ውህደት ወይም መከፈል ሲወሰን የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ፡-

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበራትን ሂሳብ ኦዲት እንዲደረግ አግባብ ላለው ባለስልጣን ጥያቄ ማቅረብ፣

ለ) ነባር አባላትን የመረጃ ማሰበሰብ፣ የመደራጀት ፍላጎት ያላቸውን መለየት፣

ሐ) ያሉና የሌሎች ነባር አባላትን አጣርቶ ለውሳኔ በሚመች መልኩ ለጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ፣

መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረት ማሰባሰብ፣ መረጃ ማደራጀትና መመዝገብ፣

ሠ) አዲስ ለሚደራጀው ኅብረት ሥራ ማህበር የሚያግዝ አዲስ መተዳደሪያ ደንብ፣ የንግድ ስራ እቅድ (የቢዝነስ ፕላን) ማዘጋጀት

ረ) አስፈላጊወን የማደረጀት ተግባራትን ማከናወን እና ለምዝገባ ማቅረብ፣

4) ቀደም ሲል ተደራጅተው ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የውህደት ወይም የመከፈል ልዩ ውሳኔ የአፈጻጸም ሂደት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) አስቀድሞ ውህደቱ ወይም መከፈሉ አባላትን በተሻለ ሁኔታ ተጠቃሚ ማድረጉ በጥናት ማረጋገጥ፣

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ መዋሃድ ወይም መከፈል ያለምንም ተፅዕኖ በአባላት ሙሉ ፈቃደኝነትነት መሆኑን በማረጋገጥ፣

ሐ) የውህደት ወይም የመከፈል ውሳኔው በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ቀርቦ በ2/3ኛ ድምፅ ማጽደቁን በማረጋገጥ፣

መ) የተደረገው የውህደት ወይም የመከፈል ውሳኔ ሃሳብ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ቀርቦ ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል፣

ሠ) የአካባቢውን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ እና ጉዳት የማያስከትል መሆኑን በጥናት ማረጋገጥ አለበት፣

ረ) ውህደት ወይም መከፈል እንዲፈጥሩ ውሳኔ የተሰጣቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ የኦዲት ሪፖርቱ በጠቅላላ ጉባኤ ማጸደቅ ይኖርበታል፤

ሰ) በመዋሃድ ወይም በመከፈል ህልውና ያጡት ኅብረት ሥራ ማህበራት ሲጠቀሙባቸው የነበሩት መዛግብት እና ሰነዶች አዲስ በተቋቋመው ኅብረት ስራ ማህበር ጽ/ቤት በጥንቃቄ ይቀመጣሉ፡፡

ሸ) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ከመዋሀዱ ወይም ከመከፈሉ በፊት ለአበዳሪዎች የሚከፈል ዕዳ እያለበት ሊዋሃድ አይችልም፤

ቀ) ዕዳ እያለበት ውህደቱን ወይም መከፈሉን የተቀበሉና የወሰኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ለተሰናበቱ አባላት ወይም ለዕዳ ጠያቂዎች የክፍያ ዋስትና መስጠት ይኖርበታል፡፡ በሰጡት የክፍያ ዋስትና መሠረት የሚደርስባቸውን የገንዘብ መጠን መደልደል አለበት፡፡

በ) የማፍረስ ሕግን ተከትለው ህልውናቸውን እንዲያጡ ማድረግ፣

5) በዋስትና የሚቀመጠው ገንዘብ ወይም ንብረት ህልውናውን ያጣው ኅብረት ሥራ ማህበር የተሰናበቱ አባላት ወይም የዕዳ ጠያቂዎች ስለሆነ ይህ ግዴታ በቀጥታ በውህደት ወይም በመከፈል ወደ ተፈጠሩት ኅብረት ሥራ ማህበራት ይተላለፋል፡፡

6) ዋስትና የተቀመጠላቸውም አባላት እና ዕዳ ጠያቂዎች ድርሻቸውን እና ሂሳባቸውን በውህደት ወይም በመከፈል የተፈጠረውን ኅብረት ሥራ ማህበር የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

7) በውህደት ወይም በመከፈል ህልውናቸውን ወደ አጡት ኅብረት ስራ ማህበራት ይገባ የነበረ ወይም ይገኝ የነበረ ጥቅም ካለ መብቱ በቀጥታ አዲስ ወደ ተቋቋሙት ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

8) ቀድሞ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም ተመዝግቦ ያሉት የሚከፋፈሉ ንብረቶችን ሕጉን ተከትሎ የሚዘጋጅ ይሆናል፣

9) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሲዋሃዱ ወይም ሲከፈሉ ቀድሞ የነበሩት ቅጥር ሠራተኞች ያላቸውን የሥራ አፈፃፀም ብቃት፣ የሥነ መግባር፣ ኅብረት ሥራ ማህበሩን የካፒታል አቀም እና የሥራ ፍሰት ከግምት ውስጥ በማስገባት በማወዳደር ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ ይቻላል፡፡

10) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 111 ንዑስ አንቀጽ 9 የተገለፀው እንደተተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሲዋሃዱ ወይም ሲከፈሉ ቀድሞ የነበሩት ቅጥር ሠራተኞች ጉዳይ በሀገሪቱ አሰሪና ሠራተኛ ህግ እና በውላቸው መሠረት የሚታይ ይሆናል፡፡

11) የንብረት ክፍፍሉም በሂሳብ አጣሪው አማካኝነት ተጠንቶ ለውሳኔ የሚቀርብ ይሆናል፣

12) ህሊውናቸውን ያጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከመዝግብ መሰረዝ ይኖርባቸዋል፡፡

## 112. <u>በውህደቱ ወይም በመከፈሉ ላይ ተቃውሞ ሲቀርብ ስለሚወሰድ ህጋዊ እርምጃ፣</u>

1) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በሚደረገው ውህደት ወይም መከፈል ላይ ተቃውሞ ሲቀርብ የሚከተሉት እርምጃዎች ሊወሰዱ ችላሉ፤

ሀ) ከአባላት ወይም ከዕዳ ጠያቂዎች መካከል ያልተስማማ ወገን ካለ ልዩ ውሳኔው ከመፈጸሙ በፊት መብታቸው የሚጠበቅበት ውሳኔ እና ድርሻቸው መቀመጥ ወይም የክፍያ ዋስትና መሰጠት አለበት፡፡

ለ) አግባብ ያለው ባለሥልጣን ውሳኔውን የሚቀበለው እና አዲስ ኅብረት ስራ ማህበር የሚመዘግበው እና ዕውቅና የሚሰጠው የአባላት ወይም የዕዳ ጠያቂዎች መብት መጠበቁን እና ሌሎች ህጋዊ ክፍያዎች መፈጸማቸውን ካረጋገጠ በኋላ ይሆናል፡፡

ሐ) በውህደት ወይም በመከፈል ላይ ተቃውሞ ያላቸው አካላት ውህደት ወይም መከፈል ከመደረጉ አስቀድሞ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ እና አግባብ ላለው ባለስልጣን ቅሬታቸውን ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፣

መ) የመዋሃድ ወይም የመከፈል የአባላትን መብት ወይም የዕዳ ጠያቂዎችን እና የቅጥር ሰራተኞችን መብት ያልጠበቀ ከሆነ ወይም ሥራው ህግን እና ሥርዓትን ያልተከተለ መሆኑ ከተረጋገጠ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የውህደቱን ወይም የመከፈሉን ጥያቄ ሊሠርዘው ወይም ሊያዘገየው ይችላል፡፡

ሠ) ውህደቱን ወይም መከፈሉን የተቃወሙ አባላት፣ ወይም ዕዳ ጠያቂዎች እና ቅጥር ሠራተኞች የሚገባቸው ክፍያ በአግባቡ መቀመጡን ወይም ዋስትና መሰጠቱን፣ ወይም በሥራው ሂደት ላይ ግልጽነት ያለመኖሩን ማስረጃ ከቀረበ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ውህደቱን ወይም መከፈሉን ሊያዘገየው ወይም ሊሰርዘው ይችላል፡፡

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሚወሰን የመከፈል ወይም የመዋሃድ ውሳኔ ከማንኛውም ጣልቃ ገብነት ነፃ በሆነ መልኩ ይከናወናል፣

## 113. <u>በመዋሃድ ወይም በመከፈል እንደገና ስለሚደራጅ ኅብረት ሥራ ማህበር</u>

1) በመዋሃድ ወይም በመከፈል እንደገና የሚደራጅ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በጥናት ላይ በመመስረት የስራ ክልል ሁኔታ፣ የካፒታል ምስረታ፣ የመሰረተ ልማት እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች አስቀድሞ የሚከናወኑ ይሆናል፣

2) በመዋሃድ ወይም በመከፈል እንደገና የሚደራጅ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መደበኛውን የማደራጀት ሂደት ተከትሎ ተደራጅቶ የሚመዘገብ ይሆናል፡፡

3) በመዋሃድ ወይም የመከፈል ተግባር የተሳካና ውጤታማ ለማድረግ እና ሊከሰቱ የሚችሉ አላስፈላጊ የሆኑ ሕገ-ወጥ አሰራሮችን ለማስወገድና የአባላትንና የሦስተኛ ወገን ጥቅምና መብት ማስጠበቅ እንድቻል የተጠናከረ ሙያዊ እገዛ ይደረጋል፡፡

4) ማንኛውም ነባር የኅብረት ሥራ ማህበር በመዋሃድ ወይም በመከፈል በአዲስ መልክ መደራጀት ይችላል፡፡ በመከፈል እንደገና የሚደራጅ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከመከፈሉ አስቀድሞ የአዋጭነት ጥናት በባለሙያ መካሄድና መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

5) በዚህ መመሪያአንቀጽ 113 ንዑስ አንቀጽ 4 እንደተደነገገው በጥናት ውጤቱ መሰረት መልሰው ለሚደራጁት በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ቀርቦ ሲወሰን እና ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ከተወሰነ በኋላ ነባሩ የኅብረት ሥራ ማህበር ህጉን ተከትሎ እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡

6) ሕጉን ተከትሎ የማፍረስ ሂደት ከተካሄደ በኋላ በተጠናው የአዋጭነት ጥናት መሰረት አዲስ የኅብረት ሥራ ማህበር ይደራጃል፡፡

7) በመዋሃድ ወይም በመከፈል የሚደራጅ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የአካባቢውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ እና ሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ እና ጉዳት የማያስከትል መሆኑ በመዝጋቢው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

8) አስፈላጊ በሆነው የማፍረስ ሂደት ውስጥ አልፎ የመጣ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር እንደገና ከሁለት በላይ በመዋሃድ ወይም በመከፈል እንደገና በመደራጀት በአዲስ መልክ ይመዘገባሉ፡፡

9) የኅብረት ሥራ ማህበር በመዋሃድ ወይም በመከፈል በአዲስ መልክ ተደራጅቶ ምዝገባ ሲከናወን በሚከተሉት ሂደቶች መሰረት ይሆናል፡-

   ሀ) በመዋሃድ ወይም የሚከፈሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት ያለባቸውን ዕዳ መክፈላቸው ወይም ዋስትና መስጠታቸውን አግባብ ባለው ባለ ስልጣን መስሪያ ቤት ይረጋገጣል፤

   ለ) ኅብረት ሥራ ማህበራት ለመዋሃድ ወይም ለመከፈል የተስማሙበት የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ-ጉባኤ፣ የአባላትንና አዲስ የተመረጡ አመራር አካላትን ስም፣ አድራሻና ፊርማ እንዲሁም ሌሎች ለምዝገባ የሚያበቁ መስፈርቶችን በማሟላት የምዝገባ ማመልከቻ በጽሁፍ አግባብ ላለው ባለስልጣን መስሪያ ቤት ይቀርባል፤

   ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን በአዲስ በመመዝገብ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ሠርተፊኬት ይሰጣዋል፡፡

10) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሲዋሃዱ ወይም ሲከፈሉ ቀድሞ የነበሩት ቅጥር ሠራተኞች ጉዳይ በሀገሪቱ አሰሪና ሠራተኛ ህግ እና በውላቸው መሠረት የሚታይ ይሆናል፡፡

11) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሲዋሃዱ ወይም ሲከፈሉ ስለማይከፋፈሉ ንብረቶች አስተዳደርና አጠቃቀም ሁኔታ በሚቀርበው የጥናት ውጤት እና በሚደረገው የጋራ ስምምነት መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

12) ቀድሞ የነበሩት ቅጥር ሠራተኞች ጉዳይ በሀገሪቱ አሰሪና ሠራተኛ ህግ እና በውላቸው መሠረት የሚታይ ይሆናል፡፡

13) በዚህ ሁኔታ የሚዋሃዱ ወይም የሚከፋፈሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የራሳቸው ስምና ዓርማ፣ የሥራ ዓይነት፣ ዓላማ፣ ተግባር እና ራዕይ ሊኖራቸው ይችላል፣ ሆኖም ግን ተመሳሳይ እና አሳሳች ሆነው እንዳይመዘገቡ አግባብ ያለው ባለስልጣን ይቆጣጠራል፡፡

## ክፍል አሥራ ስድስት

## ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት መፍረስና ሂሣባቸውን ስለማጣራት

## 114. <u>የሂሳብ አጣሪዎችን ስለመሾም እና መሻር</u>

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 56 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ካለው ባለስልጣና የሚሾሙ የሂሳብ አጣሪ አባላት ቁጥር ሦስት ሲሆኑ አመራረጣቸውም የኦዲት፣ የህግ እና አደራጅ ባለሙያዎች ይሆናል፡፡

2) አንድ የኅብረት ሥራ ማህበር የመፍረስ ውሳኔ ከተሰጠው በኋላ ሂሳቡ እንዲጠራ የሂሳብ አጣሪዎች አግባብ ባለው ባለስልጣን ይመደባሉ፡፡

3) አግባብ ያለው ባለስልጣን የመደባቸውን የሂሳብ አጣዎች ከመመሪያ ውጪ ሲሰሩ ከተገኙ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በማንኛውም ጊዜ በሙሉም ሆነ በከፊል ከሥራቸው ሊያግድ ወይም ሊሽር እና በምትካቸው አዲስ ሊሾም ይችላል፡፡

4) ከሂሳብ ማጠራት ሥራቸው የተሸሩ የሂሳብ አጣሪዎች የስንብት ደብዳቤ ከደረሳቸው ቀን ጀምሮ በሰባት ቀናት ውስጥ በእጃቸው የሚገኘውን ንብረት፣ ማስረጃዎች፣ መዛግብት፣ ሠነዶች እና የመሳሰሉትን በምትካቸው ለተመደቡት ሂሳብ አጣሪዎች የማስረከብ ግዴታ አለባቸው፡፡

5) ከሥራቸው የተሰናበቱ ሂሳብ አጣሪዎች በሰባት ቀናት ውስጥ በእጃቸው የሚገኙትን ንብረቶች እና ሠነዶች ካላስረከቡ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ይጠየቃሉ፡፡

6) የሂሳብ ሥራውን ለማጣራት ለሾሙት የሂሳብ አጣሪዎች አግባብ ያለው ባለስልጣን ተገቢውን የአገልግሎት ዋጋ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዲከፈል ሊወሰን ይችላል፤

## 115. <u>ኅብረት ሥራ ማህበር ሂሳብ ስለሚጣራባቸው ምክንያቶች</u>

1) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ሂሳብ በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ ሊጣራ ይችላል፤

ሀ) ሕልውና እንዲያጣ ሲወሰን፣

ለ) የዕዳ ጠያቂ አካላትን ለመለየት፣

ሐ) የኅብረት ስራ ማህበሩን ሃብት፣ ንብረትና ዕዳ ለመለየት እና የዕጣ ድርሻ ለማወቅ

መ) ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ዕዳዎችን ለመለየት

ሠ) ቅጥር ሰራተኞችን ለመለየት እና ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ

ረ) የማይከፋፈል የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረት ለመለየት፣

ሰ) በመከፈል ወይም በመዋሃድ ፈርሶ ዳግም ለመደራጀት ሲወሰን፣

ሸ) ተመዝግቦ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ሥራውን ያልጀመረ ከሆነ፣

ቀ) ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በቋሚነት ካላስመዘገበ ወይም ጊዜያዊ ምስክር ወረቀቱን የሚመልስ ወይም እንዲመልስ የሚደረግ ከሆነ፣

በ) ሂሳብ ተመርምሮ ኪሳራ ውስጥ የገባ እና የገባበት ኪሳራ በቀላሉ ከኪሳራው በ6 ወራት ውስጥ በመውጣት ወደነበረበት መመለስ የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ተ) ሥራውን በሌላ መልኩ ለመቀየር ሲወስን ወይም ዓላማውንና ተግባሩን ሲቀይር፣

ቸ) የአባላት ብዛት ወይም ቁጥር በሕግ ከተወሰነው በታች ሲቀንስ፣

ነ) ከተቋቋመበት ዓላማና በመተዳሪያ ደንቡ ውስጥ ከተወሰነው ተግባር ውጪ ሲሰራና ዓለም አቀፍ የኅብረት ሥራ መርሆዎችን ጥሶ ሲገኝ፣

## 116. የሂሳብ አጣሪዎች ግዴታ እና ኃላፊነት

7) የሂሳብ አጣሪዎች ተጀምረው ለነበሩት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ውል አፈፃፀም የሚያገለግሉ ሥራዎች ካልሆነ በስተቀር ወይም የሂሳብ ማጣራቱ ሥራ ካላስገደደ በስተቀር አዲስ ሥራዎችን ለመጀመር አይችሉም፡፡ ከዚህ ውጪ ለሚሰሩ ሥራዎች በነጠላም ሆነ በአንድነት ተጠያቂ ናቸው፡፡

8) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ ላይ እስከ መጨረሻው የሂሳብ ማጠቃለያ ጊዜ ያለውን የሥራ እንቅስቃሴ መግለጫ፣ የማህበሩን ሃብትና ሠነዶች በኃላፊነት ይረከባሉ፡፡

9) ኅብረት ስራ ማህበሩ ያለውን የሚከፋፍልና የማይከፋፍል ንብረት ይለያሉ፤ ይሰበስባሉ፤ ተሰብሳቢ ሂሳብ እና ተከፋይ ዕዳ በዝርዝር ያዘጋጃሉ፣

10) ኅብረት ስራ ማህበሩን የአባላት ቁጥር እና ያላቸውን የዕጣ ድርሻ ይለያሉ፣

11) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ እንዲጣራ አስፈላጊ የሆኑትን ተግባራት ሁሉ ይፈጽማሉ፡፡

12) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረት መሸጥ፣ ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሆነው በፍርድ ቤት ቀርበው መከራከርና መገላገል እንዲሁም ነገርን በሽምግልና ዳኝነት ለመጨረስ ሊዋዋሉ ይችላሉ፤

13) በዚሁ ሥራ የተከፈተውን የባንክ ሂሳብ ያስተዳድራሉ፤ ክፍያዎችንም ይፈጽማሉ፣

14) ለሂሳብ ማጣራቱ ሥራ የሚያገለግሉ ወጪዎችን ይወስናሉ፤

15) ከዕዳ ጠያቂዎች ጋር ስለአለው ዕዳና ስለአከፋፈሉ ሁኔታ በመነጋገር ሊወስኑ ይችላሉ፣

16) በኅብረት ሥራ ማህበሩ በማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ወይም ተቋም መካከል ስለአለው አለመግባባት ወይም ክርክር ኅብረት ሥራ ማህበሩን በመወከል በግልግል ወይም በዕርቅ ለመጨረስ ይችላሉ፤

17) ከዕዳ ክፍያ በኋላ በቀረው ገንዘብ ላይ ጠቅላላ ጉባኤውን በማነጋገር ስለአከፋፈሉ ይወስናሉ፣

18) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ላይ የሚጠየቀውን ዕዳ በመመርመር የአከፋፈል ቅደም ተከተል ይስናሉ፣

19) የሂሳብ አጣሪዎች በሾማቸው አካል ሥልጣናቸውን የሚቀንሱ ውሳኔዎች ካልተደረጉ በስተቀር የሂሳብ ማጣራቱን ተግባር ከፍፃሜ ለማድረስ ሙሉ ሃላፊነት ይኖራቸዋል፤

20) የሂሳብ የማጣራት አካሄድ የሚገልፅ የደረሱበትን ዝርዝር ሪፖርት በማዘጋጀት በየሳምነቱ ለሾማቸው ወይም ለመደባቸው አግባብ ያላው ባለስልጣን ማቅረብ አለባቸው፡፡

21) የሂሳብ ማጣራቱ ሥራ ተጠናቆ ውህደቱ ወይም ክፍፍሉ ከተፈጸመ በኋላ በስራ ምክንያት በእጃቸው የገቡትን ማንኛውንም መዛግብትና ሰነዶች በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ በአዲስ ለተቋቋመው ኅብረት ሥራ ማህበራት በጥንቃቄ እንዲቀመጡ ያስረክባሉ፡፡

22) በተባለው ቀን ውስጥ በእጃቸው የሚገኘውን ማንኛውንም የኅብረት ሥራ ማህበር ንብረት እና ሰነድ ከላስረከቡ አግባብ ያለው ባለስልጣን በሕግ መሠረት ይጠየቃሉ፡፡

23) የሂሳብ ማጣራቱ ስራ ሳይጠናቀቅና አግባብ ያለው ባለስልጣን ፈቃድ ሳያገኝ የሂሳብ ማጣራት ስራ ላይ የተመደበ ወይ የተሾመ ማንኛውም ሰው ስለሂሳብ ማጣራቱ ለሌለኛው አካል አሳልፎ መረጃ መስጠት አይችልም፣

24) ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ንብረቶችን ግልጽ በሆነ መንገድ ይሸጣሉ፣ ስም ያዛውራሉ፣ ክፍፍሉ እስኪፈፀምም በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም ተንቀሳቃሽ የባንክ ሂሳብ ከፍተው በኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥም “በማጣራት ላይ ሂሳብ” በማለት ያስቀምጣሉ፣

25) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 116 ንኡስ አንቀ 23 መሰረት ዬትኛውንም መረጃ አሳልፎ የሰጠ ማንኛውንም አካል አግባቢ ያለው ባለስልጣን በድስፐሊን እርምጃ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 117. በሂሳብ ማጣራት ሥራው አግባብ ያለው ባለስልጣን ተግባር እና ኃላፊነት

1) የሂሳብ ማጣራቱን ሥራ በኃላፊነት የሚያካሄደውና በኅብረት ሥራ አዋጅም ኃላፊነት የተሰጠው አግባብ ላለው ባለስልጣን በመሆኑ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

   ሀ) አግባብ ያለው ባለስልጣን በራሱ ተነሳሽነት ባደረገው ሂሳብ ምርመራ ወይም ኢንስፔክሽን ወይም ከአካለት በቀረበለት ጥያቄ መሠረት የመዋሃድ ወይም መከፈል ወይም የማፍረስ ውሳኔ ሲሰጥ የሂሳብ ማጣራት ሥራ እንዲከናወን ያዛል፤

   ለ) የሂሳብ ማጣራት ሥራው ለማካሄድ የማፍረስ ውሳኔው በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ መሰረት መጽደቁን ያረጋግጣል፣

   ሐ) የሂሳብ አጣሪዎችን ይመድባል ወይም የሾማል፤ አስራ አምስት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሂሳብ ምርመራ እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡

   መ) በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀውን የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት እና የመዋሃድ ወይም የመከፈል ወይም ለመፍረስ የተሰጠውን ውሳኔ ቃለ ጉባኤ ለሂሳብ አጣሪዎች ያስረክባል፡፡

2) አግባብ ያለው ባለስልጣን የሂሳብ ማጣራት ሥራውን የሚያዘው፡-

ሀ) 2/3ኛ አባላት የማፍረስ ተግባሩ እንዲከናወን የተስማሙበት በቃለ ጉባኤ እና የማፍረስ ማመልከቻ ሲደርሰው፣

ለ) የአባላት ቁጥር በሕግ ከተወሰነው ዝቅተኛ ቁጥር በታች መሆኑን በማስረጃ ሲያረጋግጥ፣

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ኪሳራ ውስጥ መግባቱንና በቀላሉ ከኪሳራ የማይወጣ መሆኑን ሲያምንበት፤

መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ውጪ ሲሰራ መሆኑን ሲያረጋግጥ፤

ሠ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራ አለመግባቱ ሲያረጋግጥ፣

ረ) በአንድ አመት ውስጥ በቋሚነት ያልተመዘገበ መሆኑን ሲያረጋግጥ መሆን አለበት፤

3) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ ማጣራትና የመዋሃድ ወይም የመከፈል ወይም የማፍረስ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት አግባብ ያለው ባለስልጣን የሰጠው ውሣኔ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ በደብዳቤ መላክ እና በጋዜጣም ማውጣት አለበት፤

4) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የደረሰውን የሂሳብ ማጣራትና የማፍረስ ውሳኔ ከተቃወመ በጠቅላላ ጉባኤና በሥራ አመራር ኮሚቴ ውሳኔ አስወስኖ በ15 ቀን ውስጥ ለአደራጅ መ/ቤቱ ማቅረብ አለበት፣

5) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የመቃወሚያ ደብዳቤውን በ15 ቀን ውስጥ ለአደራጅ መ/ቤቱ ካላቀረበ የማፍረስ ውሣኔውና የሂሳብ ማጣራት ሥራው ተግባራዊ ይሆናል፤

6) አግባብ ያለው ባለስልጣን አሳማኝ የሆነ ምክንያት በማንኛውም ጊዜ ኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዳይፈርስ እና ሂሳብ እንዳይጣራ ያስተላለፈውን ትዕዛዝ ሊሰርዘው ይችላል፡፡

7) የሂሳብ ማጣራት ሥራው እንዲከናወን አግባብ ባለው ባለሥልጣን ከተወሰነ በኋላ የሂሳብ ማጣራት ተግባር በሚከተለው ቅደም ተከተል መሠረት ይከናወናል፡፡

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ ማጣራት ተቃዋሚ ካለ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከነምክንያቱ እንዲቀርብ በተከታታይ ለሁለት ወራት በጋዜጣና አመቺ መንገዶችን በመጠቀም ማስታወቅ አለበት፡፡

ለ) በማስታወቂያው መሠረት በኅብረት ሥራው ላይ ዕዳ ጠያቂዎች የሚያቀርቡትን ማስረጃዎች ዝርዝር በመመዝገብ የማጣራት ሥራ ይከናወናል፤

8) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሁኔታ የሚገልጽ ዝርዝር መረጃዎችን ከሥራ አመራር ኮሚቴና ከቁጥጥር ኮሚቴ ርክክብ ይደረጋል፡፡ ዝርዝር መረጃዎችም የሚከተሉትን ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረት በዝርዝር የሚገልፅ ሆኖ ጥሬ ገንዘብ በእጅ እና በባንክ እንዲሁም ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች እና መዛግብቶች ካሉ ዋጋቸውንና ዝርዝር ሁኔታቸውን የሚገልፅ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣፣

ለ) የሚሰበሰብ እና ተከፋይ ዕዳዎችን የሚያስረዱ ሰነዶች መኖራቸውን፣

ሐ) የባለ ዕዳዎችን ስም፣ አድራሻና ሥራ በዝርዝር የሚገልጽ እና ለዕዳዎቹ የተያዘ መያዣ ካለ ዝርዝሩን የሚገልጽ ሰነዶች ያዘጋጃል፤

መ) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ላይ ዕዳ የሚፈልጉ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ስም አድራሻና ሥራቸው እንዲሁም ከኅብት ሥራ ማህበሩ ላይ የሚጠይቁትን ገንዘብ መጠን የሚገልጹ ሰነዶች፣

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የኦዲት ሪፖርትና ሌሎች መረጃዎችን አግባብ ካለው ባለስልጣን በሚያዘጋጀው ዝርዝር መሰረት የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረት እና ዕዳ በዝርዝር በመለየት ይሰበሰባል፣

## 118. የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ የማጣራት ስራ አካሄድ

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/09 አንቀጽ 56-57 ስለሂሳብ ማጣራት የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሂሳብ ማጣራት ሥራ የሚካሄደው:-

ሀ) ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነው የውህደት ወይም የመከፈል ልዩ ውሳኔ ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ሲረጋገጥ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ሂሳብ አጣሪ ይመደባል፡፡

ለ) የሚመደቡት የሂሳብ አጣሪ አባላት ቁጥር ሦስት ሲሆኑ አመራረጣቸውም ከኦዲት፣ ከህግ እና ከአደራጅ ባለሙያ ይሆናሉ፣

ሐ) የሂሳብ አጣሪዎቸ ሂሳቡን በማጣራት ዝርዝር ሪፖርት አግባብ ላለው ባለስልጣን ማቅረብ አለባቸው፤

መ) አግባብ ያለው ባለስልጣን የቀረበለትን የሂሳብ አጣሪዎች ሪፖርት እና በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ቃለ ጉባኤ መሰረት በማድረግ ውህደቱ ወይም መከፈሉ እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡

2) የሂሳብ ማጣራት ሥራው ሲከናወን ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሚኖረው ሕጋዊ ሰውነትና የሥራ እንቅስቃሴ፤

ሀ) የአንድ የኅብረት ሥራ ማህበር ሂሳብ የሚጣራው በዚህ አንቀጽአንቀጽ 4 በተጠቀሱት ምክንያቶች ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ለዚህ የሂሳብ ማጣራት አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች ሁሉ እስከ መጨረሻው የሕጋዊ ሰውነት ሙብት እንዳለው ይቆጠራል፤

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የገባውን ግዴታ ለመወጣት እና የተጀመሩትን ሥራዎች እስከ ሚፈርስ ድረስ ማካሄድ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን አዲስ ሥራ ለመጀመር አይችልም፡፡

ሐ) በአዲስ መልክ እንደገና ለመደራጀት ፍላጎት ያላቸውን ነባር አባላት ስብሰባ ይጠራል፣

መ) የሂሳብ ማጣራቱ ሂደት እንደተጠናቀቀ ህልውናውን ያጣው ኅብረት ሥራ ማህበር ህልውናውን ያጣ መሆኑን አግባብ ያለው ባለስልጣን በጋዜጣና አግባብ ባላቸው የመገኛኛ ዘዴዎች በኩል ያሳውቃል፡፡

## 119. ስለማይከፋፋል የኅብረት ሥራ ማህበራት ንብረት፤

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ዕደዎች ከመከፈላቸው በፊት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ንብረት አይከፋፈልም፣

2) ለዕዳ ጠያቂዎች ተከፍሎ ካላለቀ እና በጊዜው ተገኝተው የሚገባቸውን ከፍያ ላልወሰዱት በሚወሰነው ቦታ ካልተቀመጠ በስተቀር የኅብረት ሥራ ማህበሩ ገንዘብ ወይም ንብረት ለአባላት አይከፋፈልም፡፡

3) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በውህደት ወቅት የነበረው የማይከፋፈል የጋራ ንብረት በውህደት ለተቋቋሙት አዲስ ኅብረት ሥራ ማህበራት በማይከፋፈል የጋራ ንብረትነት ተመዝግቦ ይተላለፋል፡፡

4) የማይከፋፈል የኅብረት ስራ ማህበራት ንብረት እና ገንዘብ በማንኛውም መንገድ ለአባላትም ሆነ ለሌላው ወገን ለብድር ወይም ለዕዳ ከፍያ ወይም ዕዳን ለማቻቻል ወይም ለስጦታ ወይም ለሽልማት ወይም ለዕርዳታ እና ለመሳሰሉት ማዋል አይቻልም፡፡

5) የማይከፋፈለውን የኅብረት ሥራ ማህበሩን ካፒታል ወደ ወል ንብረትነት ይመድባል፡፡

6) አንድ የኅብረት ሥራ ማህበር በህጉ መሰረት እንዲፈርስ ሲወሰንና ንብረቱ ተጣርቶ ለክፍፍል በሚዘጋጅበት ጊዜ የሚከተሉት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ንብረቶች አይከፋፈሉም፡

ሀ) በየአመቱ ከሚገኘው ትርፍ እየተቀነሰ በመጠባበቂ ሂሳብ ውስጥ የተመዘገበ ከሆነ፣

ለ) በስጦታ ወይም በውርስ ወይም በሽልማት የተገኘ ንብረት ከሆነ፣

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማጠነከርና ለማበረታታት ሲባል ከመንግስት በነፃ የተገኘ መሬት ወይም ህንፃ ወይም ማንኛውም ቀሚ ንብረት ከሆነ፣

መ) የኅብረት ሥራ ማህበራት ለረዥም ወይም ለአጭር ጊዜ በአደራ እንዲያስተዳድረው የተሰጠ ንብረት ከሆነ፣

ሠ) እንዳይከፋፈል በህግ ክልከላ ተደረገበት ንብረት ከሆነ፣

## 120. <u>የዕዳ ወይም ገንዘብ ጠያቂዎችን ስለመጥራት እና ክፍያ ስለመፈፀም፣</u>

1) አባላት ኅብረት ሥራ ማህበራቸውን በማንኛውም ሁኔታ የማፍረስ መብት ቢኖራቸውም የሦስተኛ ወገኖች ወይም አበዳሪዎች እና ተበዳሪዎች ተቃውሞ ከተነሳ አግባብ ያለው ባለስልጣን የመፍርስ ጥያቄውን ከጠቅላላ ጉባዔ ጋር በመሆን መርምሮ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡

2) የንብረት ክፍፍል ለማድረግ የሂሳብ ማጣራት ሥራው ሲጀምር የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሕልውናውን የሚያጣ መሆኑን በመግለፅ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ለሁለት ተከታታይ ወራት በጋዜጣና አመች በሆነ መንገድ ማስታወቂያ ይወጣል፡፡

3) ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ወር ድረስ ዕዳ ጠያቂ አካላትና ህልውናውን በማጣቱ ያልተስማሙ አባላት ካልቀረቡ ወይም በወቅቱ ካልወሰዱ አዲስ በተቋቋመው የኅብረት ሥራ ማህበር በዕዳ ዋስትናነት ይቀመጣል፡፡

4) በሚወጣው ማስታወቂያ ውስጥ የመጀመሪያው የጥሪ ማስታወቂያ ካወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ወር ድረስ ተቃዋሚ ካልቀረበ የንብረት ክፍፍሉን የመጠየቅ መብት እንደሌለው መግለጽ አለበት፡፡

5) በኅብረት ሥራ ማህበሩ መዛግብት ውስጥ ለተጻፉ ዕዳ ጠያቂዎች ወይም በሌላ መልኩ ለሚታወቁ ገንዘብ ጠያቂዎች በሪኮማንዴ ደብዳቤዎች የጥሪ ማስታወቂያቸው በቀጥታ መላክ አለበት ለሌሎች ግን ግልጽ በሆነ በማስታወቂያዎች ያሳውቃል፡፡

6) በሂሳብ አጣሪዎች የተለየውን የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዕዳ ለባለዕዳዎች እንዲካፈል ይደረጋል፡፡ ሆኖም ዕዳው እንደገና ወደ ሚደራጀው የኅብረት ሥራ ማህበር እንዲተላለፍ ዕዳ ጠያቂዎችን ፍላጎት በመጠየቅ ሲስማሙ በጠቅላላ ጉባኤ ያስወስናል፡፡

7) የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ህልውናውን እንዲያጣ እና ሂሳቡ እንዲጣራ ውሳኔ የተሰጠበት የኅብረት ሥራ ማህበር ንብረት ክፍፍሉ ከመፈፀሙ በፊት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከአባላትና ከሌሎች ዕዳ ጠያቂዎች ጋር በነበረው ግንኙነት ያለበትን ዕዳና የሚሰበሰብ ሂሳቡን የማጣራት ሥራ የሂሳብ አጣሪዎች ኃላፊነትና ግዴታ ነው፡፡ በዚህም መሰረት፡-

ሀ) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ካልተከፈላቸው ወይም የእነርሱን ገንዘብ ለመክፈል አስፈላጊ የሆነው የገንዘብ መጠን ካልተቀመጠ በስተቀር አጣሪዎች የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገንዘብ ለማከፋፈል አይችሉም፡፡

ለ) ለገንዘብ ጠያቂዎች በወቅቱ ያልተከፈለ የገንዘብ መጠን ለፍርድ ቤት አቅርቦ በማስወሰን በሚሰጠው ውሣኔ መሠረት መቀመጥ አለበት፡፡

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ላልፈፀማቸው ግዴታዎች ወይም በክርክር ላይ ላሉት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ግዴታዎች ክፍያ የሚውል ተማጣጣኝ የሆነ ዋስትና ወይም ገንዘብ ተይዞ መቀመጥ አለበት፡፡

## 121. የመጨረሻ ሂሳብ ሚዛን ውጤት ለጠቅላላ ጉባኤ ስለማቅረብ

1) የሂሳብ አጣሪዎች ማንኛውንም የማጣራት ሥራ ከፈጸሙ በኋላ የመጨረሻ ሂሣብ ሚዛን ውጤት ለጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ ስለ ክፍፍሉ ውሣኔ ያሰጣሉ፤ በተሰጠው ልዩ ውሣኔም መሠረት ያከፋፍላሉ፣

2) በአዲስ መልክ እንደገና ለመደራጀት ፍላጎት ያላቸውን ነባር አባላት ስብሰባ ይጠራል፣

3) ኅብረት ሥራ ማህበር ሆነው መቀጠል ለማይፈልጉ ወይም ለማይችሉ አባላት በተደለደለው መሠረት ድርሻቸውን የሚገኙበትን የጊዜ ገደብና ሁኔታ ለጠቅላላ ጉባኤው ያስወስናል፣ ሆኖም የጊዜ ገደቡ ከአንድ አመት አይበልጥም፡፡

4) አግባብ ያለው ባለስልጣን እንደገና ለመመዝገብ የማይችሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከመዝገብ በመሠረዝ በጋዜጣ ያሳውጃል፡፡

5) በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና ለመመዝገብ ያልፈለጉና ዕዳ ያለባቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ዕዳቸውን ሳይከፍል በሌላ ኅብረት ሥራ ማህበር ስም ሊመዘገቡ አይችሉም፡፡

6) የሂሳብ አጣሪዎች ማንኛውንም የማጣራት ሥራ ከፈጸሙ በኋላ ለማከፋፈል የመጨረሻ ሂሳብ ሚዛን ውጤት ለጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ ስለ ክፍፍሉ ውሳኔ እንዲሰጠው በማድረግ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት የማከፋፈሉን ሥራ ከዚህ በታች ባለው ቅደም ተከተል መፈጸም አለበት፡፡

   ሀ) ማንኛውም ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚፈለግ የመንግስት ዕዳ በመጀመሪያ ደረጃ ይከፈላል፣

   ለ) ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ቅጥር ሠራተኞች ደሞዝ ይከፍላል፡፡ የተረፈው ገንዘብ ለሁሉም ሰራተኞች የማይበቃ ከሆነ እንደ ደሞዛቸው መጠን እየታሰበ ቀሪው ገንዘብ መከፋፈል አለበት፡፡

   ሐ) ለውጭ ገንዘብ ጠያቂዎች በቅደም ተከተላቸው እና የክፍያ ጊዜያቸው ለደረሰው ቅድሚያ በመስጠት ይከፍላል፡፡

   መ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ ከአባላት ለተበደረው ዕዳ ይከፍላል፡፡

   ሠ) ለዕጣ ግዢ ለተከፈለው ገንዘብ ይከፍላል፤ ሙሉ ለሙሉ መክፈል ካልተቻለ ያለውን ገንዘብ ባለው እጣ መጠን እየተሰላ መከፋፈል አለበት፡፡

   ረ) ለዲቪደንድ ክፍያ በዕጣ መጠን ላይ በመመሰረት ይከፋፈላል፡፡

## 122. የተጠራው ሂሳብ አከፋፈል ቅደም ተከተል

ሂሳቡ የተጣራለት የኅብረት ሥራ ማህበር ገንዘብ በሚከተለው መሠረት ይከፋፈላል፡፡

1) ማንኛውም ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚፈለግ የማንግስት ዕዳ በመጀመሪያ ደረጃ ይከፈላል፤

2) ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ቅጥር ሠራተኞች ደሞዝ ይከፈላል፡፡ የተረፈው ገንዘብ ለሁሉም ሠራተኛ ደሞዝ የማይበቃ ከሆነ እንደ ደሞዙ መጠን ያለው ገንዘብ በሬሾ መከፋፈል አለበት፡፡

3) ለውጪ ገንዘብ ጠያቂዎች በቅደም ተከተላቸው እና የክፍያ ጊዜያቸው ለደረሰው ቅዲሚያ በመስጠት ይከፋፈላል፡፡

4) ከአባላት ለተበደረው ዕዳ ይከፈላል፡፡

5) ለዕጣ ግዥ ለተከፈለው ገንዘብ ይከፋፈላል፡፡ ሙሉ ለሙሉ መክፈል ካልተቻለ ያለውን ገንዘብ ባለው ዕጣ መጠን መከፋፈል አለበት፡፡

6) ለዲቪደንድ ወይም ለትርፍ ክፍፍል ክፍያ በዕጣ መጠን ላይ በመመስረት ይከፋፈላል፡፡

## 123. <u>የኅብረት ሥራ ማህበርን ከመዝገብ ስለመሰረዝ፤</u>

1) የሂሳብ አጣሪዎች የሂሳብ ማጣራቱን ሥራ እንዲፈጽሙ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የምዝገባ የምስክር ወረቀትና ሂሳብ የተጣራበትን ሪፖርት አዘጋጅተው ለመደባቸው አካል ያቀርባሉ፤

2) የሂሳብ ማጣራት ሥራውን ያዘዘው አግባብ ያለው አካል የሚከተከሉትን ያከናውናል፣

ሀ) በማናቸውም የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሰነዶች የመጨረሻ ገጽ ላይ “ሕልውናውን ያጣ ኅብረት ሥራ ማህበር” በማለት ምልክት አድርጎ ይፈረምበታል፡፡

ለ) ሥራ ላይ ላልዋሉ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የገንዘብ ነክ ሰነዶች ላይ በእያንዳንዱ ገጽ “ታሽጓል፤ አይሠራም” የሚል ምልክት ያደርግበታል፡፡

ሐ) የሂሳብ አጣሪዎች ሂሳብ ያጣሩበትን ሪፖርት እና የኅብረት ሥራ ማህበራቱን የምዝገባ ምስክር ወረቀት፣ የተለያዩ ማህተሞችና ቃለ ጉባኤ በመያዝ ለመደባቸው ባለስልጣን መስሪያ ቤት ማስረከብ አለባቸው፤

መ) ሕልውናውን ስለአጣው የኅብረት ሥራ ማህበር ሰነዶችና መዛግብት አቀመጣጥ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

ሠ) የፈረሰውን የኅብረት ሥራ ማህበር የማይከፋፈል ገንዘብ ከኅብረት ሥራ ፈንድ ጋር እንዲገባ ያደርጋል፡፡

ረ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ከመዝገብ ይሰርዛል፤

ሰ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከመዝገብ ከተመሠረተበት ቀን አንስቶ ህልውናውን ያጣ መሆኑን በመግለጽ በጋዜጣና አመቺ መንገዶችን በመጠቀም ለህዝብ ማስታወቅ አለበት፡፡

3) የሂሳብ ማጣራት ሥራው ተጠናቆ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከመዝገብ መሠረዙ ከተረጋገጠ በኋላ በሂሳብ አጣሪዎች እጅ በሥራ ምክንያት የገቡት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሰነዶችና መዛግብት እንዲሁም ሌሎች መረጃዎች አግባብ ያለው አካል በሚወስነው ቦታ ለ10 ዓመታት ይቀመጣሉ፡፡

4) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሲታገድ ወይም እንዲፈርስ ሲወሰን በኅብረት ሥራ ማህበር አዋጅ 985/2009 መሠረት ቅሬታውን አግባብ ያለው ባለስልጣን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

5) አግባብ ያለው ባለስልጣን በቀረበው ምክንያት ካልተስማማ እና ዕግዱ እንዲነሳ ወይም የማፍረስ ሥራው እንዲቀጥል ሲወሰን የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የዳኝነት ሥልጣን ላለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰላሳ ቀን ውስጥ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 124. <u>የማይከፋፈል የኅብረት ሥራ ማህበራት ንብረት አቀማመጥና አስተዳደር</u>

1) አንድ የኅብረት ሥራ ማህበር በሕጉ መሰረት እንዲፈርስ ሲወሰንና ንብረቱ ተጣርቶ ለክፍፍል በሚዘጋጅበት ጊዜ የሚከተሉት የማህበሩ ንብረቶች አይከፋፈሉም፡፡

ሀ) ማህበሩ ሥራውን ሲያንቀሳቅስ በአዋጅ መሠረት በየአመቱ ከሚገኘው ትርፍ የተቀነሰ በመጠባበቂያ ሂሳብ ውስጥ የተመዘገበ ከሆነ፤

ለ) በስጦታ ወይም በውርስ የተገኘ ንብረት ከሆነ፣

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማበርከት ከመንግስት በነጻ የተገኘ መሬት ወይም ቤት ከሆነ አይከፋፈልም፡፡

2) የኅብረት ሥራ ማህበራት በእንቅስቃሴ በነበሩበት ወቅት በስማቸው በመጠባበቂያ ሂሳብ፣ በስጦታ፣ በውርስና ከመንግስት የተገኘ ድጋፍ ማህበሩ ሲፈርስ የማከፋፈል ንብረት ስለሆነ ለወደፊቱ ለሚቋቋሙት የኅብረት ሥራ ማህበራትና በሥራ ላይ ለሚገኙት የኅብረት ሥራ ማህበራትን የማስፋፋት ሥራ ይውላል፡፡

3) የማይከፋፈል ንበረትን ለማስተዳደርና በሥራ ላይ ለማዋል የኅብረት ሥራ ማህበራት ልዩ ፈንድ አግባብ ያለው ባለስልጣን ስም ይቋቋማል፡፡

4) የማይከፋፈሉ የማህበሩ ንብረቶች ወደ ጥሬ ገንዘብ ተቀይረው በሚቋቋመው ልዩ ኅብረት ሥራ ፈንድ ሂሳብ ገቢ ይሆናል፡፡

5) አግባብ ያለው ባለስልጣን ሂሳቡን ያንቀሳቅሳል፤ ይቆጣጠራል፤ በተገቢው ምነገድ በሥራ ላይ ያውላል፡፡

6) ኅብረት ሥራ ማህበራት ከመንግስት እና ከአቅም ገንቢዎች የሚያገኙትን ድጋፍ አዲስ የተቋቋመውም የኅብረት ሥራ ማህበር ያገኛል፡፡

7) የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማስፋፋትና ለማህበራት ከመንግስት በነጻ የተሰጠ መሬት ወይም ንብረት ለሚመለከተው የመንግስት አካል ይመለሳል፡፡ ሆኖም በመሬቱ ላይ ወይም በንብረቱ ላይ ለተካሄደው ግንባታ ወይም ማስፋፊያ የዋለው ገንዘብ ለፈረሰው ማህበር ተመላሽ ሆኖ በንብረት ክፍፍሉ ሂሳብ ውስጥ ይገባል፡፡

8) የሂሳብ ማጣራት ስራው ተጠናቆ እና ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ኅብረት ሥራ ማህበራቱ እንደገና ከተመዘገቡ በኋላ የህልውናውን ያጣው ኅብረት ሥራ ማህበር ማህተም ሥራ ላይ እንዳይውል ይወገዳል፤ መዛግብትና ሰነዶች እንዲሁም ሌሎች መረጃዎች አዲስ በተቋቋመው የኅብረት ሥራ ማህበር ጽህፈት ቤት በጥንቃቄ ይቀመጣል፡፡

## <u>ክፍል አሥራ ሰባት</u>

## <u>ስለክርክር አወሳሰን</u>

### 125. <u>ጉዳዮችን በዕርቅ ስለመጨረስ</u>

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ 1-3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ የሚፈጠሩ ማናቸውም አለመግባባቶች በእርቅ እንዲፈቱ አደራጁ ባለሙያ አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2) ዕርቅ በተከራካሪ ወገኖች መካከል ይግባኝ ሳይኖረው የመጨረሻ ሆኖ እንደ ተፈረደ ፍርድ የሚቆጠር ነው፡፡

3) ዕርቁ ለሕግ ወይም ለመልካም ተግባር ተቃራኒ ከሆነ እንዲሁም ከሌላ ውል ጋር ግኑኝነት ያለው ከሆነ ፈራሽ ነው፡፡

4) ተመሳሳይ ጉዳይ ባላቸው ባለጉዳዮች በአንዱ የተደረገ ግልግል ሌሎቹን ባለጉዳዮች አያስገድድም፡፡ እነርሱም መቃወሚያ ሊያደርጉት አይችሉም፡፡

## 126. በዕርቅ ስምምነት አስታራቂ ለመሆን ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች

1) ለአስታራቂነት የሚመረጡ ግለሰቦች በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው በመልካም ሥነ--ምግባራቸው የሚታወቁ መሆን አለባቸው፡፡
2) በአካባቢዉ ህብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያለዉ እና መልካም ሥነ-ምግባር ያለዉ
3) ለአስታራቂነት የሚመረጡት በኅብረት ሥራ ማህበሩ አከባቢ የሚኖር መሆን አለባቸው፡፡

## 127. በዕርቅ ስምምነት በተገላጋዮች መሟላት ስለሚገባቸው ጉዳዮች

በኅብረት ሥራ ማህበራት ለዕርቅ በሚቀርቡ ባለጉዳዮች የሚከተሉትን መሟላት አለባቸው፡፡

1) ለዕርቁ ሲቀርቡ የሁለቱ ስምምነት በጽሁፍ መቅረብ አለበት፡፡
2) የክርክር አቀራረቡ የፍትሐ ብሔር ሕጉ በሚያዝዘው ፎርም መሠረት መሆን አለበት፡፡
3) ለግልግል ሥራው የሚውል በጀት ተተምኖ ከሁለቱም ወገኖች ከተዋጣ በኋላ የአደራጅ መስሪያ ቤቱ በሚወክለው ሰው እጅ መያዝ አለበት፡፡

## 128. የዕርቅ ስምምነት ስለሚይዛቸው ጉዳዮች

1) ተከራካሪ ወገኖች ስም፣ አድራሻ፣ የመኖሪያ እና የሥራ አድራሻ (መጥሪያ ለመላክ አመቺነት ያለው)፣
2) የዕርቁን ስምምነት የሚያመለክት የፍሬ ነገር መግለጫ፣( ነገሩ በፍርድ ቤት ተይዞ ከሆነ)

ሀ) የቀረበበት ፍርድ ቤት ስም እና አድራሻ፣

ለ) የክሱን አርዕስትና የመዝገቡን ቁጥር፣

ሐ) ተዋዋይ ወገኖች ለውሳኔው የሚገዙ መሆናቸውን ቃል በመግባት ይህንኑ በፊርማ ማረጋገጥ አለባቸው፣

## 129. በዕርቅ ስምምነት ስለ ገላጋዮች አበል አወሳሰን፤

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 61 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚደረገው የእርቅ ስምምነት ሂደት ለገላጋዮች የሚከፈል አበል አይኖርም፡፡

2) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 129 ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሁለቱ ተዋዋዮች ስምምነት መሠረት በገላጋዮች ለወጣው ወጪ መሸፈኛ ሊከፈል ይችላል፡፡

## 130. በዕርቅ ግልግል አካሄድ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ተግባር እና ኃላፊነት

በሚደረገው በዕርቅ የግልግል አካሄድ አግባብ ያለው ባለስልጣን የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖረዋል፤

1) በተገላጋዮች መካከል ያለን ጉዳይ በዕርቅ ለመጨረስ በዕርቅ ውሳኔው ጣልቃ ሳይገባ ለሥራው ምቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
2) ተገላጋዮች ጉዳያቸውን በዕርቅ እንዲጨርሱ ሙያዊ የምክር አገልግሎት መስጠት፣
3) ከተገላጋዮች የቀረበው የዕርቅ ስምምነት በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ በተደነገገው መሠረት በተከራካሪዎች ፍልጎት እና ሙሉ እምነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥ፣
4) ለዕርቅ የቀረበው ጉዳይ ከሕግ ጋር የማይጋጭ እና ሞራልን የማይነካ መሆኑን ማረጋገጥ፣
5) የገላጋዮች አመራረጥ የኅብረት ስራ ማህበራት አዋጅ በሚፈቅደው መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

6) ተገላጋዮች ሰብሳቢ ለመምረጥ ስምምነት ላይ ካልደረሱ ሰብሳቢውን በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ መሠረት በመምረጥ ለሁለቱም ወገኖች ማሳወቅ፤

7) ተከራካሪ ወገኖች ገላጋዮችን ለመምረጥ የዕኩልነት መብት ማግኘታቸውን እና ያለምንም ተፅዕኖ መሆኑን ማረጋገጥ፣

8) የተሰጠውን ብይን ወይም ውሳኔ ተከራካሪ ወገኖች ባቀረቡት የዕርቅ ስምምነት እና በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ መሠረት መሆኑን ማረጋገጥ፣

9) ተገላጋይ ወገኖች ጉዳያቸውን ለማስረዳት እና ክርክራቸውንም ቀርበው ለማሰማት የዕኩልነት መብት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣

10) ገላጋዮች ያቀረቡት የዕርቅ ሃሳብ በተከራካሪዎች ተቀባይነት ካላገኘ የተከራካሪ ወገኖችን የክርክር ጉዳይ እና በገላጋዮች የተደረጉ የማጣራት ሂደቶች እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች በማያያዝ በ15 ቀናት ውስጥ በሽምግልና ዳኝነት እንዲታዩ ማድረግ፣

11) ለዕርቅ ሥራው የሚውል በጀት በተተመነው መሠረት ከሁለቱም ወገኖች በሚወከለው ሰው እጅ እንዲቀመጥ ማሠባሰብ፣ክፍያውንም ቀደም ሲል በተወሰነው መሠረት መፈጸሙን መከታተል፣

12) ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ በዕርቅ ጉዳዩን ለመጨረስ ፍቃደኛ ካልሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ይህንኑ በመግለጽ ፍቃደኛ ለሆነው ወገን ማስረጃ ይሰጣል፡፡

## 131. ስለሽምግልና ዳኝነት

1) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በዕርቅ ያልተፈቱ ክርክሮችን በሽምግልና ዳኝነት እንዲታዩ ማድረግ አለበት፡፡

2) ሽምግልና ዳኝነት የሚፈጸመው ተከራካሪ ወገኖች ያልተግባቡበትን ክርክሮች ለሽምግልና ዳኞች በማቅረብ በሚሰጠው ውሳኔ ለመግዛት ስምምነት ላይ ደርሰው ሲቀርቡ ነው፡፡

3) የሽምግልና ዳኝነት እንደ አንድ አስገዳጅ ያለመግባባት መፍቻ መፍትሔ መጠቀም የሚቻለው በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 በአንቀጽ 64 እና 65 ላይ የተዘረዘሩትን ክርክሮች ለመፍታት እና ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የግብይት እንቅስቃሴ ካላቸው ግለሰቦች እና ድርጅቶች ጋር የሚነሱ የፍትሐብሔር ክርክሮችን ለመፍታት ይሆናል፡፡

## 132. የሽምግልና ዳኝነት አፈጻጸም፣

1) የሽምግልና ዳኞች ክርክሮችን የሚሰሙት እና የዳኝነት ተግባሩን የሚፈጽሙት በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡

2) በሽምግልና ዳኝነት የሚሰጥ ማንኛውም ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ በፍትሐ ብሔር ችሎት እንደተሰጠ ተቆጥሮ አስፈላጊ ሲሆን ፍርድ ቤቶች ውሳኔው፣ ትዕዛዙ ወይም ብይኑ እንዲፈጸም የማስገደድ ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

## 133. በሽምግልና ዳኝነት ስለይግባኝ አጠያየቅ፤

1) በሽምግልና ዳኝነት በተሰጡ ውሳኔዎች፣ ትዕዛዝ ወይም ብይን ላይ ሁለቱ ወይም ከሁለቱ አንዱ በህግ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

2) ተከራካሪው ኅብረት ሥራ ማህበር ተጠሪነቱ ለፌዴራል መንግሥት በሆነ ከተማ የሚገኝ ከሆነ ተጎድቻለሁ የሚለው ወገን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

3) ተከራካሪው ኅብረት ሥራ ማህበር በክልል የሚገኝ ከሆነ ተጎድቻለሁ የሚለው አካል ይግባኙን ለክልል ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

4) በሁለት ክልሎች ውስጥ በተደራጁት የኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚፈጠር ክርክር ከሆነ ከመጀመሪያው የሽምግልናው ዳኝነት የሚታየው በፌዴራል ደረጃ በመሆኑ ይግባኙ የሚቀርበው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡

## 134. በሽምግልና ዳኝነት የተከራካሪ ወገኖች ግዴታዎች፣

1) ተከራካሪ ወገኖች ለሽምግልና ዳኝነቱ ሥራ የሚሆኑትን መረጃዎች እና ማስረጃዎች ለሽምግልና ዳኞቹ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

2) የሽምግልና ዳኝነቱን ሥራ ከሚያደናቅፍ ወይም በጣም አስቸጋሪ ከሚያደርጉ ተግባራት መራቅ አለባቸው፡፡

3) ተከራካሪ ወገኖች የሽምግልና ዳኞች ውሳኔ ስላለመደረጉ መግለጫ ካላቀረቡ በስተቀር የክርክሩ ጊዜ ከማለቁ በፊት ክርክራቸውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ አይችሉም፡፡

## 135. ለሽምግልና ዳኝነቱ ስለሚቀርቡ ባለጉዳዮች፤

1) ባለጉዳዮች ህጋዊ ችሎታ ያላቸው መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ክርክሩን በሽምግልና ዳኝነት ለማየት አይቻልም፡፡

2) በሽምግልና ዳኝነት ጉዳዩ እንዲታይለት የሚቀርበው ባለጉዳይ በቀጥታ ጉዳዩ የሚመለከተው ወይም ህጋዊ ወኪል መሆን አለበት፡፡

## 136. በተከራካሪዎች መሟላት ስለሚገባቸው ጉዳዮች፤

ለሽምግልና ዳኝነት የሚቀርቡ ባለጉዳዮች የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፡፡

1) በሽምግልና ዳኝነቱ ጉዳያቸውን ለመጨረስ ሲቀርቡ የተከራካሪ ወገኖች ስምምነት መኖር አለበት፡፡

2) ክርክሩ የፍትሐ ብሔር ህጉ በሚያዘው የክርክር ማቅረቢያ ፎርም መሠረት ተሟልቶ መቅረብ አለበት፡፡

## 137. የሽምግልና ዳኞች ወጪዎች እና የድካም ዋጋ፤

1) የሽምግልና ዳኞች ለሥራው አፈጻጸም ሲባል በተገቢው መንገድ የተፈጸሙ ወጪዎች ተመላሽ እንዲደረጉላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

2) ሌላ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የሥራቸውን ዋጋ ለማግኘት መብት የላቸውም፡፡

## 138. ስለሽምግልና ዳኝነት አግባብ ያለው ባለስልጣን ተግባር እና ኃላፊነት፤

1) በተከራካሪዎች መካከል ያለውን ጉዳይ በሽምግልና ዳኝነት እንዲያልቅ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

2) ተከራካሪዎች ጉዳያቸውን በሽምግልና ዳኝነት እንዲጨርሱ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡

3) ለሽምግልና ዳኝነቱ የቀረበውን ጉዳይ ከሕግ ጋር የማይጋጭ እና ሞራልን የማይነካ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

4) የሽምግልና ዳኞች አመራረጥ የኅብረት ሥራ አዋጅ በሚፈቅደው መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

5) ተከራካሪዎች የሽምግልና ዳኞችን ሰብሳቢ ለመምረጥ ስምምነት ላይ ካልደረሱ ሰብሳቢውን ይመርጣል፡፡

6) ተከራካሪዎች የሽምግልና ዳኞችን ለመምረጥ እኩል መብት ማግኘታቸውን እና ያለምንም ተጽዕኖ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

7) የተሰጠው ውሳኔ ወይም ብይን ተከራካሪ ወገኖች ባቀረቡት ፍሬ ነገር መሠረት እና በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ብቻ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

8) ተከራካሪ ወገኖች በክርክር ላይ ጉዳያቸውን ለማስረዳት እና ክርክራቸውንም ቀርበው ለማሰማት በእኩልነት መብት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፡፡

# ክፍል አሥራ ስምንት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 139. የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከርና ማዘመን

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት የተቋቋሙለትን ዓላማ ለማሳካት እንዲችሉ በተለዩ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የማጠናከር ስራ መስራት ይኖርበታል፣

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማጠናከር ቢያንስ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ በትኩረት መስራት ይኖርበታል፡-

ሀ) የአደረጃጀት፣ አመራር እና አሰራር ስርዓት ማጠናከር፣

ለ) የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን ስርጸት አገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነት ማሳደግ፣

ሐ) የመልካም አስተዳደር ስርዓት ማስፈን፣

መ) አባላት ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣

ሠ) የፋይናንስ አቅም መገንባት እና

ረ) ንብረት አስተዳደር ማጠናከር፣

ሰ) የቁጠባ ባህልና መጠን በማስፋፋት የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር፣

ሸ) የኅብረት ሥራ ማህበራትን የገበያ ድርሻ ማሳደግ፣

ቀ) በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚኖረውን የእርስ በርስ ግንኙነት ማጠናከር፣

በ) የመሰረተ ልማት ግንባታ ግንባታና አስተዳደር ማጠናከር፣

ተ) የመረጃ ስርዓት ማጠናከር፣

3) የኅብረት ሥራ ማህበራት አሰራር አዋጭ እና ጊዜ ቆጣቢ በሆኑ ዘመናዊ በቴክኖሎጂ እንዲደገፉ በማድረግ ፍትሃዊና ቀልጠፋ የሆነ አገልግሎትን ለአባላት ተደራሽ እንዲያደርጉ መስራት አለበት፣

## 140. <u>የኅብረት ሥራ አደራጅ ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ የመተዳደሪያ ደንቦች፣ የውስጠ ደንቦች እና ማኑዋሎች ላይ ያሉ ክፍተቶች በጥናት በመለየት እንዲሻሻል ማድረግ፣ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማድረግ፣

2) ለኅብረት ሥራ ልማት አስፈላጊ የሆነ የኅብረት ሥራ ፈንድ፣ የአማካሪ ምክር ቤት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን እና የኅብረት ሥራ ሊግ የሚቋቋሙበትን አሰራር መዘርጋት፣

3) የኅብረት ሥራ ማህበራት ለማደራጀት ሶሺዮ ኢኮኖሚክ ጥናት እና የአዋጭነት ጥናት ማካሄድ፣

4) የኅብረት ሥራ ማህበራት ለማደራጀት የሚያግዙ ሞዴል የመተዳሪያ ደንብ፣ የውስጠ ደንብ እና የቢዝነስ ፕላን ማዘጋጀትና አሰራሩን መዘርጋትና ማደራጀት፣

5) ለኅብረት ሥራ ዘርፍ ልማት እድገት የሚያግዝ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ማዘጋጀትና ስራ ላይ ማዋል፣

6) የኅብረት ሥራ ትምህርትና ስልጠና የሚያስፈልግ ሥርዓተ ትምህርት መቅረፅና ማኑዋሎችን ማዘጋጀትና ስራ ላይ ማዋል፣ የስልጠና ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት እና የስልጠና ውጤታማነት ጥናት ማካሄድ

7) የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚያግዙ አለም አቀፍና የአገር ውስጥ ልመዶችንና ተሞክሮዎችን በመቀመር መስፋፋት፣

8) በኅብረት ሥራ ማህበራት ዙሪያ የጥናትን ምርምር ሥራዎችን ማድረግ

9) በኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት፣ ማጠናከር እና ማዘመን ላይ የተለያዩ አማራጭ ስትራቴጂያዊ አሰራሮች ማዘጋጀትና መዘርጋት፣፣

10) ለኅብረት ሥራ ማህበራት ልማትና እድገት የሚያግዙ ፕሮጅክቶችን በማዘጋጀት ሥራ ላይ ማዋል፣

11) አገራዊ የኅብረት ሥራ ምዝገባ አሰራር ላይ ጥናት በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራት የምዝገባ አሰራር ስርዓት እና የመረጃ መረብ መዘርጋት፣

12) የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚዋሃዱበትን፣ የሚከፈሉበትን እና የሚፈርሱበትን አሰራር መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ፣

## 141. <u>የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች አባላት መብት እና ግዴታ</u>

1) ስለ አባላት መብት በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 አንቀጽ 25 ን/አንቀጽ 1 (ሀ-ሠ) እና 2 (ሀ-ሠ) ከተደነገገው በተጨማሪ በማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት አስተዳደር እና አጠቃቀም በአዋጅ ቁጥር 1223/2012 አንቀጽ 14 መሠረት የሚከተሉትን መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማትን መሰረት አድረገው የተደራጁ አባላት በማህበረሰብ ተፋሰስ ውስጥ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች በጋራ ወይም በግል የመጠቀም፣

ለ) አባላት እንደሙያቸውም ሆነ እንደፍላጎታቸው የተጠቃሚዎች ቡድን በመፍጠር ተፋሰሱን በማይጎዳ ሁኔታ ገቢ በሚያስገኙ ስራዎች ላይ የመሰማራት፣

ሐ) የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ላይ የግንዛቤ እውቀት በሚያስጨብጡ መድረኮች ላይ የመሳተፍ፣

2) ስለ አባላት መብት በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 አንቀጽ 25 ን/አንቀጽ 1 (ሀ-ሠ) እና 2 (ሀ-ሠ) ከተደነገገው በተጨማሪ በማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት አስተዳደር እና አጠቃቀም በአዋጅ ቁጥር 1223/2012 አንቀጽ 16 መሠረት አባላት የሚከተሉትን ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚካሄድ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ላይ የመሳተፍ፣

ለ) በተፋሰሱ ክልል ያሉትን ተፈጥሯዊና በልማት የተገኙ ሀብቶች ከውድመት የመጠበቅና የመከላከል፣

ሐ) በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚወሰን የአባልነት ክፍያ የመክፈል፣

መ) በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በግል፣ በቡድንና በአጠቃላይ በሚከናወኑ የውይይት፣ የእቅድ ዝግጅት፣ የጥበቃና የልማት ተግባራት ላይ የኑሮ ሁኔታቸውን በማይጎዳ መልኩ የጉልበት አስታዋፅኦ ማድረግን ጨምሮ በንቃት የመሳተፍ፣

ሠ) ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ልዩ ልዩ የተፈጥሮ ሀብት ልማት መሰረተ ልማቶች ተጠግነው የዘወትር ጥቅም መስጠታቸውን እንዲቀጥሉ ማህበሩ በሚያወጣው ፕሮግራም መሰረት በትገና ስራ ላይ የመሰማራት፣

ረ) አባል ባልሆኑ የግል ባለይዞታዎች መሬት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ተግባራት አለማከናወን፣

3) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለአባላት የተሰጡ መብቶችና ግዴታዎች በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ ማካተት ይኖርበታል፡፡

4) በኅብረት ሥራ ማህበራት በአዋጅ 985/2009 አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 1-7 ከአባልነት ስለመሰናበት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 1223/2012 አንቀጽ11 ንኡስ አንቀጽ 1-5 እና በአንቀጽ 18 መሰረት ግዴታቸውን የማይወጡ

አባለት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ይሰናበታል፡፡ ይህንን አስመልክቶ እንዴት እንደሚሰናበቱ በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ ማካተት ይኖርበታል፡፡

5) በማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1223/2012 አንቀጽ 15 መሠረት የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ያልሆኑ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች የሚከተሉትን መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) በማህበረሰብ ተፋሰሱ ውስጥ በግል ወይም በማህበረሰቡ ወይም በህጋዊ አካል በተረጋገጠ የወል ይዞታ ላይ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች የመጠቀም፣

ለ) አባል ለመሆን የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ካሟሉ በማንኛውም ጊዜ የማህበረሰብ ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበር አባል የመሆን፣

ሐ) የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ጥበቃና አጠቃቀም በሚመለከት ግንዛቤና እውቀት በሚያስጨብጡ መድረኮች ላይ የመሳተፍ፣

መ) ማህበሩ ከተፋሰሱ ልማት ጋር በተያያዘ በሚያከናውናቸው ተግባራት ምክንያት፣ በግል ይዞታ ላይ ከሚከሰት ጉዳት የመጠበቅ፣

6) በማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1223/2012 አንቀጽ 17 መሠረት የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ያልሆኑ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች የሚከተሉትን ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) በወል ይዞታ ላይ ተጠቃሚ ለመሆን የልማትና የጥበቃ ተግባር ላይ ከማህበሩ አባላት እኩል ተሳትፎ የማድረግ፣

ለ) የማህበረሰብ ተፋሰስን ሊጎዱ የሚችሉ ተግባራትን ከመፈፀም መቆጠብ፣

ሐ) በግል ይዞታቸው ላይ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም የተፋሰሱን ደህንነት የሚጎዱና የተፈጥሮ ሀብት መራቆትን የሚያስከትሉ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ፣

መ) በተፋሰሱና በአከባባው በሚገኝ የደን ሀብት ላይ እሳትና መሰል አደጋ በሚከሰት ጊዜ ማህበሩ ለሚያደርገው የልማትና የጥበቃ እንቅስቃሴ የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

## 142. <u>የማህበረሰብ ተፋሰስ ኅብረት ሥራ ማህበራት አስተዳደር እና አጠቃቀም</u>

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 እና በማህበረሰብ ተፋሰሶች አዋጅ ቁጥር 1223/2012 መሰረት የሚደራጁ እና የሚመዘገቡ ማናቸውም ማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት እንደ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ማናቸውንም ጥቅማ ጥቅም፣ ድጋፍና ክትትል የሚደረግለት ይሆናል፡፡

2) የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማደራጀት፣ ለመመዝገብ፣ አቅም ለመገንባት፣ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለማጠናከር በየደረጃው የሚገኙ የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተውና ተባብረው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

3) ከሁለት የተፋሰስ ቦታ ላይ መሬት ያለው ማንኛውም ግለሰብ ጠንካራ ተሳትፎ ለማድረግና ውጤታማ ለመሆን ስለሚያስቸግር በሁለት ቦታ በተመሳሳይ ኅብረት ሥራ ማህበር አባል መሆን አይችልም፡፡

4) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 142 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሁለት የተፋሰስ ቦታ ላይ መሬት ያለው ማንኛውም ግለሰብ አንደኛውን የተፋሰስ መሬት ለሌላ የቤተሰብ አብል በማስተላለፍ የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

5) በአንድ የማህበረሰብ ተፋሰሶች ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበር ውስጥ ባልና ምስት አባል መሆን ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን የሚኖራቸው የተሳትፎ አሰራር ላይ ግልፅ የአፈፃፀም በውስጠ ደንባቸው ውስጥ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

6) ከዚህ ቀደም በተፋሰሶቹ ውስጥ አስቀድመው በደን ልማት ላይ የተደራጁ የደን ልማት ኅብረት ሥራ ማህበራት ቀድም ሲባል በወጣው የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 መሰረት የተደራጁ ቢሆንም ለኅብረት ሥራ ማህበራቱ ጥቅም ሲባል በማህበረሰብ ተፋሰሶች፣ ልማት፣ አስተዳደርና አጠቃቀም የወጣ አዋጅ ቁጥር 1223/2012 መሰረት እንዲጠቀሙ ሊደረግ ይችላል፡፡

7) በተፋሰስ ልማቱ ውስጥ መሬት ተከራይተውም ሆነ መሬት በሌላ ህጋዊ መንገድ ያገኙ ከተፋሰሱ ጋር ግንኙነት ያላቸው አባላት የኮንትራት ውላቸው ጊዜቸውን ከጨረሱ በኃላ ወይም የኮንትራት ሳይጠናቀቅ በአባልነት የማይቀጥሉ ከሆነ የሚገባቸውን አስፈላጊውን ጥቅም አግኝተው የሚሰናበቱ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የሚገባቸውን ጥቅም የሚያገኙት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ ኦዲት ከተደረገ በኋላይ ሆናል፡፡

8) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ በተለያየ ምክንያት ከአባልነት የሚሰናበት ማንኛውም አባል ቀደም ሲባል በእጁ ያለውን የኅብረት ሥራ ማህበሩን ብድር ወይም ሌላ እዳ መመለስ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም በቂ መረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

9) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 2 በአንድ የሥራ ክልል ተመሳሳይ የኅብረት ሥራ ማህበራት አይደራጁም የሚለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተፈሰስ መሰረት በማድረግ የሚደራጁ የማህበረሰብ ተጠቃሚዎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ከባህሪያቸው በመነሳት ተመሳሳይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊደራጁ ችላሉ፡፡ ሆኖም በዚህ ሁኔታ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተገቢውን አዋጭነት ጥናት መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

10) ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ተፋሰስን መሰረት ያደረገ በመሆኑ እና የማህበረሰብ ተፈሰስ መሰረት በማድረግ በአንድ ቀበሌ ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆነ ተመሳሳይ የማህበረሰብ ተፈሰስ ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበር ሊደራጅ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን አዋጭነቱ ሳይረጋገጥ የሚደራጅ ኅብረት ሥራ ማህበር አይኖርም፡፡

11) የማህበረሰብ ተፋሰሶች ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበር ያገኘውን ተዘዋዋር ፈንድ ለአባላት በሚያከፋፍልበት ወቅት ማሟላት ስለሚኖርበት መስፍርት እና የወለድ አሰራር በተመለከተ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

12) ከማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበር የተሰጡ የተዘዋዋሪ ፈንድ ገንዘብ ወይም ሌሎች ቋሚ ንብረቶች ለኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚቀሩ ይሆናል፡፡ ሆኖም የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሲፈርስ የማከፋፈሉ ንብረቶች በመሆናቸው በአዋጅ 985/2009 መሰረት ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል፡፡

13) የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበር የባለቤትነት ጉዳይ ለማረጋገጥ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይኖርበታል፤

ሀ) የሚደራጁበት መሬት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ለመሆኑ የባለቤትነት ማረጋገጫ የቦታ ካርታ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ለ) ከማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበር የተደራጁበት የምዝገባ የምስክር ወረቀት (ሠርተፊኬት)፣

ሐ) የሚኖራቸው የመናጅምንት እቅድ (ፕላን) በማቅረብ፣

14) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 142 ንዑስ አንቀጽ 13 መሰረት ስለ የማህበረሰብ ተፈሰስ ተጠቃሚዎች የኅብረት ሥራ ማህበር የባለቤትነታቸው ጉዳይን በተመለከተ በየደረጃው ያለው የመሬት አስተዳደር አካላት አማካኝነት የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡

15) ከዚህ ቀደም በማህበረሰብ ተፋሰሶችን መሰረት አድርገው የጋራ ወይም የወል መሬት ላይ ተደራጅተው ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሳይፈርሱ ሌሎች በአከባቢው ያሉትን በአባልነት እንዲቀበሉ በማድረግ ባሉበት እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡

16) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 142 ንዑስ አንቀጽ 15 መሰረት በነባሩ ውስጥ በአባልነት ለመታቀፍ ምቹ ሁኔታ አለመኖሩን ሲያረጋግጥ አግባብ ያለው ባለስልጣን በጥናት ላይ በመመስረት ሌላ አዲስ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበር ሊያደራጅ ይችላል፡፡

17) በነባሮቹን የደን ልማት እና በአዳዲስ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረገ እርስ በርስ ትስስር በማድረግ ማጠናከር ይኖርበታል፣

18) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 አንቀጽ 10 ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ምዝገባ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማህበረሰብ ተፋሰሶች ላይ ለሚደራጁት በተጨማሪ በማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1223/2012 አንቀጽ 10 መሰረት በማድረግ መዝገብ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

19) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 142 ንዑስ አንቀጽ 18 ላይ ስለ ማህበረሰብ ተፋሰሶች ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ምዝገባ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚጠበቅባቸውን ግዴታ አሟልተው ለምዝገባ የሚመጡ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች በኅብረት ሥራ ማህበራት፤

ሀ) በተለየ መዝገብ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

ለ) የተለየ የምዝገባ ምስክር ወረቀት (ሠርተፊኬት) መሰጠት ይኖርበታል፡፡

ሐ) ሁሉንም መስፈርት ያላሟሉ ሆነው ሲገኙ በአዋጅ 985/2009 መሠረት ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት (ሠርተፊኬት) የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

## 143. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት አደራጅ ባለሙያ ስነምግባር</u>

የኅብረት ሥራ ማህበራት አደራጅ ባለሙያዎች የሚከተሉት ባህሪያት ይኖራቸዋል፣

1) **ወጥና የሚናበብ አሠራር መከተል፡** ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ወጥነት ባለውና እርስ በርስ በሚናበብ መልኩ ይሆናል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደረጉት የማደራጀት፣ የማጠናከር፣ የማዘመን፣ አሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣ ጥናትና ምርምር እና የትምህርትና ስልጠና አሰራሮች ወጥነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

2) **ከተፅዕና ነፃ መሆን፡** በምንም ዓይነት ሁኔታ በማንም ተፅዕኖ ስር መሆን የለበትም፣ ሲያደራጅም ሆነ ሲያጠናክር የሙያውን ገለልተኛነት ተጠቅሞ ትክክለኛ አዋጅ፣ ደንብና የአደረጃጀት መመሪያ ተከትሎ ማከናወን አለበት፡፡ አደራጁ ከራሱ የውስጣዊ የአእምሮ ነፃነት በመላቀቅ በንፁህ ህሊና በመሆን ተግቢውን ሙያዊ ድጋፍና አስተያት በነፃነት መስጠት ይኖርበታል፡፡ አደራጁ ከሚደግፈው እና ከሚከታተለው የኅብረት ሥራ ማህበር ጋር የሚኖረው ግንኙነት አግባቢነት ያለው፣ ሕግን የተከተለ እና አደራጁን ከሌላ ውጫዊ ተፅዕኖ ነፃ እንዲሆን የሚደርግ መሆን አለበት፡፡ አደራጅ ባለሙያ የሙያ ስንምግባሩን አክብሮ በመስራት ከኢኮኖሚ እና የፋይናንስ ጥገኝነት ራሱን መጠበቅና ማራቅ ይኖርበታል፡፡

3) **እውቀትን መሰረት ያደረገ አሰራር፡** አደራጅ ባለሙያው ራሱን በእውቀት ያበቃ መሆን ይኖርበታል፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለማደራጀት፣ ለመጠናከርና ለማዘመን አስቀድሞ በቂ መረጃ ማሰባሰብ፣ ተገቢውን ጥናት ማድረግና ከቸኮላ እና ከግዴለሽነት ነፃ ሆኖ ማከናወን፣

4) **ጠንቃቃና አስታዋይ መሆን፡** አደራጅ ባለሙያው ለሚያከናውናቸው ተግባራት አስቀድሞ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ከግዴለሽነት አሰራር ነፃ መሆን ይኖርበታል፡፡ ለሚያከናውናቸው ተግባራት የተለየ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ተልዕኮ፣ ራዕይና የጉዞ አቅጣጫዎችን በትኩረት የሚያይ መሆን ይኖርበታል፡፡

5) **ታማኝ፣ ተግባቢ እና ገብረ-ገብ መሆን፡** የአደራጅ ባለሙያ በሥራው ቦታም ሆነ በኅብረት ሥራ ማህበራት ዘንድ የሚኖረው ታማኝነት ጥያቄ ውስጥ ሊገባ አይገባም፡፡ አደራጁ በኅብረተሰቡ መካከል የሚከበር ባለሙያ መሆን አለበት፡፡ ከኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራ አመራርና ከሠራተኞች ጋር በአግባቡ ተግባቢ መሆን አለበት፡፡ ከብልሹ አሰራር ገለልተኛ መሆን አለበት፡፡

6) **ሁለገብና ሁሉ አቀፍ ድጋፍ፡** አደራጅ ባለሙያው ሁለገብ ግንዛቤ ያለው፣ የገበያ ትስስር፣ መሰረተ ልማት እና አግሮፕሮሰሰንግ አሰራር ላይ ደግፎ በማብቃት ሁሉአቀፍ ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡ ስለ ሂሳብ ዝርጋታ፣ ምዘገባ፣ ሪፖርት፣ ትንተና እና ስለ ሂሳብ አያዝ ሥርዓት የሚያረጋግጥ በመሆኑ ጥልቀት ያለው የሂሳብ መላምቶች እና ጽንሰ-ሐሳቡን ማወቅ አለበት፡፡ የፋይናንስ ሪፖርት ዝግጅት እና ትንተና በቂ እውቀት ያለው መሆን አለበት፡፡

7) **ሕግን ማወቅ፣ ማክበር እና ማስከበር፡** የኅብረት ሥራ አደራጅ ባለሙያ በህግ እውቀቱ በጣም የላቀ መሆን ባይጠበቅበትም የኅብረት ሥራ ማበራት አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያዎችን ማወቅ፣ ማክበርና መስከበር ይኖርበታል፡፡ ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪዎችን ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡ የሚያጠናክረውን የኅብረት ሥራ ማህበራት መተዳደሪያ ደንብ እና የውስጠ ደንብ በሚገባ ማወቅና መደገፍ ይኖርበታል፡፡

8) **ተዓማኒነት የተላበሰ አግልግሎት፡** አደራጁ ስራውን የሚያከናውነው በታማኝነት፣ በጥንቃቄ እና በሃላፊነት በመቀበል፣ ህግን በመከተል፣ በህግና በሙያው የሚፈለጉ መግለጫዎችን ግልፅ በማድረግ፡፡ ህጋዊ ባልሆኑ ድረጊቶች ላይ ባለመሳተፍ፣ የሙያውን ተዓማኒነት የሚያሳጡ ጉዳዮች ውስጥ ባለመሳተፍ፣ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዓላማ በማክበርና እንዲሳካ ጥረት በማድረግ ነው፡፡

9) **ገለልተኝነት፡** አደራጁ ሙያዊ ግዴታውን ለመወጣት ከአድልዎ ነፃ የሆነና የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ ከሚችሉ ሁኔታዎች ሁሉ በመቆጠብ ገለልተኛ ውሳኔዎችንና ሀሳቦች ለሰጥ ይገባል፡፡ ገለልተኝነት የአደራጁን የአዕምሮ ብስለትና እሴት የሚያሳይ መሠረታዊ የሙው መለያ ሆኖ ባለሙው በሚሰጠው አገልግሎት ሙያዊ ውሳኔዎችን አድልዎን በማስወገድ ገለልተኛ፣ ሀቀኛ እና የግል ጥቅም ፍላጎት ግጭት ከሚያስከትል ሁኔታዎች ነፃ እነዲሆን የሚያስገድድ መርህ ነው፡፡

10) **ሚስጥር መጠበቅ፡** አደራጁ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ያገኛቸውን የኅብረት ሥራ ማህበራትን መረጃዎች በጥንቃቄ መያዝ አለበት፡፡ የተገኘውን መረጃ ለማንኛውም የግል ጥቅም ወይም በህግ ከተፈቀደው ወይም ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥነ ምግባር

መርህ ውጪ መጠቀም የለበትም፡፡ ሲያደራጅም ሆነ ሲያጠናክር የኅብረት ሥራ ማህበራትን መረጃ ለሌላ አካል አሳልፎ ከመስጠት መታቀብ ይኖርበታል፡፡

11) **ሙያዊ ብቃት፡** አደራጁ በሥራ ላይ መሠማራት የሚገባው በሥራው በቂ እውቀት፣ ክህሎት እና ልምድ ካለው ነው፡፡ አደራጁ ያለማቋረጥ ሙያዊ ብቃቱንና የአገልግሎት ጥራቱን ማሳደግ አለበት፡፡ ሁልጊዜ በለውጥ ውስጥ የሚኖር መሆን አለበት፡፡

## 144. የኅብረት ሥራ የምዝገባና መረጃ አያያዝ ባለሙያ ተግባርና ሃላፊነት

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት ዘመናዊ የምዝገባ አሰራር ስርዓት እና የመረጃ መረብ ዝርጋት የሚያግዝ ጥናት ያደርጋል፣ አማራጭ የአሰራር ማሻሻያ ስትራቴጂዎችን ይዘረጋል፣
2) የኅብረት ሥራ ማህበራት አሰያየም ወጥ እንዲሆንና በህግ ተቀባይነት እንዲኖረው የሚያስችል የምዝገባና የመረጃ አያያዝ አሰራር መመሪያ እና ማንዋል ያዘጋጃል፣ ያሻሽላል፣ ይተገብራል፤
3) የኅብረት ሥራ ማህበራት ስም አሰያየም ተመሳሳይ እንዳይሆን በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት መከናወኑን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
4) የኅብረት ሥራ ማህበራት ለምዝገባ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች፣ ፎርማቶች፣ ቅፃ ቅፆችን እና መዝገቦች ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ይመዘግባል፤ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት ይሰጣል፤
5) የኅብረት ሥራ ማህበራት የመተዳደሪያ ደንባንቻውን ሲያሻሽሉ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ይመዘግባል፤
6) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ስፈርስ አስፈላጊው ፎርማሊት መሟላቱን ያረጋግጣል፣
7) በጊዚያዊ ምስክር ወረቀት የተመዘገቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በተቀመጠው ጊዜ ገደብ በቋሚ እንዲመዘገቡ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤ መዝገብ ካልተመዘገቡ፣ ከመዝገብ ይሰርዛል፣
8) የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲዋሀድ ወይም እንዲከፈል ሲወሰን ከመዝገብ ይሰርዛል፤ ሰርተፊኬት ይቀበላል፤ ሰነዶችን ይረከባል፤ መረጃውን ይይዛል፣
9) በውህደት ወይም በመከፈል የሚደራጀው የኅብረት ሥራ ማህበራትን ይመዘግባል፣ ሰርተፊኬት ይሰጣል፤
10) የኅብረት ሥራ ማህበራት በተለያዩ ምክንያት ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ ህጋዊ ሆነው እንዳይሰሩ ሰርተፍኬቱን በጊዜያዊነት ይቀበላል፣
11) የኅብረት ሥራ ማህበራት ህግ በሚያዘው መሰረት የኅብረት ሥራ ሊግ እንዲደራጅ ሲወሰን በሀገር አቀፍ ደረጃ መዝግቦ ሠርተፍኬት ሰጣል፣ እንዲፈርስ ሲወሰን ከመዝገብ ይሰርዛል፣
12) የተመዘገቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ያደራጃል፣ መረጃ ይይዛል፣ መረጃውን ያሰራጫል፣
13) እንዲፈርሱ የተወሰኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሰነዶች ይረከባል፣ አግባብ ባለው ቦታ ያስቀምጣል፣ መረጃውን ይይዛል፣ መረጃውን ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፣

## 145. የኅብረት ሥራ ማህበራት የምዝገባና መረጃ አያያዝ ባለሙያ ስነምግባር

የኅብረት ሥራ ማህበራት የምዝገባና መረጃ አያያዝ ባለሙያ የሚከተሉት ባህሪያት ይኖሩታል፣

1) በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥነት ያለውና እርስ በርስ የሚናበብ የምዝገባና መረጃ አያያዝ አሠራር ስርዓት መከተል፣
2) የምዝገባና መረጃ አያያዝ ባለሙያ ከተፅዕኖ ነፃ በመሆን የሙያውን ገለልተኛነት ተጠቅሞ አዋጅ፣ ደንብና የምዝገባ መመሪያ ተከትሎ በንፁህ ህሊና የሙያ ስንምግባሩን አክብሮ በመስራት ከኢኮኖሚ እና የፋይናንስ ጥገኝነት ራሱን መጠበቅና አግባብነት ባለው ግንኙነት ተገቢውን ሙያዊ ድጋፍና አስተያየት በነፃነት መስጠት ይኖርበታል፡፡
3) የምዝገባና መረጃ አያያዝ ባለሙያ ራሱን በእውቀት ያበቃ በቂ መረጃ በማሰባሰብ፣ ተገቢውን ጥናት ማድረግና ከችኮላ እና ከግዴለሽነት ነፃ ሆኖ እውቀትን መሰረት በማድረግ የሚከናውን መሆን ኖርበታል፣

4) የምዝገባና መረጃ አያያዝ ባለሙያ ከግዴለሽነት አሰራር ነፃ በመሆን፣ ለሚያከናውናቸው ተግባራት ጠንቃቃና አስታዋይ መሆን ይኖርበታል፡፡

5) የምዝገባና መረጃ አያያዝ ባለሙያ በሥራው ቦታ፣ በኅብረተሰቡ መካከል እና በኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራ አመራርና ሠራተኞች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ከብልሹ አሰራር ገለልተኛ፣ ታማኝ፣ ተግባቢ እና ገብረ-ገብ መሆን አለበት፡፡

6) የምዝገባና መረጃ አያያዝ ባለሙያ የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያዎችን ማወቅ፣ ማክበርና መስከበር ይኖርበታል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት መተዳደሪያ ደንብ እና የውስጠ ደንብ በሚገባ ማወቅና መደገፍ ይኖርበታል፡፡

7) የምዝገባና መረጃ አያያዝ ባለሙያው ስራውን በጥንቃቄ እና በሃላፊነት በመቀበል፣ የሙያውን ተዓማኒነት የሚያሳጡ ጉዳዮች ውስጥ ባለመሳተፍ፣ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዓላማ በማክበርና እንዲሳካ ጥረት በማድረግ ተዓማኒነት የተላበሰ አግልግሎት መስጠት ነው፡፡

8) የምዝገባና መረጃ አያያዝ ባለሙያው ሙያዊ ግዴታውን ለመወጣት ከአድልዎ ነፃ የሆነና የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ ከሚችሉ ሁኔታዎች ሁሉ በመቆጠብ ገለልተኛ ውሳኔዎችንና ሀሳቦች ሲሰጥ ሀቀኛ እና የግል ጥቅም ፍላጎት ግጭት ከሚያስከትል ሁኔታዎች ገለልተኛ እንዲሆን የሚያስገድድ ባህሪ ነው፡፡

9) የምዝገባና መረጃ አያያዝ ባለሙያው ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ያገኛቸውን የኅብረት ሥራ ማህበራትን መረጃዎችን ሚስጥር መጠበቅና በጥንቃቄ በመያዝ ለማንኛውም የግል ጥቅም ወይም በህግ ከተፈቀደው ወይም ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥነ ምግባር መርህ ውጪ መጠቀም የለበትም፡፡

## 146. የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

1) የገበሬዎች የአደረጃጀት መመሪያ ቁጥር/001 በዚህ አንቀጽ ተሽሯል፡፡

2) ይህንን መመሪያ የሚጻረሩ እና የሚቃረን መመሪያ፣ ልማዳዊ አሰራር እና በመተዳደሪያ ደንብ እና ውስጠ ደንብ ውስጥ የተቀመጠ አንቀጽ ተፈጻሚነት አይኖራውም፣

## 147. የመተባበር ግዴታ

ማንኛዉም ሰው ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 148. ስለመመሪያው መሻሻል

ይህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 149. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ  የጸና ይሆናል፣

**አዲስ አበባ ግንቦት 26/2014 ዓ.ም**

**ወ/ሮ ፍሬአለም ሽባባው**

**የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር**